# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 044 ጥቅምት 14 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# “ብሪክስ አብሮ የማደግን ትልቅ እድል ይዞ መጥቷል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ብሪክስ በሁለተናዊ መስኮች አብሮ የማደግን ትልቅ እድል ይዞ መጥቷል ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። ኢትዮጵያ በፍትሃዊነት መርህ ላይ የተመሠረተ ተሳትፎ ለማድረግ ዝግጁ መሆኗንም ጠቁመዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሩሲያ ካዛን ከተማ እየተካሄደ ባለው 16ኛው የብሪክስ መሪዎች ጉባዔ ላይ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ በብሪክስ ውስጥ ትልቅ አብሮ የማደግ እድል አለ። ይህን ዕድል አባል ሀገራቱ መካከል በንግድ፣ በኢንቨስትመንትና በቱሪዝም ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ እድገት ይዞ መጥቷል።

ብሪክስ ከዓለም ሕዝብ ግማሽ ያህሉን እንደሚወክል ገልጸው፣ ብሪክስ የለውጥ ሃይል የመሆን አቅም እንዳለውና ፍትሃዊ የዓለም ሥርዓት የሚያሰፍን እንደሚሆን አስረድተዋል።

ብሪክስ አባል ሀገራቱ መካከል ንግድ፣ ኢንቨስትመንትና ቱሪዝም ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ እድገት ማስፈን እንደሚችል የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የተለያዩ

“ብሪክስ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል














# በክልሉ ከ800 ሺህ በላይ ጎብኚዎች የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎችን ጎበኙ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከ800 ሺህ በላይ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ጎብኚዎች የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎችን መጎብኘታቸውን

በክልሉ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# የአፍሪካ የደህንነት ስጋቶችን በጠንካራ ህብረት



**አዲሱ ገረመው**

የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች "አፍሪካ በጠንካራ አንድነት፣ ለሁለንተናዊ ፀጥተና ሰላም" በሚል መሪ ሃሳብ በቅርቡ በአዲስ አበባ ባካሄዱት ጉባዔ ትብብርን ማጠናከር የሚለው አጀንዳ ጎልቶ ወጥቷል። በወቅቱ፤ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ በአፍሪካ ጸጥታን ጨምሮ እያጋጠሙ ያሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት ሌሎችን መመልከት ሳይሆን በአንድነት መቆም ይገባል ማለታቸውም አይዘነጋም። ለመሆኑ በአፍሪካ የተረጋጋ የጂኦ ፖለቲካ ሁኔታ እንዲኖር ምን መደረግ አለበት?

የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስትር አይሻ መሐመድ፤ የአፍሪካ የፀጥታ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስብስብ እየሆነ መምጣቱን ይገልጻሉ። የጸጥታ ችግሮቹ ሽብርተኝነትን፣ የፖለቲካ አለመረጋጋትን እና የሳይበር ስጋቶችን ጨምሮ በበርካታ የተጠላለፉ ተግዳሮቶች የተሞሉ ናቸው ይላሉ። በቅርቡ በአዲስ አበባ የተካሄደው የአፍሪካ መከላከያ ሚኒስትሮች ጉባዔና ሌሎች አፍሪካዊ አጀንዳ ያላቸው ሁነቶች እነዚህን ተግዳሮቶች በጋራ ለመፍታት አስፈላጊ መሆናቸውንም ይጠቅሳሉ። “አንድ ሀገር ብቻውን እነዚህን ተግዳሮቶች ሊጋፈጥ አይችልም” በማለት፤ በአፍሪካ ሀገሮች መካከል የተቀናጀ አካሄድ እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

የአፍሪካ ህብረት ቀጣናዊ ትብብርን በማጎልበት ረገድ በተለይም የአፍሪካ ተጠባባቂ ኃይል ለመመሥረት እና ሌሎች ውጥኖችን ለማሳካት የህብረቱ አባል ሀገራት ጠንካራ አንድነት መፍጠር እንዳለባቸውም ነው የሚመክሩት። እሳቸው ይህን ይበሉ እንጂ እነዚህ ጥረቶች በቂ የገንዘብ ድጋፍ ባለመኖሩ እና በአባል ሀገራቱ መካከል የፖለቲካ ፍላጎት ባለመኖሩ ብዙ ጊዜ አፍሪካ

የአፍሪካ የደህንነት ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



TAZMA ታዝማ
Medical & Surgical Specialized Center
የውስጥ ደዌና የቀዶ ሕክምና ልዩ ማዕከል

# በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ነፃ የልብ ቀዶ ህክምና ተደረገ

**ሔርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ አስተባባሪነት በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ብቻ ነፃ የልብ ቀዶ ጥገና የህክምና ማድረጉን የታዝማ የውስጥ ደዌ እና የቀዶ ሕክምና ልዩ ማዕከል አስታወቀ፡፡

የማዕከሉ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አስቻለው አለማየሁ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳሉት፤ ማዕከሉ በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ አስተባባሪነት በአካባቢው ለሚገኙ የልብ ህሙማን በሀገር ውስጥ ባለሙያዎች ብቻ ነፃ የልብ ቀዶ ሕክምና አገልግሎት ሰጥቷል፡፡

ቀዶ ህክምናው በጂግጂጋ ዩኒቨርሲቲ ሼይኽ ሀሰን ያባሬ አጠቃላይ ልዩ ሆስፒታል በመገኘት መደረጉን ጠቅሰው፤ የቀዶ ህክምናው ከአዲስ አበባ ውጪ ለመጀመሪያ ጊዜ መደረጉን እና በሀገር ውስጥ የህክምና ቡድን ብቻ የተዋቀረ መሆኑ ልዩ እንደሚደርገው አመልክተዋል፡፡

አሁን የተደረገው የልብ ቀዶ ህክምና ከአምስት ዓመት ህፃን ጀምሮ እስከ 42 ዓመት የዕድሜ ክልል ድረስ ለሚገኙ ታካሚዎች መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ህክምናው የተሰጠው ልብ እና ሳምባን ተክቶ የሚሠራ መሣሪያን ጨምሮ ሌሎች አስፈላጊ ግብአቶች ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ወደ ጅግጅጋ በመውሰድ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ለቀጣይ ተመሳሳይ የልብ ቀዶ ጥገና ለማከናወን እና በልብ ህክምናው ዘርፍ ብቁ ባለሙያዎችን ለማፍራት ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ጋር ስምምነት መደረጉን ገልፀዋል። ማዕከሉ ከዚህ ቀደም ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ጋር በልብ ህክምናው ዘርፍ ብቁ ባሙያዎችን ለማፍራት እና የህክምና መሣሪያ ለመጠቀም ስምምነት መደረጉን አስታውሰዋል።

በሱማሌ ክልል አካባቢው ያለው ማህበረሰብ ወደ አዲስ አበባ እየመጣ አገልግሎቱን ያገኝ እንደነበር አውስተው፤ የክልሉ ጤና ቢሮና የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ከማዕከሉ ጋር በመተባበር አቅማቸው ለማይፈቅድ ታካሚዎች ህክምናውን ባሉበት በነጻ እንዲያገኙ ማድረጉን ጠቁመዋል። በቀጣይ ተቋሙ ወደ ሌሎች አካባቢዎች በመሄድ ተመሳሳይ ሥራ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ቀጣይነት ያለው ቀዶ ህክምና እንዲሰጥ እና ግብዓት ለማሟላት የሚያስፈልግ ወጪ እና የሰው ኃይል ባለሙያ አስፈላጊውን ጥናትና ውይይት መደረጉን ጠቅሰው፤ ይህም በጅግጅጋ ከተማ ቀጣይነት ያለው የልብ ህክምና ሥራ ለመሥራት የሚያስችል መሆኑን አብራርተዋል፡፡

# ተስፋ ሰጪው የጥጥ ምርምር

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

**ዜና ሐተታ**



የጥጥ ምርምር በኢትዮጵያ ስድስት አስርት ዓመታትን እንዳስቆጠረ የጥጥ ተመራማሪዎች ያነሳሉ፡፡ የጥጥ ሰብል በከፍተኛ ሁኔታ በተባይ ተጠቂ በመሆኑ የምርት ሂደቱ ከፍተኛ ጥንቃቄን እንደሚሻም ያስረዳሉ፡፡ ጥጥን ከተባይ ለመከላከል በምርት ወቅት እስከ አምስት ጊዜ ድረስ የኬሚካል ርጭት ይደረጋል። ይህም ለከፍተኛ የሰው ኃይል እና የገንዘብ ወጪ መዳረጉን ተመራማሪዎች ይናገራሉ፡፡

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የወረር ግብርና ምርምር ማዕከል ለመላው ሀገሪቱ የጥጥ ዘር አቅራቢ ሲሆን፣ ከ1958 ዓ.ም ጀምሮ በመስኖ እየታገዘ የምርትና ጥራት ደረጃቸው የተሻሻሉ የጥጥ ዘሮችን ለተጠቃሚዎች ሲያቀርብ ቆይቷል፡፡

በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የወረር ግብርና ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር አቶ ሽመልስ አለማየሁ እንዳሉት፣ ወረር ግብርና ማዕከል በአካባቢው እየለማ የነበረውን ጥጥ በተሻሻሉ የግብርና ቴክሎጂዎች ለመደገፍ ታስቦ በ1956 ዓ.ም ነው የተቋቋመው። ማዕከሉ የጥጥ ምርትን ዓላማ አድርጎ ይቋቋም እንጂ፣ በጊዜ ሂደት በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና ሌሎችም የምርምር መስኮች ላይ በርካታ ሥራዎችንም ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

በማዕከሉ በጥጥ ላይ ሲካሄድ የነበረው ምርምር በዋናነት የምርት መጠንን ለመጨመር ትኩረት ያደረገ መሆኑን አስታውሰው፤ በኋላ ላይ ወደ ምርት ጥራት ምርምር መሸጋገሩን ይገልጻሉ፡፡

በምርምር ማዕከሉ የጥጥ ምርምር ፕሮግራም ራሱን ችሎ የተቋቋመው በ1981 ዓ.ም መሆኑን አንስተው፤ ከፕሮግራሙ መቋቋም በኋላ የኢንዱስትሪ ሰብሎች ምርምር ፕሮጀክትን በመጀመር የጥጥ ዘረመሎችን መጨመር፣ የምርት ብክነትን ማጥናትና መፍትሔ ማፈላለግ፣ የጥጥ ጥራትን መጨመርና አርሶ አደሩ በቀላሉ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ የተባይ መከላከያዎች ለማምረትን ዓላማው አድርጎ ሲሠራም ቆይቷል፡፡

ፕሮጀክቱ በመስኖና በጥጥ በሚለሙ የሀገራችን አካባቢዎች ተስማሚ የሆኑ በድምሩ 43 የተሻሻሉ የጥጥ ዝርያዎችን በምርምር በማውጣት በአብዛኛው ተጠቃሚው ጋር እንዲደርሱ አድርጓል ይላሉ። ከተሻሻሉ የጥጥ ዝርያዎች ውስጥ በአሁኑ ወቅት በመመረት ላይ ያሉት ውስን ስለሆኑ ከሶስት ዓመታት ወዲህ ደግሞ፣ ከፍተኛ ምርት መስጠት የሚችሉ አራት ዝርያዎችን ከምርምር ማዕከሉ ማውጣት ተችሏል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

ዳይሬክተሩ እንደሚጠቁሙት፤ በአጠቃላይ በሰብሉ ላይ በተደረጉ ምርምሮች በ1960ዎቹ በሄክታር 18 ኩንታል የነበረውን የምርት መጠን በአሁኑ ሰዓት ወደ 54 ነጥብ 3 ኩንታል ማድረስ ተችሏል፡፡

የጓይ ትል የሚያስከትለውን የምርት መቀነስና ለኬሚካል ግዢ የሚወጣውን ወጪ መቀነስ የሚያስችሉ ቢፒ ጥጥ የተሰኘ ዝርያን ከውጭ አስገብቶ ማላመድም የተቻለ ሲሆን፣ ሌሎች ዝርያዎችንም በማፍለቅ በግምገማ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡

በጥጥ ላይ የተደረጉ ምርምሮች ረጅም መንገድ የተጓዙና ሰፊ ለውጥም የተገኘባቸው ቢሆኑም ሰብሉ የሚፈለገውን ያህል ትኩረት ያገኘ አለመሆኑ፣ የጥጥ ተጠቃሚ ኢንዱስትሪዎች የሀገር ውስጥ የጥጥ ምርትን ከመጠቀም ይልቅ ከውጭ ማስገባት ላይ እንደሚያተኩሩ የተናገሩት የማዕከሉ ዳይሬክተር፣ የጥጥ ምርት ፍላጎት አለመኖር ምርቱ እንዳይጨምር እንቅፋት መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ ጥጥ ገበያ ከማጣቱ የተነሳ በያማሳው ላይ ገበያ ያጡ ትልልቅ የጥጥ ክምሮች እንደሚስታወሉም ነው ዳይሬክተሩ የተናገሩት፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ በሀገራችን ለጥጥ ምርት ምቹ የሆነ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ቢኖርም ከዚህ ውስጥ ጥቅም ላይ ማዋል የተቻለው አራት ከመቶ እንኳ የማይሞላ 101 ሺህ ሄክታር ብቻ።

ኢንዱስትሪዎቻችን ኢትዮጵያ ጥጥ የማምረት አቅሟ እስከምን ድረስ ነው? የሚለውን ግንዛቤው ያላቸው አይመስለም ያሉት ዳይተሬክተሩ፤ ይህን ችግር ለመፍታት ደግሞ አምራችን ከምርት ፈላጊው የሚያቀራርብ አካልና አሠራር ይፈልጋል ሲሉ ያስረዳሉ።

መንግሥትና ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የግብርና ሚኒስቴርና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ተቀራርበው መሥራት ቢችሉ የጥጥ ምርትን ለሀገራችን ጨርቅ አምራች ኢንደስትሪዎች ብቻ ሳይሆን፣ ልክ ወደ ውጪ እንደምንልካቸው ቡና እና መሰል ምርቶች ሁሉ ወደ ውጪም በመላክ የውጭ ምንዛሪን ማስገኘት ይቻላል ይላሉ፡፡

የዘርፉ ተመራማሪ አቶ ዶኒስ ጉርሜሳ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ከሁለት ወራት በፊት በመልካ ሰዲ ብሔራዊ የጥጥ ምርምር የመስክ ቀን ሲያካሂድ እንደተናገሩት፤ የመልካ ሰዲ የጥጥ ምርምር የሙከራ ማሣ በሁለት ነጥብ አምስት ሄክታር ላይ የሚደረግ ሙከራ ነው።

በባዮቴክኖሎጂ የታገዘውና በሌሎች ዓለማት ውጤታማ በመሆኑ የተመሠከረለት የቢቶ ኮተን ዘር እና በማዕከሉ በምርምር ላይ የሚገኘው ምርምር ለበሽታ እና ለጥጥ ተባይ እስከ አምስት ጊዜ በተደጋጋሚ የሚረጨውን የኬሚካል ርጭት የማይፈልግ መሆኑን ይገልጻሉ።

የጥጥ ተባይን ለመከላከል በተደጋጋሚ የሚደረገው የኬሚካል ርጭት የሰው ኃይል እና የኬሚካል ዋጋ ከፍተኛ ወጪ መሆኑን የዘርፉ ተመራማሪ አንስተው፤ ምርምሩ ተስፋ ሰጪ ውጤት የተገኘበት መሆኑን ነው ያነሱት።

# ስምምነቱ አመቺ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመዘርጋት ያስችላል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ከጃፓኑ ዶዳይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ አምራች ካምፓኒ ጋር ያደረገው ስምምነት በኢትዮጵያ ዘላቂና አመቺ የትራንስፖርት አገልግሎትን ለመዘርጋት የሚያስችል መሆኑን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ብሩክ ታዬ (ዶ/ር) እና የዶዳይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ አምራች ኩባንያ መሥራች እና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዩማ ሳኪ የመግባቢያ ስምምነቱን ተፈራርመዋል።

በዚሁ ወቅት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ብሩክ ታዬ (ዶ/ር)፤ ስምምነቱ የድርጅታቸው አጠቃላይ ራዕይ ከሆነው የገቢ ዋስትናን ከማረጋገጥ፣ ኢኮኖሚን ከመምራት፣ ለማህበረሰቡ መሠረታዊ ምርትና አገልግሎት ከማድረስ ጋር የተያያዘ መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ በሥራ እድል ፈጠራ ላይ ትኩረት ያደረጉ ቢዝነሶች ላይ ኢንቨስት ያደርጋል ያሉት ዶክተር ብሩክ፤ የአየር ንብረት ለውጥን ለመግታት ታሳቢ ያደረጉ ሀገራዊ ስትራተጂዎችን ለማስፈጸም የሚረዱና ለኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሥራ ሃሳቦችን እንደሚያበረታታም ጠቁመዋል።

አክለውም፤ ትብብሩ በኢትዮጵያ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ሞተር ብስክሌቶችን በስፋት በማቅረብ በትራንስፖርት ዘርፍ ውስጥ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት የትራንስፖርት ሥርዓቱን ለማቀላጠፍ እንደሚያግዝ ተናግረዋል።

ታዳሽ ሃይል ላይ የተመሠረተ የትራንስፖርት ሥርዓት መዘርጋት የካርበን ልቀትን በከፍተኛ መጠን እንደሚቀንስ የገለጹት ዶክተር ብሩክ፤ ስምምነቱ የታለመለትን ግብ እንዲመታ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ አስፈላጊውን ሁሉ እንደሚያደርግ አንስተዋል፡፡

የዶዳይ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ አምራች ኩባንያ መሥራች እና ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዩማ ሳኪ በበኩላቸው፤ አጋርነቱ የኢትዮጵያን የትራንስፖርት ዘርፍ ወደ ኤሌክትሪክ ተኮር ተሽከርካሪዎች ለመቀየር ወሳኝ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ኩባንያው በቀጣይ በ12 ወራት ውስጥ እስከ 100 የባትሪ መለዋወጫ ጣቢያዎችን በመትከል፤ የአጠቃቀም መረጃ በመሰብሰብ ቀልጣፋ አገልግሎት እንደሚሰጥ ዩማ ሳኪ አመላክተዋል።

በሶስት ዓመታት ውስጥ በአዲስ አበባ እና በሸገር ከተማ ለሚገኙ ነዋሪዎች የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ተደራሽ ማድረግም ዓላማችን ነው ያሉት ዩማ ሳኪ፤ ዶዳይ አስተማማኝ የባትሪ መለዋወጫ ጣቢያዎችን እና




**ብሩክ ታዬ (ዶ/ር) እና ዩማ ሳኪ የመግባቢያ ስምምነቱን ፈርመዋል**

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ መሠረተ ልማቶችን በማቅረብ የኢትዮጵያን የከተማ ትራንስፖርት ገጽታ ለመለወጥ ያለመ ኩባንያ ነው ብለዋል።

# የ14 ሀገራት ድርጅቶች የሚሳተፉበት የእንስሳት ሀብት ልማት አውደ ርዕይ ሊካሄድ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**




አዲስ አበባ፡- በእንስሳት ሀብት ልማት ከ14 የተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ ውጤታማ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሚሳተፉበት ዓለም አቀፍ አውደ ርዕይ ከጥቅምት 21 ጀምሮ ለሶስት ቀናት በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ እንደሚካሄድ ተገለፀ።

አውደ ርዕዩ በግብርና ሚኒስቴር፣ በኢትዮጵያ እንስሳት ልማት ኢንስቲትዩት፣ በኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን፣ በኤስኤንቪ - የኔዘርላንድስ ልማት ድርጅት ፕሮግራም እንዲሁም በዓለም አቀፍ የነፍሳት ፊዚዮሎጂ እና ሥነ ምህዳር ማዕከል (ICIPE) የተዘጋጀ ሲሆን ይህም በእንስሳት ሀብት ልማትና የተዋጽኦ ምርቶች ላይ ትኩረት ያደረገ መሆኑ ተገልጿል።

የአውደ ርዕዩ አስተባባሪና የፐራና ኢቨንት ዳይሬክተር አቶ ነብዩ ለማ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደተናገሩት፤ አውደ ርዕዩ የእንሰሳት ሀብት የገበያ ሰንሰለቶች ላይ ያሉ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለማስተዋወቅ፣ የገበያ ትስስር ለመፍጠር እንዲሁም የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት ይረዳል። በዚህም ከ100 በላይ ዓለም አቀፍ የእንስሳት ሀብት ዘርፍ ተዋናዮች ይሳተፋሉ።

ለሶስት ቀናት በሚካሄደው ዓውደ ርዕይና ጉባዔ ከቻይና፣ ቼክ ሪፐብሊክ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ ህንድ፣ ኬንያ፣ ጆርዳን፣ ኔዘርላንድስ፣ ስኮትላንድ፣ ቶጎ፣ ቱርክ፣ ዩጋንዳ እና አሜሪካ የሚመጡ ዓለም አቀፍ የዘርፉ መሪዎች እና ጠንካራ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ከንግድ ጎብኚዎች ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

በዚህም 13ኛው የኢትዮ ፖልተሪ ኤክስፖ (ኢትዮፔክስ)፣ 9ኛው የአፍሪካ እንስሳት ዓውደ ርዕይና ጉባዔ (አሌክ) እንዲሁም 4ኛው የአፒካልቸር እና አኳካልቸር ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የንግድ ትርዒትና ዘንድሮ የሚጀመረው የባዮ ኢነርጂ የንግድ ትርዒት እንደሚካሄድ ጠቁመዋል።

በኹነቱ ከ5000 በላይ የኢትዮጵያ፣ የምስራቅ አፍሪካ እና ዓለም አቀፍ ሀገራት ጎብኚዎች እንደሚገኙም ተናግረዋል።

የኔዘርላንድ መንግሥት ኤምባሲ የግብርና አማካሪ ሚስተር ሚዩዌስ ብሩወር በበኩላቸው፤ በአውደ ርዕዩ ከዶሮ ርባታ ጋር የተያያዙ ምርቶችን እና አገልግሎቶቻቸውን እንደ መኖ፣ መሣሪያ፣ ክትባቶች እና የማርቢያ ቴክኖሎጂዎች ይቀርባል ብለዋል።

አውደ ርዕዩ ለተሳታፊዎች ግንኙነቶችን ለመገንባት እና የንግድ እድሎችን ለማሰስ ከኢንዱስትሪ ባለሙያዎች፣ ደንበኞች እና አቅራቢዎች ጋር የሚገናኙበትን ዕድል እንደሚፈጠርም ጠቁመዋል።

ባለሙያዎች ስለ የዶሮ ርባታ ኢንዱስትሪው የተለያዩ ገጽታዎች፣ የምርት ቴክኒኮችን፣ በሽታን መከላከል እና የገበያ አዝማሚያዎችን ጨምሮ ግንዛቤዎችን እና ዕውቀትን ያጋራሉ ብለዋል።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሮ ጽጌሬዳ ፍቃዱ በበኩላቸው፤ መንግሥት በዘርፉ ያለውን ምርታማነት ለማሳደግ በሌማት ትሩፋት ዕቅዱ ፕሮግራም ነድፎ የወተት፣ ዕንቁላልና የዶሮ ስጋ እንዲሁም የማር ምርት ለማሳደግ እንቅስቃሴ መጀመሩ ይታወቃል ብለዋል።

በዚህም የላም ወተት ምርትን አሁን ካለበት 6 ነጥብ 9 ቢሊዮን ሊትር ወደ 11 ነጥብ 7 ቢሊዮን ሊትር፤ የዕንቁላል ምርትን ከ3 ነጥብ 2 ቢሊዮን ወደ 9 ነጥብ አንድ ቢሊዮን እና የዶሮ ስጋ ምርትን ከ90 ሜትሪክ ቶን ወደ 296 ሺህ ሜትሪክ ቶን እንዲሁም የማር ምርትን ከ147 ሺህ ወደ 296 ሺህ ሜትሪክ ቶን ለማሳደግ ግብ አስቀምጦ እየሠራ መሆኑን ገልፀዋል።

በአጠቃላይ አውደ ርዕዩ በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ውስጥ አስፈላጊውን አስተዋፅኦ የሚያደርግ መሆኑ በመድረኩ ተገልጿል፡፡

# ኢትዮጵያና ቻይና በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ያላቸውን ግንኙነት አጠናክረው ለማስቀጠል እየሠሩ ነው

## - በኢትዮጵያ የሚገኘውን የሉባን ወርክሾፕ ለማስፋፋት የሚረዳ ስምምነት ተፈረመ

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያና ቻይና በቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ያላቸውን ግንኙነት አጠናክረው ለማስቀጠል እየሠሩ መሆኑን የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ከድር (ዶ/ር) ገለጹ። በኢትዮጵያ የሚገኘውን የሉባን ወርክሾፕ ለማስፋፋት የሚረዳ ስምምነት መፈረሙንም ጠቁመዋል።

በቻይና ምክትል ትምህርት ሚኒስትርና በሀገሪቱ ኮሙኒስት ፓርቲ ተወካይ ዉ ያን የተመራ ልዑክ የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያና ሥልጠና ኢንስቲትዩትን ትናንት ጎብኝቷል።

የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ከድር (ዶ/ር) ጉብኝቱን አስመልክተው ለመገናኛ ብዙሃን በሰጡት ማብራሪያ፤ ቻይናውያን የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያና ሥልጠና ኢንስቲትዩትን ከመገንባት ጀምሮ፣ ሙያቸኞችን በመላክ፣ የመምህራንን አቅም በማሳደግ እና ሌሎች ድጋፎችን በማድረግ ከኢትዮጵያ ጋር የረጅም ጊዜ አጋርነት አላቸው።

በቀጣይም ቻይና እና ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂ ልማት፣ በሥልጠና ጥራት እና በቴክኒክና ሙያ ዘርፎች ጥራት ሊያመጡ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ትብብራቸውን አጠናክረው እንደሚያስቀጥሉ ጠቁመዋል።

የዩኒቨርሲቲ ዩኒቨርሲቲ ግንኙነትን በማጠናከር የኢትዮጵያ ተማሪዎች ቻይና ሄደው እንዲሠለጥኑ እንዲሁም ቻይናውያን አሠልጣኞች ኢትዮጵያ መጥተው እንዲያሠልጥኑ የሚያደርግ ተከታታይ የመምህራን የአቅም ግንባታ በመስጠት የሁለቱን ሀገራት ግንኙነች ለማጠናከር እንደሚሠራም አብራርተዋል።

የሁለቱን ሀገራት የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ለማጠናከር የቲያንጂን ቴክኖሎጂ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ እና የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያና ሥልጠና ኢንስቲትዩት በኢትዮጵያ የሚገኘውን የሉበን ወርክሾፕ ለማስፋፋት የሚረዳ ስምምነት መፈራረማቸውን አስታውቀዋል።

ቴክኒክና ሙያ ከፍተኛ መዋለ ንዋይ የሚጠይቅ ተቋም በመሆኑ የተፈረመው ስምምነት ለኢትዮጵያ የሥልጠና ጥራትን ለማሳደግ፣ የግብዓት አቅርቦትን ለመጨመር እና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል ነው ያሉት።

የቻይና ፕሬዚዳንት ከአራት ዓመት በፊት በተመረጡ የተለያዩ ሀገራት የሉባን ወርክሾፕን ለማቋቋም ባመነጩት ሃሳብ በኢትዮጵያ የሉባን ወርክሾፕ መቋቋሙን አስታውሰው፤ ወርክሾፑ በአርተፊሻል ኢንተለጀንስ እና በሮቦቲክስ ላይ ትኩረቱን አድርጎ ዘመኑን የሚመጥኑ ሥልጠናዎች እየተሰጡበት ነው ብለዋል።

በሉባን ወርክሾፕ ሠልጣኝ መምህራን፣ የኢንዱስትሪ ተዋንያኖች እና አጫጭር ሥልጠና የሚወስዱ ተማሪዎች ተጠቃሚ እየሆኑ መሆናቸው ገልጸው፤ ባለሙያዎች በጨርቃጨርቅ፣ በመጠጥ፣ በሲሚንቶ እና በሌሎች ዘርፎች ክህሎታቸውን የሚያዳብሩበት ሥልጠና እያገኙ መሆኑን አስረድተዋል።

የቲያንጂን ቴክኖሎጂ ትምህርት ዩኒቨርስቲ ሉባን ወርክሾፕን በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት እንዲያቋቁም ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም መሆኑን አመልክተው፤ በኢትዮጵያ ያለውን የሉባን ወርክሾፕ በሰው ሃይል፣ በግብዓት እና በቴክኖሎጂ ለማሳደግ በትኩረት እንደሚሠራ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል በቻይና ምክትል ትምህርት ሚኒስትርና በሀገሪቱ ኮሙኒስት ፓርቲ ተወካይ ው ያን የተመራ ልዑክ የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩትን የጎበኙ ሲሆን፤ ጉብኝቱ ሁለቱ ሀገራት በትምህርቱ ዘርፍ ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር ዓላማ ያደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያና ሥልጠና ኢንስቲቲዩት የቴክኒክና ሙያ አሠልጣኞችን፣ ቴክኒሻኖችን እና መሪዎችን የማፍራት ተልዕኮ የተሰጠው ተቋም ሲሆን፤ ይህንን ተልዕኮ ለመወጣት የውስጥ አቅም የመገንባትና ጊዜውን የዋጀ ቴክኖሎጂ መላበስ አለበት ሲሉ ተናግረዋል።

ይህንንም ጥረት ማሳካት የሚቻለው በሀገር ውስጥ ካሉ አጋር አካላት በተጨማሪ ዓለም አቀፍ አጋሮችን ማፍራት ሲቻል መሆኑን በመጠቆም፤ ኢንስቲትዩቱ ከቻይና ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከር የሚያስችለውን ስምምነት አድርጓል።

ስምምነቱን የቲያንጂን ቴክኖሎጂ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ሊቀመንበር ዣንግ ጂንጋንግ እና የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ከድር (ዶ/ር) የፈረሙት ሲሆን፤ የሥራና ክህሎት ሚኒስትር ሙፈሪሃት ካሚል እና የቻይና ምክትል ትምህርት ሚኒስትርና የሀገሪቱ ኮሙኒስት ፓርቲ ተወካይ ዉ ያን ተገኝተዋል።

ቻይናውያን የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩትን ከመገንባት ጀምሮ፣ ሙያተኞችን በመስጠት፣ የመምህራንን አቅም በማሳደግ እና የተለያዩ ድጋፎችን ማድረጋቸውን አስታውሰዋል።

# የበረሃው ፈውስ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**ዜና ሐተታ**

ወታደራዊ ማሠልጠኛው ከተመሠረተበት 1972 ዓ.ም ጀምሮ ለብዙሃኑ ፈውስ በመሆን ዘመናትን ተሻግሯል፡፡ የሠራዊትና የሠራዊት ቤተሰብ እንዲሁም ለአካባቢው ማህበረሰብ የጤና አገልግሎት በመስጠት የቀኝ እጅ ሆኖ አገልግሏል፡፡ የጦላይ ከፍተኛ ባለሌላ ማዕረግተኛ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ሆስፒታል፡፡

ሆስፒታሉ ትምህርት ቤቱ ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ እስከ አሁንም በሁለተኛ ደረጃ ሆስፒታል የሚገኙ አገልግሎቶች እየሰጠ ይገኛል፡፡ በረሃ ላይ የተለያዩ ወረርሽኞች በየጊዜው ይከሰታሉ፡፡ ታዲያ ይህ የጤና ችግር ተቋቁሞ ለማለፍ፣ ብቁና ጤናማ የሀገርን ዳር ድንበር የሚያስጠብቅ ወታደሮች ለማፍራት የጤና ተቋሙ ሚና ከፍተኛ ነው። በተለይም ማሠልጠኛው የተመሠረተበት አካባቢ ከመሠረተ ልማት የራቀና ሌሎች ጤና ተቋማት በአካባቢው ባለመኖራቸው ሚናው ይበልጥ ከፍተኛ እንዲሆን አድርጎታል ሲሉ ነዋሪዎች ይናገራሉ፡፡

በጦላይ ከፍተኛ ባለሌላ ማዕረግተኛ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት የሁለተኛ ደረጃ ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተር ሻምበል ዶክተር መኮንን ጉቼ ለኢፕድ እንዳሉት፤ ሆስፒታሉ ማሠልጠኛው ተመሥርቶ ወደ ሥራ ከገባበት ጊዜ አንስቶ እስከአሁን የሚገባውን አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

ሆስፒታሉ በተለያዩ ጊዜያት ለሚገቡ ምልምል ሠልጣኞች፣ የሠራዊቱና የሠራዊቱ ቤተሰቦች እንዲሁም ለአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል የሚሉት ዶክተር መኮንን፤ በተለይ በአካባቢው ምንም አይነት የጤና ተቋም ባልነበረበት ጊዜ ህብረተሰቡን የጤና አገልግሎት ሲሰጥ እንደቆየ ያስታውሳሉ፡፡

እንደ ዶክተር መኮንን ገለጻ፤ በሆስፒታሉ የተመላላሽ ህክምና፣ ተኝቶ ህክምና፣ የማዋለድ አገልግሎት፣ የጽንስና እርግዝና ክትትልና፣ የቅድመ በሽታ መከላከል እንዲሁም ሌሎች ህክምናዎች በሁለተኛ ደረጃ ሆስፒታሎች መሰጠት ያለባቸው አገልግሎቶች አሟልቶ እየሰጠ ይገኛል፡፡ ሆስፒታሉ ማከም ብቻ ሳይሆን ቅድመ መከላከል ላይ ይበልጥ ትኩረት ይደረጋል። በማሠልጠኛው ያሉ ሁለት ክሊኒኮች ላይ አብዛኛው ሥራ የሚሠራው ቅድመ መከላከል መሆኑንም ነው ዶክተር መኮንን የሚጠቁሙት፡፡

ሆስፒታሉ አሁን ላይ በቀን ከ50 እስከ 60 ተመላላሽ ታካሚዎች እና እስከ 40 ተኝቶ ማከም የሚያስችል አቅም አለው፡፡ ሆስፒታሉ አሁንም ለአካባቢው ማህበረሰብ የኤች አይ ቪ ምርመራ እየሰጠ ነው፡፡ በተጨማሪም አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲገጥሙ አሁንም ተጨማሪ አገልግሎት ይሰጣል። ሆስፒታሉ በሀገሪቱ ጤናማ ሠራዊት ለመገንባት እያደረገ ያለው አስተዋጽኦ ጎን ለጎንም ስለ ጤና ሁኔታ በቂ ግንዛቤ እንዲኖረው እያደረገ እንደሆነ ያስረዳሉ።

አንዳንድ የህክምና መሻሪዎች፣ መሠረተ ልማትና የሙያተኛ እጥረት ቢኖርም ባለው ሀብት የሚጠበቀውን ያህል አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል ያሉት ደግሞ የሆስፒታሉ ሜዲካል ዶክተር ሌተናል ኮረኔል ነጋ ጣሰው ናቸው፡፡ አሁን ላይ የመከላከያ ሠራዊት አባላት ሠልጣኝ ምልምል ወታደሮችን እንዲሁም የሠራዊት ቤተሰቦች በአካባቢው የሚገኙ የሲቪል ሠራተኞች በተለይ የኤች አይ ቪ ህሙማን በሆስፒታሉ አገልግሎት እያገኙ ነውም ይላሉ፡፡

ሆስፒታሉ ሙያተኛው ከተሟላና ያሉበት የመሠረተ ልማት እንዲሁም የመሣሪያ እጥረቶች መቅረፍ ከቻሉ ከሠራዊቱና የሠራዊቱ ቤተሰብ በተጨማሪ ለአካባቢው ማህበረሰብ አገልግሎት የመስጠት አቅም እንዳለው ያስረዳሉ፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## እግር ኳሱን የማነቃቃት ትልቅ ርምጃ!

ስፖርት ረቂቅ ነው፤ ምክንያቱም፣ በስፖርት የማይታየው፣ የማይሰማው፣ የማያገናኘው ክስተት ስለሌለ ለአንድ ሀገር ኃይል ነው። ከዚህ በመነሳትም ስፖርት ሀገራዊ የልማት ማስፈፀሚያ መሣሪያ ስለመሆኑም ይነገራል። ይሄን ከሚያስብሉ ጉዳዮች መካከልም፣ ታላላቅ የሀገር መሪዎችን በአንድ የስፖርት መድረክ በማገናኘት ስለ ሀገራቸው የስፖርት ልማት ብሎም ሀገራዊ ብልፅግና የሚመክሩበት እንዲሁም ውሳኔ የሚያሳልፉበት በመሆኑ ነው።

ለዚህም ነው ዛሬ ላይ ሀገራት ስፖርትን በመጠቀም ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም ፖለቲካዊ ገፅታቸውን ለመገንባት ሲሠሩ የሚታየው። በዚህም በርካቶች ስፖርትን በመጠቀም ገጽታቸውን ገንብተዋል፤ ኢኮኖሚያዊ እድገታቸውንም አሳይተውበታል። ማህበራዊ ሁነትና እሴቶቻቸውንም ከፍ አድርገው ገልጠውበታል። ለዚህ ደግሞ የኦሎምፒክ ውድድሮች፣ የዓለም ዋንጫ እና የአህጉራት ስፖርታዊ ውድድሮች ከፍ ያለ ቦታ አላቸው፡፡

በአፍሪካ ደረጃም ስናይ፣ የአፍሪካ ዋንጫንና ሌሎች መሰል አህጉራዊም ሆነ ዓለምአቀፋዊ ውድድሮችን ለማስተናገድ ያለው ፍላጎት ከፍ ያለ ነው። ብዙ የአፍሪካ ሀገራትና ከተሞቻቸው እነዚህን ሁነቶች ለማስተናገድ ጥያቄን ከማቅረብ ጀምሮ የቻሉትን ሁሉ ሲጥሩ የሚታየውም ውድድሮቹ የሚያስገኙትን ከፍ ያለ ፋይዳ በመገንዘብ፤ እነዚህ ትልልቅ የስፖርት ሁነቶችም ለአጭር ጊዜም ይሁን ለረጅም ጊዜ ለማህበራዊ እና ለኢኮኖሚያዊ እድገት ጥቅም ስለሚያስገኙ፤ እንዲሁም የገፅታ ግንባታ ላይ ጉልህ ሚናን ስለሚጫወቱ ነው።

ይሁን እንጂ እንዲህ ያሉ ትላልቅ የስፖርት ሁነቶችን ማዘጋጀት እጅግ በጣም ፈታኝ ነው። ምክንያቱም ለሁለቱ የሚውሉ የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎችም ሆኑ ለደህንነት ሥራዎች ከፍተኛ ወጪን ይጠይቃሉ። ይሄን ከፍ ያለ የወጪ ጫና ተቋቁሞና ከሁነቱ የሚገኘውን ሁሉን አቀፍ ፋይዳ ተገንዝቦ ሁነቶች ለማዘጋጀት መወሰንና ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መግባት ደግሞ ከፍ ያለ ኃላፊነትን የመወጣት ውሳኔን ይጠይቃል፡፡

ምክንያቱም፣ እነዚህ ሁነቶች ከፍ ካለው ወጪያቸው ባሻገር ለአዘጋጁ ሀገርና ከተማ ትልቅ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ልማት አወንታዊ ተፅእኖ አላቸው። በተለይም የምጣኔ ሀብት እድገትን፣ የመሠረተ ልማት ግንባታን፣ ጤናማና ታታሪ ትውልድን የማፍራትን፣ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት መጨመርን፣ የሥራ እድልን መፍጠርን እና የከተሞች መስፋፋትን እድል ይዘው የሚቀርቡ ናቸው፡፡

በዚህ ረገድ የስፖርት ቱሪዝምን ማነቃቃት፣ የስፖርት ኢንቨስትመንትን ማሳደግ፣ የስፖርት ቤተሰቡን ማቀራረብ፣ የስፖርት ዲፕሎማሲን ማሳደግ እንዲሁ በሀገራዊ ገፅታ ግንባታ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት የኢትዮጵያን ስፖርት በበላይነት ከሚመራው የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በኃላፊነት ሊያከውናቸው ከሚገቡ ተግባራት መካከል ተጠቃሾች ናቸው።

በዚህ ረገድ ከ46ኛው የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ጠቅላላ ጉባዔ ጎን ለጎን ሰሞኑን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪ ሞትሴፔን የተሳተፉበት፤ እንዲሁም የቀድሞው የካሜሮን ኮኮብ ተጫዋች ሳሙኤል ኢቶና ሌሎችም እንዲሁም አንጋፋ የሀገር ውስጥ ተጫዋቾች ያካተተ የወዳጅነት ጨዋታ አንዱ ማሳያ ነው፡፡

የዘንድሮው ኢትዮጵያ እያስተናገደች የሚገኘው የካፍ ጠቅላላ ጉባዔም በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ የስፖርት እንቅስቃሴን ገፅታ ከመገንባት አንጻር የተለየ ምዕራፍ ከፍቷል። ከዚህም በላይ ኢትዮጵያ ከ53 ዓመት በኋላ ለአራተኛ ጊዜ የአፍሪካ ዋንጫን በ2029 ለማዘጋጀት ለካፍ በይፋ ጥያቄ ያቀረበችበትም ነው።

ለዚህም መንግሥት ከፍተኛ ፍላጎት ብቻ ሳይሆን አቅሙና ቁርጠኝነቱ እንዳለው ማሳየቱ በተለይም ቁልቁለት ጉዞ ላይ የሚገኘውን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ለማነቃቃት ትልቅ ርምጃ ነው። የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት የታየው ቁርጠኝነት ውድድሩን ከማሰናዳት የዘለለ ዘርፈ ብዙ ጥቅም እንዳለው ግልፅ ነው።

ለምሳሌ፣ ውሳኔው ለዓመታት ግንባታቸው ሳይጠናቀቅ ዛሬም ድረስ በተለያዩ ከተሞች ቆመው የሚገኙ ስቴድየሞችን ለማጠናቀቅ ትልቅ እድል ነው። ይህም የካፍን መስፈርት የሚያሟላ አንድ ስቴድየም አጥቶ ባለፉት አራት ዓመታት ገደማ ጨዋታዎቹን በሌሎች ሀገራት ለማድረግ ለተገደደው ብሔራዊ ቡድን ጥያቄም ዘላቂ መልስ የሚሰጥ ይሆናል።

ከዚህ ባሻገር፣ መንግሥትም የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ሲያስብ ከስቴዲየሞቹ ባሻገርም ተተኪ ስፖርተኞች የሚወጡባቸው ትንንሽ ሜዳዎች (Mini stadium) ታሳቢ እንደሚደረጉ እና ውድድርን ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ተጨማሪ የመሠረተ ልማቶች ሥራዎች ላይ ትኩረት እንደሚደረግ አረጋግጧል። ይህም የበርካታ ዓመታት ጥያቄ የሆነውን የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ጥያቄ በመቅረፍ ረገድ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። በየአካባቢው ታዳጊዎችን በብዛት ከማፍራት አኳያም ፋይዳው የጎላ ነው።

እነዚህ እና ሌሎችም ከፍ ያሉ የዝግጅቱን ፋይዳዎች ለተገነዘበ ደግሞ፣ ኢትዮጵያ ከግማሽ ክፍለዘመን በኋላ የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ቆርጣ መነሳቷ ቅንጦት አይደለም። ምክንያቱም ውድድሩን ማዘጋጀት በራሱ ካለው ዘርፈ ብዙ ጥቅም ባሻገር የ«ይቻላል» አስተሳሰብን ለመፍጠር ፋይዳው ቀላል አይደለም። ትውልዱም የአህጉሪቱን ታላቅ ውድድር በሀገሩ የመመልከት እድል ይሰጠዋል።

መንግሥት ውድድሩን ለማስተናገድ ጥያቄ ከማቅረብና ፍላጎቱን ከመግለፅ ባሻገር፣ ይህ ውጥን የተሳካ እንዲሆን በሌሎች መሠረተ ልማቶች ላይ ያሳየውን ፈጣን የአፈፃፀምና ቁርጠኝነት ለዚህ ሁነት በሚያስፈልጉ መሠረተ ልማቶች ላይ በመድገምም የመፈጸም አቅም ክህሎቱን ከሀገር አልፎ ለዓለም ለመግለጥ እድል ይሰጠዋል፡፡

ስቴድየሞችን በሚፈለገው ጥራትና ደረጃ እንዲጠናቀቁና እንከን እንዳይኖርባቸው ከማድረግ አኳያም በዘርፉ እውቀትና ልምድ ካላቸው ባለሙያዎች ጋር በመስራትም ለሌሎች መሰል ሥራዎች የልምድ፣ የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ለመፍጠርም ያስችላል። በጥቅሉም ርምጃው እንደ ሀገር ከፍ ያለ ገጽታን የመገንቢያ፣ ዘርፉንም የማነቃቂያ አቅም የሚፈጥር እንደመሆኑ ለስኬታምነትና ውጤታማነቱ ሁሉም የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የአፍሪካ ዋንጫን ማዘጋጀት እንችላለን

ልዑል ከካምቦሎጆ

ኢትዮጵያ ከተወዳጁ አፍሪካ ዋንጫ ሦስት መሥራች ሀገራት አንዷ ብቻ ሳትሆን ውድድሩን ሦስት ጊዜ በማስተናገድም ታሪክ አላት፡፡ በዚህ ታላቅ መድረክ አንድ ጊዜም ቢሆን ድል ያጣጣመች ሀገርም ናት፡፡ የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ)ን በፕሬዚዳንትነት በመምራት «የአፍሪካ ስፖርት አባት» በሚል የሚታወቁትን ይድነቃቸው ተሰማን የመሳሰሉ በአፍሪካ እግር ኳስ ትልቅ ዐሻራ ያሳረፉ የስፖርት አመራሮችንም አፍርታለች፡፡

በአፍሪካ እግር ኳስ ላይ ትልቅ የታሪክ ዐሻራ ያሳረፈችው የኢትዮጵያ እግር ኳስ በጀመረበት ፈር ቀዳጅ መንገድ ለመቀጠል ተስኗታል፡፡ በተለይም ባለፉት አራት አስርተ ዓመታት ገደማ እግር ኳሳ ቁልቁል እንጂ ሽቅብ መሄድ አቅቶት በመሠረተችው አህጉራዊ የውድድር መድረክ ለመሳተፍ እንኳን ከሦስት አስርተ ዓመታት በላይ ሲፈጅባትና የበዪ ተመልካች ስትሆን ተመልክተናል።

እግር ኳሱ እንዲህ ተስፋው በሰለለበት ወቅት መንግሥት የአህጉሪቱን ትልቅ የስፖርት መድረክ የአፍሪካ ዋንጫን ከአምስት ዓመት በኋላ እኤአ በ2029 ለማዘጋጀት ሰሞኑን ለካፍ በይፋ ጥያቄ ማቅረቡ ይታወቃል።

ካፍ 46ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን ባለፈው ሰኞ አዲስ አበባ ላይ ባደረገበት ወቅትም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) የካፍና የፊፋ ፕሬዚዳንቶችን ጨምሮ በጉባዔው ለመታደም ለመጡ ልዑካን እየተገነባ የሚገኘውን ብሔራዊ ስቴድየም አስጎብኝተዋል። በቤተመንግሥት በነበረው የእራት ግብዣ ላይም ኢትዮጵያ የ2029ኙን የአፍሪካ ዋንጫ የማዘጋጀት አቅም እንዳላት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አረጋግጠዋል። የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ታዬ አፅቀ ሥላሴም በካፍ ጉባዔ ላይ የኢትዮጵያ ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ እንዲፀድቅ ጥሪ አቅርበዋል። ይህንንም ተከትሎ የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሙሴፔ የኢትዮጵያ ጥያቄ ካፍ ባለው የአሠራር ሥርዓት እንደሚታይ ተናግረዋል። የኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫ የማስተናገድ ጥያቄዋን ያቀረበችው በትክክለኛው ጊዜ መሆኑንም ገልፀዋል። ያም ሆኖ ጥያቄው ተቀባይነት ማግኘት አለማግኘቱ በቀጣይ ዓመት ካፍ ሞሮኮ ላይ በሚያደርገው ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ይወሰናል።

ኢትዮጵያ ይህን የአፍሪካ ዋንጫ ለማዘጋጀት ለካፍ ገና በይፋ ጥያቄ ከማቅረቧ አስቀድሞ ብዙዎች አልተዋጠላቸውም። ለዚህም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የካፍን መስፈርት የሚያሟላ ስቴድየም አጥቶ ባለፉት አራት ዓመታት ገደማ ውድድሮችን በሌሎች ሀገራት ለማድረግ መገደዱ አንዱ ምክንያት ነው። ይህ ችግር ወይም ጥያቄ ባልተመለሰበት ሁኔታ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ለማስተናገድ መነሳቷ እንደ እብደት ተቆጥሯል። የማይመስልና የማይቻል ነው ብለው የሚያምኑም ጥቂት አይደሉም።

እርግጥ ነው ትንሹን ችግር መቅረፍ ሳይቻል ሌላ ትልቅ ነገር ለማሳካት ማሰብ ለብዙዎች አሳማኝ ላይሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ ከሃምሳ ሦስት ዓመት በኋላ ትልቁን አህጉራዊ ውድድር ለማሰናዳት ማሰቧ በራሱ ለስፖርቱ ትልቅ ርምጃ ነው። ደግሞም የማይቻልና ቅንጦት የሆነ ህልም አይደለም።

አዎ፣ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ከአምስት ዓመት በኋላ ማስተናገድ ትችላለች። ለዚህም የሚሆን አቅም አላት። መንግሥት በዚህ ደረጃ "ይቻላል" ብሎ በቁርጠኝነት መነሳቱ ዋናው ጉዳይ ነው። ቀጥሎ እንዴት? የሚለውን መጠየቅ ተገቢ ነው። ለዚህ ደግሞ በቂ መልስ አለው።

**አዎ፣ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ከአምስት ዓመት በኋላ ማስተናገድ ትችላለች፡፡ ለዚህም የሚሆን አቅም አላት**

ኢትዮጵያ ባለፉት በርካታ ዓመታት በተለያዩ ከተሞች ግዙፍ ስቴድየሞችን ጀምራ ማጠናቀቅ አልቻለችም። አሁን የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ስትነሳ ግን እነዚህ ጅምር ስቴድየሞች ትልቅ አቅም እንደሚሆኗት አያከራክርም። ይህ ማለት ኢትዮጵያ በቀሪዎቹ ዓመታት የአፍሪካ ዋንጫውን ለማዘጋጀት ከዜሮ አትነሳም። የተጀመሩትን ስቴድየሞች ማጠናቀቅ ነው የሚጠበቅባት። ይህ ደግሞ ከገንዘብም ከጊዜም አኳያ ትልቅ ሚና አለው።

የአፍሪካ ዋንጫን ለማስተናገድ አንድ ሀገር ሁለት 40ሺ፣ ሁለት 20ሺና ሁለት 15ሺ ተመልካች የሚይዙ ስቴድየሞችን እንዲሁም ደረጃቸውን የጠበቁ ከ12 በላይ የልምምድ ሜዳዎችን ማዘጋጀት በቂ ነው። በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በየከተሞቹ የተጀመሩ ስቴድየሞች መስፈርት አሟልተው እንዲጠናቀቁ ከማድረግ ውጭ ተጨማሪ የምትገነባው ትልቅ ፕሮጀክት አይኖርም።

እዚህ ጋር የብዙዎች ጥያቄና ስጋት ስቴድየሞቹ በጥራትና በጊዜ አይጠናቀቁም የሚል ነው። መንግሥት አሁን ካሳየው ቁርጠኝነት ወደ ኋላ ካላለ ልክ እንደኮሪደር ልማቱ ሌት ከቀን በትኩረት ከሠራ ይህም የማይቻል አይደለም። ለዚህም ፕሮጀክቶች ዝም ብሎ በዘፈቀደ መንገድ ሳይሆን በሙያው እውቀቱና ልምዱ ባላቸው ሰዎች እንዲመሩ ማድረግ ይጠበቅበታል። በዚህ ረገድ ከካፍ ጋር በቅርበት መሥራት ያስፈልጋል።

ባለፉት ዓመታት በርካታ ሀገራት የአፍሪካ ዋንጫን የማዘጋጀት እድል አግኝተው ዝግጅታቸው ከጊዜና ከጥራት አኳያ ተፈትሾ መጨረሻ ላይ እድሉን ሲነጠቁ ታዝበናል። የእኛም ተመሳሳይ እጣፋንታ እንዳይገጥመን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። እንዲህ አይነት ችግሮች ቢገጥሙ ለሀገር ኪሳራና አንገት የሚያስደፉ ቢሆንም በሌላ መልኩ ይዞት የሚመጣ መልካም አጋጣሚ እንዳለም ማሰብ ይቻላል።

ለአፍሪካ ዋንጫው ሲባል ቆመው የነበሩ ስቴድየሞች አንድ ርምጃ መጓዛቸው እንዳለ ሆኖ፣ የሚዘጋጁ የመለማመጃ ሜዳዎችና ሌሎች መሠረተ ልማቶች የስፖርት ቤተሰቡን የዓመታት ጥያቄ ይፈታሉ። ይህም በዘላቂነት ከእግር ኳሱ በተጨማሪ በሌሎች ስፖርቶች ታዳጊዎችን በብዛት ለማፍራትና ለማነቃቃት ትልቅ ጥቅም አለው። ሀገራት ውድድሮችን ሲያዘጋጁ ከዝግጅታቸው በኋላ እነዚህን እድሎች እንደሚያገኙ ታሳቢ አድርገውም ነው።

በርካቶቹ ስቴድየሞች የሚገኙባቸው ከተሞች ከአውሮፕላን ማረፊያና ደረጃቸውን ከጠበቁ ሆቴሎች ጋር በተያያዘ ጥያቄ የሚነሳባቸው አይደሉም። ይህም አንድ ትልቅ እድል ነውና የሚናቅ አይደለም።

ካፍ እድሉን ሲሰጥ የመሠረተ ልማት መሟላትን ብቻ እንደማይመለከት ግልፅ ነው። የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት መሠረተ ልማት ከማሟላት አኳያ ኢትዮጵያ አቅሙ እንዳላት ሁሉ በቀሩት ዓመታት በመላ ሀገሪቱ ያለውን ሰላም ማረጋገጥ የግድ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው።

እነዚህን የቤት ሥራዎች ከተወጣን በኋላ አንድ ትልቅ ጥያቄ መመለስም ግድ ይለናል። ይህም ነገሩ ባዶ ቤት ድግስ መጋበዝ እንዳይሆን ተፎካካሪ ብሔራዊ ቡድን የመገንባት ጉዳይ ነው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ የአፍሪካ ዋንጫን ማዘጋጀት ብቻ በቂ አይደለም። ከአንዴም ሦስቴ አዘጋጅተን አይተናል። ብሔራዊ ቡድኑ በተንኮታኮተበት ወቅት እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ ሳይቆርጥ ውጤት እንደሚጠብቅ ይታወቃል። በገዛ ሀገሩ ላይ በሚዘጋጅ የአፍሪካ ዋንጫ ደግሞ ይህ ጉጉቱ ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል መገመት ቀላል ነው። ስለዚህ በቀሪ ዓመታት ዋንጫ የሚያነሳ ወይም ግማሽ ፍፃሜ የሚደርስ ቡድን መገንባት ከባድ ቢሆን እንኳን ቢያንስ እስከ ሩብ ፍፃሜ ጥሩ ፉክክር የሚያደርግ ቡድን የመገንባቱን ነገር የሚመለከታቸው አካላት ትልቅ የቤት ሥራ ሊሆን ይገባል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# “መንግሥት በቻለው መጠን በተለያየ መንገድ የኢትዮጵያ ባንኮችን ለማጠናከር ጥረት አድርጓል”

- የሲዳማ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ
አቶ ታደሰ ሐጢያ

**ምሕረት ሞገስ**

የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያን ለመተግበር የተለያዩ ሕጎች እና አዋጆች እየፀደቁ፤ ማሻሻያውን ከአንድ ወደ ሁለት በማሳደግ እየተተገበረ እና ውጤት እየተገኘበት ነው። በዚህ ላይ የባንኮች ሚና አንደኛው ሲሆን፤ ባንኮች እና የኢኮኖሚ ማሻሻያውን በተመለከተ የሲዳማ ባንክ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ታደሰ ሐጢያን አነጋግረናል። ከባንኩ እንቅስቃሴ ጀምረን ሀገር በቀል ኦኮኖሚው እና ባንኮች መካከል ያለውን ግንኙነት ከዚሁ ጋር ተያይዞ ገበያ መር የውጪ ምንዛሪን እና ሌሎች ጥያቄዎችን አካተን ያካሔድነውን ቃለመጠይቅ በዚህ መልኩ አቅርበንላችኋል። መልካም ንባብ፡-

**አዲስ ዘመን፡- የሲዳማ ባንክ እንቅስቃሴ አሁናዊ ተጨባጭ ሁኔታው ምን ይመስላል?**

**አቶ ታደሰ፡-** እንቅስቃሴውን እንቃኝ ስንል በጣም ሰፊ ነው። ነገር ግን ጠቅለል ባለ መልኩ በሁለት መንገድ ውስጣዊ እና ውጫዊ በሚል ከፋፍለን ማየት እንችላለን። በሀገር ውስጥ ከደንበኞች በቁጠባ እና በተንቀሳቃሽ መልክ ገንዘብ እንሰበስባለን፤ የደንበኛ አገልግሎት ሥራዎችን እንሠራለን። ከብድር አንፃር ደግሞ ኢኮኖሚውን ለመደገፍ ብድር እየሠጠን እንገኛለን። የውጪ ምንዛሪ አቅርቦት ላይም እንሰማራለን።

የውጪ ግንኙነትን በተመለከተ ስድስት ከሚሆኑ የውጪ ሀገር ባንኮች ጋር ግንኙነት አለን። አዲስ እንደመሆናችን መጠን ከስድስት አላለፍንም። ከገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች ጋርም ግንኙነት አለን። በሀገር ውስጥ ካሉ 31 ባንኮች ጋር በአር ቲ ጂ ኤ ሲስተም እርስ በእርስ ተገናኝተን እንሠራለን። ሀገራችን ከምትከተለው ዲጂታላይዜሽን ሲስተም አንፃር ባንኩን ዲጂታላይዝድ ለማድረግ ስላሰብን በቶሎ ወደ ቴክኖሎጂ ገብተናል። ስለዚህ ኤቲ ኤም እና ከባንክ ወደ ባንክ ማዘዋወር እንዲሁም ከቴሌ ጋር ግንኙነት ፈጥረን እየሠራን ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሲዳማ ባንክ በሐዋሳ ለቤት ገንቢዎች ያዘጋጀው ብድር ነበር። ምን ላይ ደረሰ?**

**አቶ ታደሰ፡-** የክልሉ መንግሥት በሁለት መልኩ ቤት እንዲገነባ ፈቅዶ ነበር። አንደኛው በማህበር ተደራጅተው ይመጣሉ። ቆጥበው ያስቀምጣሉ፤በተጨማሪ በጋራ መኖሪያ ቤት መልክ የሚቆጥቡም አሉ። እኛ ለሁለቱም የገንዘብ አቅርቦት እንሠጣለን። የክልሉ የማህበራት ማደራጃ ቢሮ ያደራጅና በባንኩ የሒሳብ ቁጥር እንዲከፈት ያደርጋል። የተጠየቁት 50 በመቶ ሲሞላ የከተማ አስተዳደሩ ለእያንዳንዳቸው መሬት ይሠጣቸዋል። እነሱ ዲዛይን አውጥተው ቤቱን የሚገነቡበትን ሁኔታ በሚመለከት ሂደቱን ጨርሰው ሲያጠናቅቁ ወደ ባንካችን ይመጣሉ። እኛ ደግሞ ግንባታውን ማጠናቀቂያ ብድር እንሰጣቸዋለን።

የጋራ መኖሪያ ቤቱን በተመለከተም ባንኩ ለከተማ አስተዳደሩ ብድር ይሰጣል። የከተማ አስተዳደሩ ብድር ይወስድና የጋራ መኖሪያ ቤት ይገነባል። በዕጣ ለሚያስተላልፍላቸው ሲያስተላልፍ እኛ ደግሞ ብድር ለገዢዎቹ እንሰጣለን። ገዢዎቹ ዕዳውን ሲከፍሉ የከተማ አስተዳደሩ ብድር ይዘጋል ማለት ነው። በሁሉም ሞዳሊቲ ባለፈው ወደ 35 ማህበራት መሬት ወስደው የቤት ዲዛይን እየጨረሱ ነው። እርሱ ብቻ አይደለም፤ ከዋጋ ንረት አንፃር መጀመሪያ የተገመተው እና አሁን ያለው እኩል አይደለም። ስለዚህ መቆጠብ አለባችሁ እየተባሉ ስለሆነ አሁን ላይ መቆጠብ ጀምረዋል። ያንን ጨርሰው ሲመጡ እኛ ደግሞ የብድር ሁኔታን እናመቻቻለን።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ካፒታላችሁ ምን ያህል ነው?**

**አቶ ታደሰ፡-** ካፒታል የሚገለፀው በብዙ መልኩ ነው። መጠባበቂያ ካፒታል፣ ጠቅላላ ካፒታል የሚባሉ አሉ። ጠቅላላ ካፒታል ከተባለ ከአንድ ቢሊዮን በላይ ነው። ሃብታችን ደግሞ 2 ነጥብ 7 ቢሊዮን አካባቢ ነው። ሃብት የሚባለው የደንበኞች ቁጠባ የተሠሩ ቁጥሮች ይደመራሉ። የባንኩ ቋሚ ሃብቶችም አሉ። እነዛ ሁሉ ተደማምረው ነው። ያበደርነው ደግሞ 1 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር ነው። ስለዚህ የሚለካው ሃብታችን ተደርቦ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- ተግባራዊ የተደረገው ገበያ መር የውጪ ምንዛሪ ሥርዓት ለባንኮች ያለው ጥቅም እና ጉዳትን በተመለከተ ቢያብራሩልን ?**

**አቶ ታደሰ፡-** ገበያ መር የሆነ የውጪ ምንዛሪ ተመን በጣም ትልቅ ዕምርታን ያሳየ ነው። እኛ እንደውም አዲስ ባንክ በመሆናችን ብዙ የውጪ ምንዛሪ ለማግኘት ጠቅሞናል። የውጪ ምንዛሪ ግኝታችን ከ60 በመቶ በላይ ጭማሪ አሳይቷል። ምክንያቱም ወደ ውጪ የሚልኩ ባለሃብቶች ያገኙትን ዶላር መጠቀም እና ማስቀመጥ ይፈልጋሉ። ከዛ አንፃር የተለያዩ ደንበኞች የውጪ ምንዛሪ ባንክ ሲያስቀምጡ በአንድም በሌላም መንገድ ሌሎች ዶላሩን የሚያገኙበት ዕድል ይኖራል።

ሌላው ደንበኞች ያመጡትን የውጪ ምንዛሪ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ተስማምተው ለባንክ መሸጥ እና ከባንክ መግዛት ይችላሉ። አንድ ለአንድ መደራደር ባይቻልም፤ የዕለቱን የመግዣ እና የመሸጫ ምንዛሪያችንን ይፋ እናደርጋለን። የውጪ ሀገር ገንዘብ ያላቸው ደንበኞች በመረጡት ባንክ ሔደው ይሸጣሉ። ይህ ለእኛም ጠቅሞናል።

ውጪ ያሉ ዘመዶቻችንም ገንዘብ በዛ መልኩ እያስተላለፉ ነው። የእኛ ገንዘብ አስተላላፊ ወኪሎች (ኤጀንቶች) ግን ውስን ናቸው። ይቀረናል እንጂ የመንግሥት አካሔድ በጣም እየረዳን ነው። ያለንን የውጪ ሀገር ገንዘብ ስልክ እየደወልን ‹‹ከውጪ የምታስገቡት ነገር ካለ መጥታችሁ መውሰድ ትችላላችሁ፡፡›› እያልን እስከ መደወል ደርሰናል። ስለዚህ ለእኛም ለተገልጋዩም ትልቅ ለውጥ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ አሁን ላይ የውጭ ምንዛሪ የሚፈልግ በሙሉ እያገኘ ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ታደሰ፡-** መንግሥት የውጪ ምንዛሪን ፈሰስ አድርጓል። ይህ የውጪ ምንዛሪው ገበያ መር ሲሆን፤ የተለያዩ ባንኮች እንዲገዙ ለማገዝ የተለቀቀ ነው። ወደ ውጪ የሚላከው እና ከውጪ ሀገር የሚላከውም ገንዘብ ስለጨመረ ማግኘት እየተቻለ ነው። በባንክ በኩል የውጪ ምንዛሪውን ይዞ መቆየት አክሳሪ ነው። ምክንያቱም ባንኩ ራሱ ትርፍ የሚያገኘው ደንበኞች ባለው ገንዘብ ሲጠቀሙ ነው። ለምሳሌ ሊዝ ሲከፈል የሚከፈሉ ክፍያዎች አሉ። የአገልግሎት ክፍያዎች ለባንኩ እንደገቢ ናቸው። አስር ሚሊዮን ዶላር አካውንቴ ውስጥ አለ ከማለት ይልቅ አንድ ሚሊዮን ዶላር ብቻ ተቀምጦ፤ ሌላው ለገበያ ቢውል ይሻላል።

የሀገር ውስጥ ገንዘብም ቢሆን ተመሳሳይ ነው። በቢሊዮን ቁጥር የገባ ብር መንቀሳቀስ አለበት። አዲሱ ፖሊሲ ብዙ የውጭ ምንዛሪ እንዲገባ አድርጓል። በተመሳሳይ መልኩ ለደንበኞች ለመስጠትም ጥሩ ዕድል ፈጥሯል። ከዚህ በፊት የውጪ ምንዛሪ እጥረት አለ ስለሚባል አንዳንድ ባንኮች አካባቢ የመልካም አስተዳደር ችግር እየተፈጠረ ነው ይባል ነበር። አስር ሰው ጠይቆ ለአንዱ ብቻ ሲሰጥ የመልካም አስተዳደር ችግር የመፈጠር ዕድሉ የሰፋ ነው። አሁን ግን የውጪ ምንዛሪ እጥረት ስለሌለ ችግሩን ማስወገድ ችለናል ብለን እናስባለን።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ባንኮች ገንዘብ የሚሰበስቡት ከብዙ ሕዝብ ቢሆንም፤ የሚያበድሩት ለጥቂት ሰዎች ነው። በተለይ ድሃውን እየጠቀሙት አለመሆኑ ይታወቃል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ታደሰ፡-** በእርግጥ የቆጣቢ እና የተበዳሪ ቁጥር ሙሉ ለሙሉ አይገናኝም። ምናልባትም አንድ ሰው በአራት እና በአምስት ባንኮች በተለያየ የሒሳብ ቁጥር ሊቆጥብ ይችላል። ያ ሁሉ ሲቆጠር የሁሉም ባንኮች



ፎቶ፡- ሐዲስ አብርሃ

**ከዚህ በፊት የውጪ ምንዛሪ እጥረት አለ ስለሚባል አንዳንድ ባንኮች አካባቢ የመልካም አስተዳደር ችግር እየተፈጠረ ነው ይባል ነበር። አስር ሰው ጠይቆ ለአንዱ ብቻ ሲሰጥ የመልካም አስተዳደር ችግር የመፈጠር ዕድሉ የሰፋ ነው። አሁን ግን የውጪ ምንዛሪ እጥረት ስለሌለ ችግሩን ማስወገድ ችለናል**

ተደማምሮ የቆጣቢ ቁጥር ከኢትዮጵያ ሕዝብ በላይ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ከባንኮች 93 ሺህ አካባቢ ብቻ ተበዳሪ አለ። ያን ያህል ሕዝብ ቆጥቦ ጥቂቱ ይወስዳል። በእርግጥ ገንዘቡ ተሰብስቦ የሚሰጠው ለጥቂቶች ነው።

ሲዳማ ባንክ አነሳሱ አነስተኛ የቁጠባ እና ብድር ተቋም ሆኖ የተቋቋመ ነው። ስለዚህ የቀረፅነው መንገድም ያንኑ ተከትሎ የሚሄድ ነው። ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው መሠረት አንድ ባንክ የካፒታሉን 25 በመቶ ድረስ ማበደር ይችላል። እኛ ግን ያደረግነው ጥቂቶች ብቻ ወስደው እንዳይጨርሱ የምናበድረው አስራ አምስት በመቶ ብቻ ነው። ያ ያለችውን ሃብት ለብዙዎች እንድትከፋፈል ይጠቅመናል። ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተር ፕራይዞች ራሱን የቻለ የባንኩ ዲፓርትመንት አለ። በዚህ ዲፓርትመንት ወደ አምስት መቶ ሚሊዮን ብር ትንንሽ ብድሮች ይሰጣል። ባለፈው ዓመት ለጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት ስናበድር ነበር፡፡

እንግዲህ ድህነት በንፅፅር ነው። አንድ ሚሊዮንም፤ አምስት ሚሊዮንም የሚበደር አለ። እኛ ከአንድ ሚሊዮን ብር በታችም እናበድራለን። የትኛውም ባንክ ሃምሳ ሺህ እና መቶ ሺህ አያበድርም። እኛ ግን እናበድራለን። ነገር ግን ባንኮች አነስተኛ ብድር የማይሰጡት ለምንድን ነው? የሚለውንም ማወቅ ያስፈልጋል። ምናልባት የአሁኑን ዲጂታል ሥራ ላይ በማዋል ለብዙሃን ብድር መስጠት ይቻላል። ነገር ግን አሁንም ማግኘት የሚችሉት ዘመናዊዎቹ ዲጂታሉን የሚጠቀሙት ብቻ ናቸው፡፡

ባንኮች ብድር የማይሰጡት ለምንድን ነው ተብሎ ሲጠየቅ፤ መልሱ ተበዳሪው አንድ ጊዜ ብድር ከወሰደ፤ የታወቀ እና መገኘት የሚችል መሆን አለበት። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ግን አንድ ጊዜ ከተበደረ በኋላ ማግኘት አይቻልም። እኛ እያበደርን ያለነው የሕዝብን ገንዘብ ነው። አንዱ ያስቀመጠውን ለሌላ ስናበድር፤ የግድ በሌላ ጊዜ ብር ያስቀመጠው ሰው ገንዘቡን ሲጠይቅ ማግኘት አለበት። ተበድሮ የሚጠፋ ከሆን

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

# ወቅታዊ

## “መንግሥት በቻለው መጠን በተለያየ...

ከገጽ 6 የዞረ



ያንን መመለስ አይቻልም። ስለዚህ ብድር ስንሰጥ ብሩ እንደሚመለስ እርግጠኛ መሆን አለብን።

መንግሥት በቅርቡ እየዘረጋ ያለው የብሔራዊ መታወቂያ ሥርዓት ለባንኮች በጣም ትልቅ ውጤት ሊያመጣ የሚችል ሥርዓት ነው። ምክንያቱም ዲጂታል መታወቂያ ከተለመደ የትም ቦታ ቁጥር ሲገባ ግለሰቡ ማን እንደሆነ ይታወቃል። ይህ በኋላ ሕግ ሆኖ ሲወጣ ዲጂታል መታወቂያ የሌለው ሰው መበደር አይችልም ይባላል። የትም ቦታ ሔዶ መታወቂያ ማውጣት አይችልም። ስም ቀይሬ መታወቂያ አወጣለሁ ቢል አሻራ ይይዘዋል። በዛ ጊዜ ተበዳሪን ማግኘት ይቻላል።

እስከዛም ቢሆን እኛ የድሃውን ማህበረሰብ ለማገዝ ከተለያዩ ተቋማት ጋር አብረን እንሰራለን። ሴቶችን የምንደግፍበት ሁኔታ አለ። ከድጋፍ አድራጊ ድርጅቶች ጋር እንሰራለን። ለድሃው ማህበረሰብ ተመጣጣኝ የሃብት ክፍፍል እንዲኖር የተቻለንን እናደርጋለን። 100 ሚሊዮን ብር ለአንድ ግለሰብ አናበድርም፤ የምናበድረው አነስተኛ ብድሮችን ነው። ይህ የብድር አቅርቦትን ለማዳረስ በሚል የመጣ ሃሳብ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በአጠቃላይ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያውን በተመለከተስ ምን ይላሉ?**

**አቶ ታደሰ፡-** ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያውን በማየት እኛ ደግሞ ከዛ ላይ ቆርሰን የምንፈልገው ምንድን ነው? በሚል እያየን ነው። እያንዳንዱ ዘርፍ የየራሱን ቆርሶ ይወስዳል። የፋይናንስ ዘርፉ የሌማት ትሩፋቶች ላይ ለምሳሌ የአሳ ሃብት፣ የዶሮ እርባታ ላይ በቡድን እየተደራጁ አንዱ ለሌላው ዋስ እንዲሆን በማድረግ ብድር እየሰጠን ነው። ሌላኛው ደግሞ ወጣቶችን የሚያደራጁ ፅህፈት ቤቶች አሉ። እነርሱ ለተደራጁት ኃላፊነት ይሰጡዋቸዋል፤ ይከታተሉዋቸዋል። ሙያዊ ድጋፍ ይሰጧቸዋል። ለእነርሱ የፋይናንሺያል አቅርቦት አለን።

በባንኩ በኩል ለወጣቶች የማማከር ሥራም ይሠራል። ለምሳሌ የፋይናንስ ኦፕሬሽን ዲፓርትመንት ውስጥ ያሉ ባለሙያዎቻችን ሙያዊ ድጋፍ ይሰጧቸዋል። ሀገር በቀል ኢኮኖሚው የሚያበረታታው የፈጠራ ባለሙያዎችን ነው። ጥገኛ ሆነን ብቻ ሳይሆን ራሳችን ፈጥረን መስራት እንችላለን። ስለዚህ በዚህ መልኩ ድጋፍ እያደረግን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ወደፊት የውጪ ባንኮች እንደሚገቡ እየተነገረ ነው። የሀገር ውስጥ ባንኮች ምን ያህል አቅም አላችሁ? ምን ያህል ተዘጋጅታችኋል?**

**አቶ ታደሰ፡-** ለረዥም ጊዜ ኢትዮጵያ ለውጪ ባንኮች በሯን ዝግ አድርጋ ኖራለች። በዓለም ደረጃ ተገዳዳሪ ኢኮኖሚ ለመገንባት ከተፈለገ የግድ የዓለም ማህበረሰብን ሳያቅፉ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግሥት ለዚህ ተዘጋጅቻለሁ እያለ ነው። ደግሞም ብዙ የማሻሻያ ሥራዎች ተሠርተዋል። ባንኮች እንዲጠናከሩ ተደርጓል። ካፒታላቸውን እንዲያሳድጉ ሥራዎች ተሠርተዋል። ነገር ግን ከደርግ መንግሥት በኋላ የመጀመሪያው የግል ባንክ አዋሽ ባንክ መነሻው 25 ሚሊዮን ብቻ ነበር። አሁን ግን ካፒታሉ በቢሊዮን የሚቆጠር ነው። ልክ እንደአዋሽ ሁሉ መንግሥት በተቻለው መንገድ የግል ባንኮችን እያጠናከረ ነው።

አንድ ባንክ ተወዳዳሪ መሆን የሚችለው በካፒታሉ እና በቴክኖሎጂ ነው። የእኛን ጨምሮ ባንኮች ቴክኖሎጂ መር ሥራ እየሠሩ ነው። ይህ ማለት ግን ሲመጡ መቋቋም ይችላሉ ማለት አይደለም። ስለዚህ መጣመር ያስፈልጋል። መጣመር ሲባል መተባበር ነው። ከሌላው ጋር ተባብሮ መሥራት ማለት ነው። ምናልባት አንዳንዴ በተቃራኒው የሚወራው የእኔነት ስሜት የሚባል ነገር አለ። ነገር ግን እውነታውን ማወቅ ያስፈልጋል። ምንጊዜም ቢሆን ባለገንዘቡ የሚፈልገው ከፍተኛ ገንዘብ የሚገኝበትን ባንክ ነው። ከዛ ውጪ የሚወራውን ወሬ አይፈልግም።

ባለድርሻው የኔ ባንክ የሚለው ለእርሱ ጥሩ ትርፍ የሚያመጣለትን ነው። ሲዳማ ባንክ ትልቅ ትርፍ ማግኘት ባይችልና ከሌላ ባንክ ጋር ተባብሮ ከፍተኛ ገንዘብ ቢያገኝ የአክሲኦን ድርሻ ባለቤቱ ከፍተኛ ትርፉ ያስደስተዋል። ደንበኛ 100 ሺህ ድርሻ ገዝቶ ምን ያህል ትርፍ እንደሚያገኝ ያስባል እንጂ ሌላ ምንም አያስብም። አንዳንድ ሰዎች ግን ጉዳዩን በግድ ፖለቲካ ለማድረግ ይሞክራሉ።

ባንኩን ማጠናከር እና ተወዳዳሪ ማድረግን በተመለከተ በእኛ በኩል የአምስት እና የአስር ዓመት ስትራቴጂ ቀርፀን ጨርሰናል። አማራጮችን አስቀምጠናል። አንደኛው ብሔራዊ ባንክ ባስቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካፒታላችንን ከአምስት ቢሊዮን በላይ ማድረስ ነው። ሁለተኛው ደግሞ አምስት ቢሊዮን ብቻ ሆኖም ላንቀጥል እንችላለን፤ ምክንያቱም ትሬዠሪው አምስት ቢሊዮን ብር ወደ ዶላር ሲቀየር በጣም ትንሽ ነው። ስለዚህ የውጪ ባንኮች እንዳያሸንፉን ከሌላ ባንክ ጋር ልንተባበርም እንችላለን። የግድ ከሌላው ጋር መተባበር ሊገባ ይችላል። ከእኛም ያነሰ ሊመጣ ይችላል። በራሳችን ውስጥ እናካትተዋለን።

እኛ እንደሙያተኛ ለባለድርሻው ጥቅም የሚያመጡ ነገሮች ላይ ጠንክረን እንሠራለን። የባንኩን ካፒታል እና ትርፍ በማሳደግ የሰለጠነ የሰው ኃይልን በመጠቀም በጣም ምርጥ ቴክኖሎጂን ሥራ ላይ በማዋል ባንኩን ለማሳደግ ጥረት እያደረግን ነው። ቴክኖጂውን የበለጠ በጥራት እና በስፋት ለመጠቀም በቅርብ ጊዜም ጨረታ ወጥቷል። ስለዚህ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ እና የሰለጠነ የሰው ኃይል በመጠቀም ለውጡን ለመቀበል ጥረት እያደረግን ነው። መንግሥት ደግሞ በቻለው አቅም ባንኮችን መደገፉ የሚካድ አይደለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ባንኮች አካባቢ በዋናነት ሲጠቀሱ የሚችሉ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?**

**አቶ ታደሰ፡-** መንግሥት በቻለው ሁሉ በተለያየ መልኩ የኢትዮጵያ ባንኮችን ለማጠናከር ጥረት እያደረገ ነው። ለምሳሌ የውጪ ምንዛሪን ለባንኮቹ ሰጥቷል። ይህ ራሱ ቀላል ድጋፍ አይደለም። ሌላው የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማቶችን ለማሟላት ትልቅ ድጋፍ እያደረገ ነው። ለምሳሌ ውልና ማስረጃ የሰጠውን ውክልና በቀላሉ በቴክኖሎጂ ማረጋገጥ የምንችልበት ሲስተም ተዘርግቷል። ይሔ ቀላል አይደለም። የእኛ ደንበኛ የመንግሥትን ግብር በቀጥታ በእኛ ባንክ በኩል ይከፍላል። ይህ ለእኛ ትልቅ ድጋፍ ነው። ነገር ግን እንደተግዳሮት ሆነው የሚነሱት አንዳንድ ጊዜ መንግሥት ሳይፈልግ ፈተና ሆነው የሚመጡ ነገሮች ናቸው። ለምሳሌ የፀጥታ ችግር መንግሥት ፈልጎት የሚመጣ አይደለም። ባንክ በራሱ በጣም ጥንቃቄ እና ጥበቃን የሚሻ ተቋም ነው። ያገኘውን ገንዘብ እንዴት ላስጠብቅ ማለት ብቻ ሳይሆን እንዴት ላሳድግ እያለ ሲያስብ፤ የፀጥታ ችግሮች ከባድ ፈተና ይፈጥራሉ።

ሌላው የውጪ ዜጋ የሲዳማ ባንክን ድርሻ (ሼር) መግዛት እንዲችል ተፈቅዶለታል። ነገር ግን የፀጥታ ችግር ካለ አይተማመንም። መንግሥት የሚሰራው በተለይ የሀገር ግንባታ ላይ ማተኮሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ፀጥታው ላይ ያለው ችግር መፈታት አለበት። ሌላው የውጭ ምንዛሪ ላይ ሰዎች እያመጡ ያሉበት ሁኔታን የበለጠ ማሳደግ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ትንንሽ አንድ መቶ ወይም ሁለት መቶ ዶላር ሊልኩ ይችላሉ። ያ ወደ ሆነ የኢንቨስትመንት ደረጃ እንዲመጣ የማስተዋወቅ ሥራ መሠራት አለበት። ለምሳሌ አሁን ይፋ የተደረገው ዩናይትድ አፍ ኢቲ የሚለው ብዙ ዳያስፖራዎች እዛው ሆነው የአካውንት ቁጥር ከፍተዋል። በቪዲዮ በፎቶ እዛው ሆነው መረጃቸውን ይልካሉ። በኤሌክትሮኒክስ ይፈርማሉ። ስለዚህ ስርዓቱ ስለተዘረጋ ወዲያውን ብር መላክ ይችላሉ። ገንዘብ ማስቀመጥም ይችላሉ፤ እዚህ ላይ ከፍተኛ የማስተዋወቅ ሥራ መሠራት አለበት።

**አዲስ ዘመን፡- የዋጋ ንረት ባንኮች ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖ ምን ያህል ነው?**

**አቶ ታደሰ፡-** ፈተና ተብለው ከሚጠሩ ጉዳዮች መካከል አንደኛው የዋጋ ንረት ነው። የገንዘብ የመግዛት አቅም ማነስ ነው። የዋጋ ንረት ሲኖር ቆጣቢዎች ያስቀመጡትን ገንዘብ በብዛት የሚያወጡበት ሁኔታ አለ። ዛሬ በስንት መከራ የተቀመጠ ገንዘብ ይወጣል። ምክንያቱም ደንበኛው ለሚያወጣው ወጪ ገንዘቡ አይበቃም። በእኔ እምነት ለዚህ ትልቁ መፍትሔ አቅርቦትን ማስፋት ነው። የሚፈለገው ነገር በገፍ ከተገኘ ዋጋ መቀነሱ አይቀርም። ለምሳሌ የቻይና ኢኮኖሚ በምዕራቡ ዓለም ሳይቀር ፈተና የሆነው አቅርቦት ስላበዙ ነው። በቻይና በጣም ብዙ ፋብሪካዎች ያመርታ። ቻይናዎች በጣም አቅርቦት ላይ በስፋት ይሠራሉ። አውሮፓዎች ደግሞ በጥራት ጥቂት ምርት ያመርታሉ። ስለዚህ እኛም በግብርና በኢንዱስትሪው አቅርቦቱን ማብዛት ያስፈልገናል። አቅርቦት ከበዛ ባንኮችም ገንዘብ መሰብሰብ ይችላሉ።

በእርግጥ የዋጋ ንረትም ቢኖር ገንዘቡም ወጥቶ ወደ ባንክ ሊገባ ይችላል። ነገር ግን አንዳንዴ አይገባም። ብሔራዊ ባንክ የሚያውቀው ገንዘብ እና በአጠቃላይ ያለው ገንዘብ የተለያየ ነው። ማለትም ብሔራዊ ባንክ አትሞ ያወጣው ብር ባንኮች ውስጥ የለም። አንዳንዴ ባንኮች አካባቢ ያለው እጥረት ባንክ ሔጄ ላላገኝ እችላለሁ በሚል ስጋት ሰዎች ብራቸውን ወደ ባንክ ላያስገቡ ይችላሉ። ከዚህ በላይ ማውጣት አይቻልም ሲባል ሰዎች ገንዘባቸውን ባንክ ማስቀመጥ ይቀንሳሉ። ስለዚህ የሚሻለው መልቀቅ ነው። ሰዎች ባንኮች ላይ እንዲተማመኑ መሥራት ያስፈልጋል። አንድ ሚሊዮን ሁለት ሚሊዮን ማውጣት ከቻሉ ለማስገባት አይጨነቅም።

በሌላ በኩል ምርታማነት ላይ በደንብ ከተሠራ አቅርቦቱ ሲጨምር የዋጋ ግሽበትን መቆጣጠር ይቻላል። በዛ ላይ መንግሥት አሁን ጥሩ እየሔደ ነው። አሁን እየተቀመጠ ያለው ፖሊሲ ጥሩ እየተሠራበት ጥሩ ውጤት እያስገኘ ነው። አንዳንዴ ባንኮች ቢዝነሱ ከሚያስፈልገው በላይ ገንዘብ የመልቀቅ ዝንባሌ ይታይባቸዋል። ዋስትና በማየት ብቻ ሲለቁ፤ ችግር ነው። ስለዚህ የሚለቁት ብድር እንዲወሰን በማድረግ ራሱ የራሱ በጎ ተፅዕኖ ይኖረዋል። እንዲህ ሲወሰን ትንንሽ ብሮች ይወጣሉ። ትልልቅ ብድሮች ሲሰጡ ተጠቃሚዎቹ የተወሰኑ ብቻ ናቸው። አነስተኛ ብድሮች ሲሰጡ ግን ብዙ ሰው ጋር ይዳረሳል። ብዙዎች ያመርታሉ። የማምረት አቅም ሲጨምር ደግሞ ምርታማነት ይጨምራል።

**አዲስ ዘመን፡- ባንኮች በጨረታ ላይ ተስማምተው የሚገቡበት እና አሻጥር የሚሰራበት ሁኔታ ስለመኖሩ ይነገራል። እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ታደሰ፡-** በፊት ነበር አሁን ግን ጨረታ የለም። አሁን ባንኮች በጠዋት የውጪ ምንዛሪ ባንኩ የሚሸጥበትን እና የሚገዛበትን መጠን ወስነው በየራሳቸው ይፋ ያደርጋል። እያንዳንዱን የማነጋገር ሁኔታ የለም። ነገር ግን አንድ ዶላር ያለው ሰው ለመሸጥ ብዙ ዶላር ይዞ ከመጣ መስማማት እንዲቻል ዕድሉ አለ። ይህ ሌላ ቦታ እንዳይሔድ ነው፤ ሌላ ነገር የለውም። 100 ዶላር ከሚያመጣ ሰው ጋር ግን ድርድር ውስጥ አይገባም። ነገር ግን አንድ እና ሁለት ሚሊዮን የውጪ ምንዛሪ አመጣለሁ ወስንልኝ የሚል ከመጣ በመወሰን እዚሁ እንዲመነዝር ይደረጋል። ከዛ ውጪ ባንኮች አሁን ላይ ደፍረው እርስ በእርስ የሚደራደሩበት ሁኔታ የለም። ነገር ግን አንዱ ባንክ ለሌላው ባንክ የሚሸጥበት ዕድል ተፈቅዷል።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ ዕድሉን እንስጥዎት?**

**አቶ ታደሰ፡-** አዎ! በመንግሥት ደረጃ እየተቀረፁ እና እየተተገበሩ ያሉ የልማት ፕሮግራሞች ለእኛ ትልቅ መነቃቂያ የፈጠሩ ናቸው። በተለይ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ወደ ውስጥ ራሳችንን ጠለቅ አድርገን ስናይ የተደረገው የለውጥ አካሔድ ብዙ አቅሞችን እያወጣ የመጣ ከመሆኑ አንፃር በጣም ሊበረታታ የሚገባ ጉዳይ ነው። ሌላው ተቋማት የማስፈፀም አቅማቸው በቴክኖሎጂም ሆነ በሰው ኃይል እንዲያድግ እየተደረገ መሆኑ፤ ለእኛ ትልቅ አቅም ሆኖናል። ምክንያቱም አገልግሎቶች ግልፅ እና ውጤታማ እየሆኑ ነው። አዲስ አበባም ሆነ ሌሎች ከተሞች ላይ የሚገጥሙን ችግሮች እየተቃለሉ ናቸው። ነገር ግን ይኸው በጣም በተሻሻለ መልኩ መቀጠል አለበት፡፡

ሌላው ከውጪ ምንዛሪ ጋር ያለው ሁኔታ መንግሥት አጠናክሮ ቢቀጥል የበለጠ አደጋ እንዳይመጣ ቶሎ ለመከላከል ያግዛል። አደጋ ውስጥ ከመግባት ይልቅ ቀድሞ መከላከል ግድ ይላል። ምናልባት ኑሮ ውድነቱን የውጪ ምንዛሪው ገበያ መር መሆኑን ተከትሎ የመጣ ለማስመሰል የሚደረገው ሙከራ ሐሰት ነው። እንደውም አቅርቦቱ እየጨመረ ስላለ ለምሳሌ ፒኤልሲ ሲከፈቱ የነበሩ ክፍያዎች በመግዣና በመሸጫ ልዩነት እንድንወስድ ስለተደረገ ባንኮች የሚጭኑት የአገልግሎት ክፍያ በጣም ትንሽ ሆኗል። እየመጡ ያሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች የውጪ ባንኮች መግባትን ጨምሮ የምናየው በመልካም ነው። አቅምን ያጠናክራል። እንቅልፍ እንቅልፍ ያለንን እንድንነቃ ያደርገናል። ስለዚህ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ባይ ነኝ። በተረፈ ፈጣሪ ሀገራችንን ይባርክ።

**አዲስ ዘመን፡- አሜን ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም እጅግ እናመሰግናለን፡፡**

**አቶ ታደሰ፡-** እኔም በጣም አመሠግናለሁ፡፡

# በዞኑ በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች የታገዘ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እየተካሄደ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በማዕከላዊ ጎንደር ዞን በአዳዲስ የግብርና አሠራሮችና ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ 30 ሺህ ሄክታር በሚጠጋ የእርሻ መሬት ላይ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሥራ መጀመሩን የዞኑ ግብርና መምሪያ አስታወቀ፡፡

በመምሪያው የአትክልት ፍራፍሬና መስኖ አጠቃቀም ቡድን መሪ አቶ ሃውልቱ ታደሰ እንዳሉት፤ በምግብ ሰብል ራስን ለመቻል የተቀመጠውን የስንዴ ልማት መርሃ ግብር ለማሳካት እየተሠራ ነው፡፡

ለዚህም በያዝነው የበጋ ወራት 29 ሺህ 748 ሄክታር መሬት ለመስኖ ስንዴ ልማት መዘጋጀቱን ጠቅሰው፤ እስካሁን በተከናወነ ጥረትም 3 ሺህ 652 ሄክታር መሬት ታርሶ ለዘር ሥራ መዘጋጀቱን ገልጸዋል፡፡

በመስኖ ስንዴ ልማቱ ከ60 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች የሚሳተፉ ሲሆን በመስኖ ልማት አሠራርና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም በየደረጃው ሥልጠና እንዲያገኙ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

ለመስኖ ልማቱ የሚያገለግሉ 92 አነስተኛና መካከለኛ የመስኖ አውታሮች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ 23 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የመስኖ ካናል ጠረጋ በማከናወን ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ መቻሉን ገልፀዋል፡፡

እንዲሁም ለመስኖ ልማቱ የሚውሉ አራት ሺህ ነባር የውሃ መሳቢያ ሞተሮችን አርሶ አደሮቹ ማዘጋጀታቸውን ጠቁመው፤ 249 አዳዲስ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች መቅረባቸውን አመልክተዋል፡፡

ባለፈው ዓመት በበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ በሄክታር 32 ኩንታል ምርት የተገኘ ሲሆን ዘንድሮ የተሻለ ቴክኖሎጂንና ግብዓትን በመጠቀም በሄክታር ወደ 40 ኩንታል ለማሳደግ ታቅዶ እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

ለበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ ከ50 ሺህ ኩንታል በላይ የአፈር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሮች ለማቅረብ መታቀዱን ጠቁመው፤ ከሚለማው መሬትም አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የስንዴ ምርት ይጠበቃል፡፡

በዘንድሮ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ግማሽ ሄክታር መሬት አርሰው ለዘር ሥራ ማዘጋጀታቸውን የገለጹት ደግሞ በምዕራብ ደንቢያ ወረዳ ነዋሪ አርሶ አደር እሸቴ ማሩ ናቸው፡፡

በአካባቢያቸው የተገነባውን የመስኖ ካናል በመጠቀም በስንዴ ከሚያለሙት መሬት 20 ኩንታል ምርት እንደሚጠብቁ ተናግረዋል፡፡

በምስራቅ ደንቢያ ወረዳ ነዋሪ አርሶ አደር ጋሻው ሲሳይ በበኩላቸው፤ በኩታ ገጠም እርሻ አንድ ሄክታር ማሳቸውን በበጋ መስኖ ስንዴ ለማልማት መሬት የማለስለስ ዝግጅት ማጠናቀቃቸውን አስረድተዋል፡፡

ከሚያለሙት መሬትም 40 ኩንታል የስንዴ ምርት እንደሚጠብቁ ገልጸው፤ ያመረቱትን ምርት በአካባቢያቸው ለሚገኙ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበራት በገበያ ዋጋ በማቅረብ ተጠቃሚ ለመሆን እንዳቀዱም ገልፀዋል፡፡

በዞኑ በዘንድሮ የበጋ መስኖ ልማት 40 ሺህ ሄክታር በሚጠጋ መሬት ላይ በሁለት ዙር አትክልትና ፍራፍሬን ጨምሮ የምግብ ሰብሎችን ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን ከመምሪያው የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

# "ብሪክስ…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ኢኮኖሚዎችንና ከፍተኛ የዕድገት አቅሞችን በመጠቀም ሕዝቦቻችን ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ማስመዝገብ አለብን ብለዋል፡፡

በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ እድገት ውስጥ ትብብርን ማጎልበትም አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለአዲሱ ልማት ባንክ የአባልነት ጥያቄም በፍጥነት እንዲጤንና አማራጭ የፋይናንስ ልዩነትን ለማሻሻልና ለመሠረተ ልማት ፕሮጀክቶች እንደሚረዳ ጠቁመዋል።

ብሪክስ ለፍትሃዊና ውክልና ያለው የባለብዙ ወገንነት ድጋፍን እንደሚያበረታታ በመግለጽ፣ የታዳጊ ሀገራትን ስጋት የሚፈታ ማሻሻያና ድምፃቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲሰማ ማድረግ እንደሚቻልም ተናግረዋል፡፡

የብሪክስ አባል ሀገራት መካከል በማኑፋክቸሪንግ፣ ግብርና፣ ኢነርጂ፣ ቱሪዝምና የመሳሰሉ ዘርፎች ላይ ጠንካራ የኢኮኖሚ ትብብር ሊያደርጉ እንደሚገባ ጠቅሰው፣ ኢትዮጵያ የጋራ ራዕይን ለማሳካት በንቃት ለመሳተፍ ያላትን ቁርጠኝነትንም ገልጸዋል፡፡

የቡድኑ መሪዎች መሰባሰብ ሀገራቱ ዛሬ የሚያጋጥሟቸውን አንገብጋቢ ዓለም አቀፍ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ ውጤታማ የባለብዙ ወገን ትብብር ተስፋ እንዳለው የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ኢትዮጵያ ያደጉትንና በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት መካከል በፍትሃዊነት መርህ ላይ በተመሠረተ መልኩ ለመሳተፍ ዝግጁ ናት ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ አዲስ የብሪክስ አባል እንደመሆኗ በፍትሃዊነት መርህ ያደጉ እና በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ያማከለ ባለብዙ ወገን ትብብር እንዲጎለብት ለማድረግ እንደምትሠራም አመልክተዋል፡፡

ዓለም ጥበብና ማስተዋልን በሚጠይቁ በርካታ ቀውሶች በፍጥነት እየተለወጠች መሆኗን ጠቅሰው፣ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን የምጣኔ ሀብት እድገት የሚፈታተነው ፍትሃዊ ያልሆነ የዓለም የፋይናንስ ሥርዓት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ማዕቀፋችን ውስጥ ያለው አለመመጣጠን የዋጋ ንረት፣ ስራ አጥነትን እየጨመረ መምጣቱ ከምንጊዜውም በላይ የጋራ ጥረቶችን እንደሚጠይቅ በመግለጽ፣ ቀውሱ እየጨመረ በሄደ ቁጥር የአየር ንብረት ርምጃና የአየር ንብረት ፋይናንስ የቀረቡ ጥያቄዎች ችላ እየተባሉ መቀጠላቸውንም ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፀጥታው ምክር ቤት ማሻሻያ ትኩረት ሊሰጠን የሚገባው መሆኑን እንደምታምን የገለጹት ዐቢይ (ዶ/ር)፣ የጉባዔው ተሳታፊ ሀገራትም አፍሪካ በተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት የአፍሪካን ውክልና የአፍሪካን የጋራ አቋም በማክበር ቅድሚያ እንደሚሰጥ ያላቸውን እምነት ገልጸዋል፡፡

ጥያቄው ውክልና ብቻ ሳይሆን ፍትህ፣ ፍትሃዊነትና ሁሉም ሀገራት ለዓለምአቀፍ አስተዳደር የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ከሰሃራ በታች ካሉ ሀገራት በሶስተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሀገሪቱ ወጣት የሰው ሃይል፣ ሰፊ የእርሻ መሬትና በቂ የታዳሽ ሃይል ሀብት እንዳላትና የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያውም አዳዲስ ለውጦችን እያስገኘ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ በስድስት ዓመታት የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃግብር ከ40 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን ለመትከል ኢኒሼቲቭ ቀርጻ ዜጎችን ማንቀሳቀሷን በመግለጽ፣ ቀጣይነት ያለውና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ሥርዓት ለመገንባት ቁርጠኛ መሆኑዋን ተናግረዋል፡፡

ከጉባዔው ጎን ለጎን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከተለያዩ የብሪክስ አባል ሀገራት መሪዎች ጋር በሁለትዮሽና ቀጣናዊ ጉዳዮች ላይ ውይይት አድርገዋል፡፡

# በክልሉ ከ800 ሺህ …

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የክልሉ ባሕል ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ ገለጸ፡፡

የሲዳማ ክልል ባሕል ቱሪዝም እና ስፖርት ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊና የቱሪዝም ዘርፍ ኃላፊ አቶ አበበ ማሪማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሩብ ዓመቱ 800 ሺህ የሀገር ውስጥ ጎብኚዎች እና 5 ሺህ የውጭ አገር ጎብኚዎች የክልሉ የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎችን ጎብኝተዋል፡፡

እንደ አቶ አበበ ገለጻ ፤ በሩብ ዓመቱ ከጎብኚዎች በተለያየ መልኩ የተገኘ 750 ሚሊዮን ብር ኢኮኖሚው ላይ ፈሰስ ተደርጓል፡፡

የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ቁጥር በቀጣዮቹ የበጋ ወራት እየጨመረ እንደሚሄድ እንደሚጠበቅ ገልጸው የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ቁጥር ግን በተመሳሳይ ሊቀጥል እንደሚችል አመላክተዋል፡፡

የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን የተናገሩት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በባለፈው በጀት ዓመት ብቻ ሶስት ሚሊዮን ቱሪስቶች ክልሉን መጎብኘታቸውን ተናግረዋል፡፡ በዓመቱ ሁለት ነጥብ 5 ቢሊዮን ብርም ወደ ኢኮኖሚው ፈሰስ መደረጉንም አክለው ገልጸዋል፡፡

በመንግሥት ቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ መሆኑን ተናግረው፤ የቱሪስት መዳረሻዎችን ቁጥር ለማሳደግ እና የቱሪስት የቆይታ ጊዜን ለመጨመር እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

በክልሉ ያሉት ሶስት ትልልቅ የቱሪስት መዳረሻዎች መሆናቸውን ጠቁመው፤ አሁን ላይ ተጨማሪ መዳረሻዎችን ለመጨመር ከሃዋሳ ከተማ በስተደቡብ 90 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኝ ገራምባ በሚባል ቦታ ላይ ማህበረሰብ አቀፍ የቱሪዝም መዳረሻ እየለማ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

በክልሉ ብቸኛው ፓርክ የሆነውን ሎካ አባያ ብሔራዊ ፓርክን የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ሳፋሪ ሎጅ እየተገነባ መሆኑን ገልጸው፤ ግንባታው ሲጠናቀቅ በክልሉ አምስተኛው የቱሪዝም መዳረሻ እንደሚሆን ጠቁመዋል። ሁለቱም በግንባታ ላይ የሚገኙት የቱሪዝም መዳረሻዎች በተያዘው ዓመት እንደሚጠናቀቁም ገልጸዋል፡፡

ከመዳረሻ ልማት ጎን ለጎን ነባር የቱሪስት መዳረሻዎች ላይ እሴት የመጨመር ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረው፤ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በጥራት፣ በብቃት እና በቁጥርም በብዛት እንዲደራጁ እንደሚደረግም ተናግረዋል፡፡ የቱሪዝሙን ሀብት የማስተዋወቅ ሥራዎችም እየተከናወኑ ነው፡፡

የሲዳማ ክልል በተፈጥሮ ሀብት የታደለ መሆኑን አመልክተው፤ ሁሉም ሰው ወደ ክልሉ በመምጣት ክልሉን እንዲጎበኝ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የአፍሪካ የደህንነት…

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚጠበቅባትን ያህል ተጉዛለች ማለት እንደማይቻል ሌሎች ያነሳሉ፡፡

በአፍሪካ ኅብረት የፖለቲካ ጉዳዮችና የፀረ ሽብር ማዕከል ኃላፊ ባባቱንዴ አባዮሚ እንደሚሉት፤ በትብብሩ ምንም እንኳን መሻሻል ቢኖርም፤ በፖለቲካዊ ፍላጎት እና ፋይናንስ እጥረት ምክንያት አሁንም በጋራ ጉዳዮች ላይ መላላቶች ይስተዋላሉ፡፡ ይህ መቀዛቀዝ የአፍሪካ ለችግሮች ውጤታማ ምላሽ የመስጠት አቅምን በእጅጉ ይጎዳል።

ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች፣ የጸጥታ ችግሮች፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የጂኦ ፖለቲካ ፉክክርና ሌሎች ከጸጥታ ጋር የተገናኙ ችግሮች አህጉሪቱን እየፈተኑ ይገኛሉ በማለት፤ ለአፍሪካ የጸጥታ ችግሮች የአፍሪካ አባል ሀገራት በተጠናከረ የጋራ ትብብር ሊሠሩ እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡ የአፍሪካ ህብረትም ለመሰል የትብብር ሥራዎች ድጋፉን አጠናክሮ ይቀጥላል ነው ያሉት፡፡

የውጭ ኃይሎች በአፍሪካ ሰላምና ደህንነት ላይ ተጽዕኖ ለመፍጠር መሞከር አንዱ ተግዳሮት መሆኑን በማንሳት፤ በአፍሪካ ጉዳይ የኃያላን ሀገራት ፍላጎቶች መጨመር ወደ ሀብት ፉክክር እየገባ እንዳለ፤ ይህም ብዙውን ጊዜ የአፍሪካን አንድነት ሊያቀዛቅዝ እንደሚችል ይጠቅሳሉ፡፡ ይህ ውድድር በአህጉሪቱ የገጠማትን የጸጥታ ችግር የበለጠ ያባብሰዋልም ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የጂኦፖለቲካል ፉክክር እና የኃያላን ሀገራት ፉክክር እየጨመረ በመምጣቱ የአፍሪካን የጋራ ጥረት እያናጋ፣ የድንበር ግጭት እና የፖለቲካ አለመረጋጋት ብሎም የአፍሪካ ህብረት 2063 አጀንዳን ስኬታማነት ላይ መሰናከል እየሆነ መሆኑን አስጠንቅቀዋል።

ይህ ሃሳባቸው አፍሪካ የብዙ ግጭቶች መነሻ ከቅኝ ግዛት ይዞቻው ከመጣው ጦሶች ጋር የተቆራኘ ነው የሚሉትን የባለሙያዎችን ሃሳቦች የሚደግፍ ነው፡፡

አዲባጆ እና ራሺድ የተባሉ አጥኚዎች እኤአ በ2019 በጸጥታ ዙሪያ ባደሩገት ጥናት መሠረት እነዚህ የቅኝ ግዛት ድንበሮች አለመግባባቶችን ዘርተዋል፤ ይህም አሁን ያለውን የጥታ ሁኔታ አወሳስቦታል ይላሉ፡፡

አሁን ላይ የሚታዩት ፉክክሮች ኢኮኖሚያዊ ውጤቶችም ከፍተኛ መሆናቸውን ያመላከቱት አጥኚዎቹ፤ የውጭ ኃይሎች ከአፍሪካ ፍላጎቶች ይልቅ ስልታዊ ጥቅሞቻቸውን ሊያስቀድሙ ስለሚችሉ የጂኦፖለቲካ ውድድር ብዙውን ጊዜ አስፈላጊ ከሆኑ የልማት አጀንዳዎች ትኩረትን ይሰርዛል ሲሉ ነው የገለጹት፡፡

እንደ ቦኮ ሃራም እና አልሸባብ ባሉ ቡድኖች ከሽብርተኝነት እስከ የሳይበር ዛቻዎች ድረስ ያለው የደህንነት ስጋቶች ጠንካራ እና የተቀናጀ ምላሽ ያስፈልገዋል ያሉት ባባቱንዴ፤ ለዚህ ደግሞ የተሻለ የፖለቲካ ቁርጠኝነት አስፈላጊነት ላይ አፅንዖት መስጠት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ፡፡ በአዲስ አበባ የተካሄደው ጉባዔ የአፍሪካ ሀገራት የመከላከያ ስልታቸውን እና የትብብር ማዕቀፎቻቸውን እንደገና እንዲገመግሙበት ወሳኝ ጊዜ ሆኖ እንደሚያገለግል የባባቱንዴ አባዮሚ ጠቅሰዋል፡፡

የግሎባል ሽብርተኝነት ኢንዴክስ እኤአ በ2022 "አፍሪካ የዓለማችን ገዳይ አሸባሪ ድርጅቶች መገኛ ናት" በማለት፤ አስቸኳይ የአንድነት ግንባር እንደሚያስፈልግ አመልክቷል፡፡

የጎሳ ግጭቶችን ጨምሮ ከመፈንቅለ መንግሥት የሚመነጩ አካሄዶችና የፖለቲካ አለመረጋጋት በሚያስደነግጥ ሁኔታ ተደጋጋሚ በሆነ መልኩ የጸጥታ ምህዳሩን እያወሳሰቡ መሆናቸውን አትቷል፡፡

የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዳይሬክተር ጄኔራል አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን "በአፍሪካ የመከላከያ ኃይሎች መካከል ያለውን ትብብር" በተመለከተው ጽሑፋቸው፤ አሸባሪዎች፣ ጽንፈኛ ቡድኖች፣ የባህር ላይ ወንበዴዎችና የድንበር ግጭቶች አፍሪካን እያመሷት መሆኑን ገልፀዋል። በዚህም አህጉሪቱ በአሁኑ ወቅት በርካታ ማኅበረ-ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን እየተጋፈጠች መሆኗን አመላክተዋል፡፡

የውጭ ኃይሎችም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አህጉራዊ የደህንነት ስጋት መፍጠራቸውን ያነሱት አምባሳደር ሬድዋን፤ አፍሪካ እያጋጠሟት ያሉትን ችግሮች የውጭ ኃይሎች እንዲፈቱልን ማማተር አይገባም በማለት፤ "ከውጭ የሚመጣ መፍትሔ ቢኖር እርስ በርስ እየተጋጨን ልዩነቶቻችንን አስፍተን በችግር እንድንማቅቅ የሚያደርግ ነው" ይላሉ፡፡

ለዚህ ደግሞ መተማመን ላይ የተመሠረተ የሀገራት ግንኙነት፣ ችግሮችን በሰላማዊ ድርድር የመፍታት ባህል፣ የተፈጥሮ ሀብቶችን በፍትሃዊነት መጠቀም ግጭቶችን አስወግዶ አፍሪካዊ የጋራ የብልፅግና እና የሰላም ራዕይን ማሳካት እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡ ይህ የአምባሳደር ሬድዋን ምልከታም ከተመራማሪዎቹ አዲባጆና ረሺድ ምልከታ ጋር የሚዛመድ ብሎም ለአፍሪካ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሄ አስፈላጊነትንም የሚጠቁም ነው፡፡

አፍሪካ በተባበረ ክንድ ሰላሟን እንድታስጠብቅ የአፍሪካ አንድነት ታሪካዊ ሁኔታም ጉልህ ሚና ይጫወታል የሚሉት ባባቱንዴ በበኩላቸው፤ የአፍሪካ ህብረት አጀንዳ 2063 የበለፀገች፣ የተዋሃደች አፍሪካን የመገንባት ራዕይ ሊሳካ የሚችለው በአባል ሀገራት መካከል አንድነት ሲኖር መሆኑን አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡ የተለያዩ ቀጣናዊ ግጭቶች፣ የፖለቲካ አለመረጋጋትን ለመፍታት ብቃቱ ከፍ ያለ ጠንካራ ህብረት እንደሚያስፈልግ ያብራራሉ፡፡

የዘርፉ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች እንደሚገልጹት፤ በአፍሪካ ውስጥ ጠንካራና የተዋሃደ የመከላከያ ማዕቀፍ መመሥረት የአህጉሪቱን የፀጥታ ሁኔታ በእጅጉ ሊለውጠው ይችላል። የአፍሪካ ሀገራት የፖለቲካ ፍላጎትን እና ትብብርን ማጎልበት ከቻሉ ያሉትን ስጋቶች ማቃለል ብቻ ሳይሆን በጋራ የሚያድጉበት ሁኔታም ይፈጠራል፡፡ ለዚህ ደግሞ አህጉራዊ ስትራቴጂዎችን በተሳካ ሁኔታ መተግበሩ ለተረጋጋ እና አስተማማኝ አፍሪካ መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በውጭ ኃይሎች ርዳታ ላይ ያለውን ጥገኝነት ተባብሶ የአህጉሪቱ ደህንነት ስጋት እየሆነ ይቀጥላል ሲሉ ያስጠነቅቃሉ፡፡

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ለትራንስፖርት ዘርፍ ታዳሽ የኃይል አማራጭን ያቀረቡት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች

**አንተነህ ቸሬ**

ኢትዮጵያ ከመኪና ጋር የተዋወቀችው ከ115 ዓመታት በፊት፣ በዳግማዊ አፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ነው። በ1900 ዓ.ም የተጀመረው የኢትዮጵያና የመኪና ትውውቅ፣ ብዙ ደረጃዎችን አልፎ ዛሬ ካለበት ደርሷል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ተሽከርካሪዎች ይገኛሉ። ይሁን እንጂ ከእነዚህ ተሽከርካሪዎች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት እድሜያቸው የገፉ (አሮጌዎች) እና ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ የሚጠይቁ ናቸው፡፡

በዓለም ገበያ የነዳጅ ዋጋ እየጨመረ ነው። ከዚህ በተጨማሪም በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች የሚወጣውና ለአየር ብክለት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ጭስ፣ ለአካባቢ ስነ ምኅዳር ትልቅ አደጋ ሆኖ ቀጥሏል።

የነዳጅ ዋጋ መጨመር ያደጉትንም ሆኑ ታዳጊ ሀገራትን አማራጭ የትራንስፖርት ዘርፎችን እንዲያማትሩ እያስገደዳቸው ነው። ከእነዚህ አማራጮች መካከል አንዱ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን መጠቀም ነው። ቻይና የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በብዛት በመጠቀም ቀዳሚውን ስፍራ ይዛለች።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በየጊዜው በአዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እየተሻሻሉና ተጠቃሚያቸውም እየጨመረ ይገኛል። ተሽከርካሪዎቹ በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱት ተሽከርካሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ የራሳቸው የሆኑ ጥቅሞች አሏቸው። ለአብነት ያህል ከወጪ አንፃር የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎቹን ባትሪ ሙሉ (Full) ለማድረግ የሚፈጀው ወጪ፣ የነዳጅ ተሽከርካሪዎች ከሚፈልጉት ወጪ በ24 በመቶ ይቀንሳል።

ተሽከርካሪዎቹ ለመንቀሳቀስ የሚጠቀሙት በሀገር ውስጥ የተመረተ የኤሌክትሪክ ኃይል ነው። የሀገር ውስጥ ኤሌክትሪክ የሚገኘው ደግሞ ከታዳሽ የኃይል ምንጮች ስለሆነ ይህ ዓይነቱ የኃይል አጠቃቀም እንደሀገር ጭምር ለነዳጅ የሚጣውን ወጪ ለመቀነስ ትልቅ ሚና ይኖረዋል። ከዚህ በተጨማሪም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ምንም ዓይነት ጭስ ወደ ከባቢ አየር የማይለቁ በመሆናቸው የአየር ብክለትን በማስወገድ የአካባቢ ጥበቃን አስተማማኝ ለማድረግ ያስችላሉ።

ኢትዮጵያም በየዓመቱ ለነዳጅ ግዢ ከፍተኛ ገንዘብ ታወጣለች፤ይህም በውጭ ምንዛሬ ክምችቷ ላይ ትልቅ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው። በሀገሪቱ የሚገኙት አብዛኞቹ ተሽከርካሪዎች ከፍተኛ የነዳጅ ፍጆታ ያላቸው በመሆናቸው ከተሽከርካሪዎቹ የሚወጣው ጭስ ለአየር ብክለት ምክንያት በመሆን በከፍተኛ ደረጃ ይጠቀሳል። እነዚህን ፈተናዎች ለመቀየር ከተጀመሩት ስራዎች መካከል አንዱ የማበረታቻ ስርዓቶችን በመዘርጋት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባትና አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ነው፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግሥትም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎች ጋር ሲነፃፀሩ ያላቸውን አንፃራዊ ጥቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ኢንቨስትመንት ላይ የሚሰማሩ ኢንዱስትሪዎችንና አስመጪዎችን የሚያበረታታ እንዲሁም ህብረተሰቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ የታክስ ማሻሻያ ተግባራዊ ማድረጉን የገንዘብ ሚኒስቴር ማስታወቁ ይታወሳል። የታክስ ማሻሻያው ዓላማ በኢትዮጵያ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ የመጣውን የተሽከርካሪዎች ቁጥር በፖሊሲ ማሕቀፍ ከአካባቢ ደህንነት ጋር የሚስማማ ለማድረግ፣ በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትል፣ በአየር ንብረትና በብዝሃ ህይወት ላይ ተጽእኖ የማያሳርፍ እና ታዳሽ የኃይል ምንጮችን በአግባቡ የሚጠቀም የመጓጓዣ ሥርዓት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲሁም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለህብረተሰቡ እንዲቀርቡ ለማስቻል እንደሆነም መገለፁ ይታወሳል፡፡

በዚህ የታክስ ማሻሻያ ከውጭ የሚገቡም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረቱ የኤሌክትሪክ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች፣ የቤት አውቶሞቢሎች እና የእቃ መጫኛ ተሽከርካሪዎች ላይ ዝቅተኛ የጉምሩክ ታሪፍ የሚጣልባቸው ሲሆን ከተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ከኤክሳይዝ ታክስና ከሱር ታክስ ነፃ ይደረጋሉ። በታክስ ማሻሻያው መሰረት የኤሌክትሪክ የቤት አውቶሞቢሎችን በተመለከተም ሙሉ በሙሉ ተበትነው ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው የሚገጣጠሙ የኤሌክትሪክ የቤት አውቶሞቢሎች ከጉምሩክ ቀረጥ፣ ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

> “
>
> **መንግሥት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለማበረታታት በወሰዳቸው እርምጃዎች ምክንያት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቁጥር እንደጨመረ ይገኛል፡፡ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ የሚገጣጥሙ ድርጅቶች 15 እንዲሁም ተሽከርካሪዎቹን የሚያስመጡ ደግሞ ከ200 በላይ ሆነዋል**

በከፊል ተበትነው ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው የሚገጣጠሙ የኤሌክትሪክ የቤት አውቶሞቢሎች አምስት በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ ብቻ የሚጣልባቸው ሲሆን፣ ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ ተደርጓል። ሙሉ ለሙሉ ተገጣጥመው ያለቀላቸው የኤሌክትሪክ አውቶሞቢሎች ወደ ሀገር ሲገቡ ደግሞ 15 በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ ብቻ የሚጣልባቸው ሲሆን ከኤክሳይዝ ታክስ፣ ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከሱር ታክስ ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ ተወስኗል። የታክስ ማሻሻያው ከተደረገ በኋላም በርካታ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር አስታውቆ ነበር፡፡

በአሁኑ ወቅት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ በመገጣጠም እና ከውጭ በማስመጣት ለገበያ የሚያቀርቡ ድርጅቶች አሉ። መኪኖቹን በሀገር ውስጥ በመገጣጠም ለገበያ ከሚያቀርቡት ድርጅቶች መካከል ‹‹በላይነህ ክንዴ ግሩፕ›› አንዱ ነው። ድርጅቱ ደብረ ብርሃን እና ገላን በሚገኙ ፋብሪካዎቹ የኤሌክትሪክ ሚኒባሶችንና አውቶቡሶችን በሀገር ውስጥ ገጣጥሞ ለገበያ በማቅረብ ፈር ቀዳጅ ተቋም መሆን ችሏል።

የ‹‹በላይነህ ክንዴ ግሩፕ›› የኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሰጠኝ እንግዳው እንደሚናገሩት፣ ድርጅቱ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን እየገጣጠመ ለገበያ ማቅረብ የጀመረው ባለፈው ዓመት (በ2016) ነው። ‹‹ድርጅታችን ‹በላይነህ ክንዴ ግሩፕ› ከተሰማራባቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች መካከል አንዱ የአውቶሞቲቭ ዘርፍ ነው። በአውቶሞቲቭ ዘርፍ ስራ ከጀመረ ስምንት ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ ዓመታት የደረቅና ፈሳሽ ጭነት መኪኖችን፣ በተለይም የ ‹IVECO› ብራንድ መኪኖችን እየገጣጠመ ለገበያ ሲያቀርብ ቆይቷል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

ካለፈው ዓመት ጀምሮ ደግሞ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ገጣጥሞ ለገበያ እያቀረበ እንደሚገኝ አመልክተው፣ በመጀመሪያው ዙር 15 ሰው የመያዝ አቅም ያላቸውን፣ በአንድ ጊዜ ቻርጅ ከ270 እስከ 350 ኪሎ ሜትር ድረስ መጓዝ የሚችሉ 216 የኤሌክትሪክ ሚኒባሶችን ገጣጥመን ለገበያ አቅርበናል ብለዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ሚኒባሶቹ በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ 150 የሚሆኑትን ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በማቅረብ የተለያዩ ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎች ሴክተር ተቋማት እየተጠቀሙባቸው ይገኛሉ። ሌሎች ተቋማትም መኪኖቹን ገዝተው ጥቅም ላይ አውለዋቸዋል። የደብረ ብርሃኑ ፋብሪካ በቀን አራት ሚኒባስና ሁለት አውቶቡሶችን እንዲሁም የገላኑ ደግሞ በቀን አራት ሚኒባሶችን የመገጣጠም አቅም አላቸው።

አቶ ሰጠኝ እንደሚገልፁት፣ ድርጅቱ ከኤሌክትሪክ ሚኒባሶች በተጨማሪ የኤሌክትሪክ አውቶቡሶችንም እየገጣጠመ ለገበያ እያቀረበ ነው። በአሁኑ ወቅት እስከ 70 ሰው የሚይዙ 10 የኤሌክትሪክ አውቶቡሶች ለገበያ ቀርበዋል። የመጀመሪያዎቹን አራት የኤሌክትሪክ አውቶቡሶች ለኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስረክቧል። ሁለት ተጨማሪ አውቶቡሶች ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ። የደንበኞችን ፍላጎት መሰረት በማድረግ በቅርቡ ተጨማሪ አውቶቡሶች እና 120 የኤሌክትሪክ ሚኒባሶች ተገጣጥመው ለገበያ ይቀርባሉ።

ድርጅቱ የኤሌክትሪክ አውቶቡሶችንና ሚኒባሶችን ገጣጥሞ ለገበያ ከማቅረብ በተጨማሪ፣ በኤሌክትሪክ መኪኖች የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጠ ነው። የኤሌክትሪክ መኪኖችን ወደ ስራ ይዞ ገብቷል። ‹‹ቬሎሲቲ›› በሚባል የድርጅቱ እህት ኩባንያ አማካኝነት 20 ሚኒባሶችንና ሁለት አውቶቡሶችን ይዞ በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን አገልግሎት ላይ የማዋሉ ተግባር ስኬታማ እንዲሆን ከሚያስፈልጉ ግብዓቶች መካከል አንዱ ለተሽከርካሪዎቹ ኃይል የሚያቀርቡ የባትሪ መሙያ ጣቢያዎችን (Charging Stations) መገንባት ነው። በርካታ ግለሰቦችና ተቋማት የእነዚህን መሰረተ ልማቶች እጥረትን እንደዋና የዘርፉ ተግዳሮት አድርገው ሲጠቅሱት ይስተዋላል። ‹‹በላይነህ ክንዴ ግሩፕ›› ገጣጥሞ ለገበያ የሚያቀርባቸው የኤሌክትሪክ መኪኖች የቻርጀርና የመለዋወጫ እጥረት እንደሌለባቸው አቶ ሰጠኝ ይገልፃሉ። ድርጅቱ በዓለም ላይ በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙ ቻርጀሮችንም ከቻይና በማስመጣት ለገበያ ማቅረቡን አስታውቀዋል።

‹‹በሀገር ደረጃ ያለው አንዱ ችግር የኤሌክትሪካ ቻርጀሮች በበቂ ሁኔታ አለመኖር ነው። የኤሌክትሪክ መኪና ስላስመጣን ብቻ የኤሌክትሪክ መኪኖቹን መንገድ ላይ እናያለን ማለት አይደለም። ባትሪያቸው የሚሞላበት ቻርጀር ያስፈልጋል። የኤሌክትሪክ መኪኖች ሁለት ዓይነት ቻርጀሮች አሏቸው። አንደኛው ሁሉም ሰው በቤቱ ውስጥ ከሚገኝ የኃይል ምንጭ ባትሪ ሊሞላበት የሚችለው ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ በአጭር ጊዜ (ቢበዛ በ45 ደቂቃ) ባትሪ የሚሞሉ ፈጣን ቻርጀሮች (Fast Chargers) ናቸው›› ሲሉ አቶ ሰጠኝ ያብራራሉ።

‹‹በመጀመሪያ ከ60 እስከ 180 ኪሎ ዋት ከፍተኛ አቅም እንዲሁም ዋስትና ያላቸውን 120 ፈጣን ቻርጀሮችን አስመጥተናል። መኪና ለሚገዙም ሆነ በቻርጀር አቅርቦት ላይ ለተሰማሩ አካላትም እያቀረብን ነው። የስልጠና አገልግሎትም እንሰጣለን›› ይላሉ። ከዚህ በተጨማሪም ድርጅቱ ከመንግሥት ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎች ቻርጀሮችን ለመግጠም ስራ እንደጀመረም ጠቁመዋል።

አቶ ሰጠኝ እንዳብራሩት፤ የኤሌክትሪክ መኪኖችን ተጠቃሚነት የማበረታታት ሀገራዊ እቅድ የተሻለ አፈፃፀም እንዲኖረው የኤሌክትሪክ መኪኖቹ ጥንካሬ ኖሯቸው በተሻለ ጥራትና አስተማማኝነት ለገበያ እንዲቀርቡ ይደረጋል። የሚገጣጠሙት የመኪኖቹ ክፍሎች ከመሰራታቸውና ወደ ሀገር ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ከኢትዮጵያ የአየር ፀባይ ጋር ተስማሚ እንዲሆኑ ጥናት ተደርጓል። ለሞተር መቀመጫ የሚሆኑት ቦታዎች ከኢትዮጵያ የመሬት አቀማመጥ፣ የመንገድ ሁኔታ ጋር የሚስማማ መሆኑም ተጠንቷል። ድርጅቱ መኪኖቹን ለገዢዎች ሲያስረክብ ስልጠናና ዋስትና ይሰጣል። ደንበኞች መኪኖቹን ከወሰዱ በኋላም በድርጅቱ ባለሙያዎች ክትትልና ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

በነዳጅ ዋጋ መጨመርና በአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ምክንያት የኤሌክትሪክ መኪኖች ፍላጎት እየጨመረ እንደሚገኝ የሚናገሩት አቶ ሰጠኝ፣ እንደሀገር ደግሞ ታዳሽ ኃይልን በስፋት ከመጠቀም አንፃር የኤሌክትሪክ መኪኖችን የመጠቀም ፍላጎት እያደገ እንደሚሄድ ያላቸውን እምነት ይገልፃሉ። ‹‹በላይነህ ክንዴ ግሩፕ››ም በኢትዮጵያ በኤሌክትሪክ መኪኖች ልማት ላይ በስፋት በመሳተፍ በሀገር ደረጃ የራሱን አሻራ የማሳረፍ እቅድ እንዳለው ይናገራሉ። የኤሌክትሪክ መኪኖችን ለማስፋፋት በመንግሥት በኩል ያለው ጥረት አበረታች መሆኑ ለዚህ አስተዋፅዖ እንደሚኖረውም ገልፀው፣ ኃይል አቅርቦትን ማሻሻል፣ መሰረተ ልማቶችን (በተለይም የባትሪ መሙያ ጣቢያዎችን) ማሟላት እንዲሁም ኅብረተሰቡ ስለኤሌክትሪክ መኪኖች ያለውን አስተሳሰብ ማሳደግ እንደሚገባም ይመክራሉ።

በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴር የአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ይዘንጋው ይታይህ፣ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ካላቸው አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊና ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ አንፃር መንግሥት ተሽከርካሪዎቹ በሀገር ውስጥ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውሉ የሚያበረታቱ እርምጃዎችን እየወሰደ እንደሚገኝ ይገልፃሉ።

ይህን ለማሳካትም ስትራቴጂዎች፣ የማበረታቻ ስርዓቶች እና የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ስታንዳርዶች ተዘጋጅተዋል። ስትራቴጂው የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ እንዲሁም በሀገር ውስጥ እንዲገጣጠሙና በስፋት ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ያበረታታል። ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችና መሰረተ ልማቶቻቸው በአነስተኛ ታክስ ብሎም ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ተደርጓል።

መንግሥት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ለማበረታታት በወሰዳቸው እርምጃዎች ምክንያት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ቁጥር እንደጨመረ የሚጠቁሙት አቶ ይዘንጋው፤ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ የሚገጣጥሙ ድርጅቶች 15 እንዲሁም ተሽከርካሪዎቹን የሚያስመጡት ደግሞ ከ200 በላይ እንደሆኑ ይገልፃሉ። ከዚህ በተጨማሪም የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ወጭንና የአካባቢ ብክለት በማስቀረት ረገድ ከፍተኛ ጥቅም ስላላቸው፣ ኅብረተሰቡ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ሊጠቀም እንደሚገባም አቶ ይዘንጋው ይመክራሉ።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ጎሜ

# ኢትዮጵያ የምትሻው ሰላምንና ወንድማማችነትን ነው

**ይቤ.ከደጃች ውቤ**

የሰው ልጅ ከራሱ አልፎ ፍቅርን ፣ወንድማማችነትን እነ ሰላምን ከእንስሳት መማር ይችላል። ለመማር የፈለገ ማለቴ ነው። በተለይም ለሰው ልጆች አብሮ ለመኖር እና ኑሮንም በደስታ ለማሳለፍ ሰላም የማይተካ ሚና አለው። ሰላም ሁሉም ነገር ማጠንጠኛ ነው። አርሶ ለመብላት፣ወልዶ ለማሳም ፣ነግዶ ለማትረፍ፣ተምሮ ለመመረቅና እና ሥራ ለመያዝ ሰላም መሰረታዊ ነገር ነው።

ሆኖም ይህንን እውነታ በመዘንጋት ዓለም ሰላሟን ካጣች ውላ አድራለች። በአራቱም ማእዘናት የሚተኮስ ጥይት፣የሚፈናዳ ፈንጂ የትየለሌ ነው። በዚህም የሰዎች ሕይወት ይቀጠፋል፣ አካል ይጎድላል፣ስደት እና መፈናቀል ይበዛል፣የሰዎች ሕይወት ይመሰቃቀላል፣ይህቺ ዓለምም ገሃነም ትሆናለች። በዚህ ውስጥ ደግሞ ሴቶችና ህጻናት የበለጠ ተጎጂዎች ይሆናሉ፡፡

መረጃዎች እንደሚያሳዩት በዓለም 126 የሚጠጉ ሀገራት በሳል እጦት ውስጥ ይገኛሉ። በዚህም ዓለማችን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ እና ሰብአዊ ኪሳራዎችን እያስተናገደች ትገኛለች። ጦርነት እና ግጭቱ በፈጠረው ምስቅልቅል ምክንያት ሸቀጦችን ከአንዱ አህጉር ወደሌላው መጓጓዝ አዳጋች ሆኗል። የሰዎች ዝውውርም ተገድቧል። በዚህም የሸቀጦች ዋጋ እንዲንር እና የኑሮ ውድነት በዓለም ደረጃ እንዲባባሳ ምክንያት ሆኗል፡፡

ከኑሮ ውድነቱ ባሻገር የሰው ልጅ እርስ በራሱ ሲጫረስ ማየት ያሳዝናል። ህጻናት በየቦታው ወድቀው፤አረጋውያን ተጎሳቁለውና እና የጥይት እና የቦንብ እራት ሆነው መመልከት በእጅጉ ያሳቅቃል። ድርጊቱም የሰው ልጅ ከእንስሳት ያነሰ ወንድማማችነት እና አንድነትን እያጣ መምጣቱን የሚያሳይ ነው፡፡

ውሻ ለማዳ የቤት እንስሳ ሲሆን ከቀበሮ፣ ተኩላ እና ጅብ ተዛማጅ ነው፤የከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ውሻ የቤት እንስሳ ቤትን የሚጠብቅ ሲለው ተኩላን ደግሞ ሥጋን የሚበላ የጅብ የቀበሮ የውሻ ዘመድ በቆላ በሙቀት ሀገር የሚኖር በግን ፍየልን እየነጠቀ የሚበላ በሚል ይፈታዋል፡፡ቀበሮንም እንደ ውሻ ያለ በግ የሚበላ ጉድጓድ እየቆፈረ የሚኖር ይለዋል፡፡

ውሻ ከሰዎች ጋር ረጅም ዘመን ከኖሩና ካገለገሉ የቤት እንስሳት ይጠቀሳል። የሚለየው ከበድ ያለ ሥራ የማይጠበቅበት መሆኑ ነው። አንዳንዶች ግን ለአሳዳሪዎቹ ጭራውን እየቆላ የሚኖር ይሉታል። እርግጥ ነው በአንዳንድ ሀገሮች ቤትና ንብረትን መጠበቅ ሰራቂን መጠበቅ ጭምር ነው። ሰዎች ውሻን ሲያሳድጉት ቤት እንዲጠብቅላቸው ሌባ እንዲይዝላቸው ነው። ከዚህ አልፎ በዘመናችን ውሻ እየሠለጠነ ለፖሊስ አጋዥ እየሆነ ነው። በተጨማሪም በፖሊስ ሰልጥኖ ድንበሮችንና የጉምሩክ ቦታዎችን ይጠብቃል። እንደ አደንዛዥ ዕጽ፣ የጦር መሣሪያ የመሳሰሉ መሣሪያዎችን ከተደበቁበት ያጋልጣል።

በእኛም ሀገር በፖሊስ የሠለጠኑ ውሾች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች ተይዘው፤የተደበቁ የጦር መሣሪያዎችን የተቀበሩ አደንዛዥ ዕጾችን ያጋልጣሉ። ለፖሊስ አገልግሎት በአጋዥነት የሚሰለጥነው ውሻ፤ በቁመቱ ዘለግ ያለ እንደ ተኩላ ዓይነት ቁመና ያለው ነው።

አሜሪካ ብቻ በየዓመቱ አንድ ሚሊዮን የሚደርሱ ውሾችን ከሌሎች ሀገራት የምታስገባ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ አሁን ከፍተኛ የእብድ ውሻ ስጋት አለባቸው ተብለው እገዳ ከተጣለባቸው ሀገራት የሚመጡት ውሾች መጠን 60 በመቶውን እንደሚሸፍን መረጃዎች ያሳያሉ። አሜሪካ ውስጥ ውሾች በመደበኛነት የሚከተቡ ሲሆን የእብድ ውሻ በሽታ ከ15 ዓመት በፊት ከሀገሪቱ እንደጠፋ ይነገራል።

በሳይንስ እንስሶች በሦስት እንደሚከፈሉ ይነገር ነበር። ሣርና ቅጠል በል Herbivorous ሥጋ በል (Carnivorous) እና Omnivorous ሁለቱንም የሚበሉ። በወቅቱ ትምህርት ሥጋም አረንጓዴ ቅጠልም የሚበላው ሰው ብቻ ነበር። ግን ዘግይቶ ስንረዳው ድመትና ውሻም ቅጠላ ቅጠሉንም ሥጋውንም ይበላሉ፤ ቅጠላ ቅጠሉን ስል ደግሞ እንደ በግና ፍየል ሣር እየነጩ ውሃ እየተጎነጩ ይኖራሉ አለማለቴ ይሰመርበት። ያው ቂጣውን ዳቦውን እንጀራውን ጣል ሲደረግላቸው ይበላሉ ለማለት ነው። አይጥም ስትፈልግ እንጨቱን በጥርስዋ ትነጨዋለች በቤት ያለ የሚበላም የማይበላም በመብላት ቀዳሚ ነች። አዲስ ልብስ ገዝታችሁ ስታበቁ የቆዳም ይኹን የጨርቅም በጥርስዋ በመቦጨቅ ማን ይችላታል? እርሷም እንዲሁ በኔ እሳቤ ሥጋውንም ቅጠሉን ከሚበሉ የምትመደብ ነች።

በመዲናችን ብቻ በ2012 በወጣ መረጃ ሩብ ሚሊዮን የሚጠጉ ውሾች ይገኛሉ፤ አብዛኞቹ ደግሞ ጎዳና ተዳዳሪዎች (ባለቤት አልባ) ናቸው ውሻ የእብድ ውሻ በሽታን Rabbis በማስፋፋት ትታወቃለች። በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እየጨመረ የመጣውን የባለቤት አልባ ውሾች ቁጥር ለመቀነስ ሴት ውሾችን እንዳይወልዱ የማምከን ሥራ ቢሠራ ሸጋ ነው። በሽታው ለሰዎችም ሆነ ለሌሎች እንስሶች ጠንቅ ስለሆነ በቀደሙት ዘመናት በመዲናዋ፤ጎዳና ተዳዳሪ ውሻ አይገኝም ነበር። አሁን እናቴ መዲናው ሰፍቶ ፓስተርም ውሾቹን ለማስወገድ ተቸገረ። ቀደም ሲል በተለምዶ ፓስተር የሚባለው ጤና ተቋምና ማዘጋጃ ቤት በሌሊት በየሠፈሩ እየዞሩ ውሾችን ገድለው በመኪና ጭነው ይሄዱ ነበር። አሁን በግል ግቢያቸው ውሻ ያላቸው በተወሰኑ ወራት ልዩነት ወደ ፓስተር እየወሰዱ ውሾችን ያስከትባሉ። በአንዳንድ ብሔራዊ ፓርኮችም የቤት ውሾች ከፓርክ እንስሶች ጋር የሚገናኙባቸው አጋጣሚዎች ስላሉ ቀይ ቀበሮ፣ ዋሊያ የመሳሰሉ ውድና ብርቅ እንስሶቻችንንም እንዳናጣቸው የሚመለከታቸው አካላት እንዲመለከቱት አመለክታለሁ።

ውሾች የሚበሉት ሲያገኙ እርስ በርስ ሊባሉ ይደርሳሉ። ግን ሌባ ሆነ ጅብ በአካባቢያቸው ቢመጣ ልዩነታቸውን ጥለውት በኅብረት ሊያጠቁትና ሊያባርሩት ይጮኹበታል። በክረምት ወራት ውሾች ሙቀት ለማግኘትና ዓለማቸውን ለመቅጨት ተሰብስበው ይሳረራሉ፤ሲጮሁ ያድራሉ፤ እርስ በርስም የሚጣሉበት አጋጣሚ አለ። ሰው የሚሞት ከሆነም በመጮህና በማላዘን ሌሊቱን ስለሚረብሹት አዋቂ ሰዎች በሠፈሩ የሚሞት ሰው አለ ማለት ነው ይላሉ። በጎዳና ተዳዳሪዎች ዘንድ ውሻ ሌሊት በሚያድሩበት አይለያቸውም በ‹ቴክኒክ› ስህተት ባመሸሁባቸው ቦታዎች ውሾች ጎዳና ተዳዳሪዎች ከተኙበት ጎን ወይም ባደረቡት ልብስ ላይ ሲተኙ አይቻለሁ።

በገጠር ከብቶች በበረት እህል በጎተራ ስላለ ውሻ ሌሊት ከጅቦችም ከቀማኞችም ሀብቱን ከብቱንም በሉት ኩበቱንም ይጠብቃሉ። ጅብ ሲመጣ እንደሚጠቃ ስለሚሰጋ በጥንቃቄ ሳይጠጋ ይጮህል። ተረቱም ‹‹ውሻ ካልቀበጠ ጅብ አይበላውም›› ይላል። በአንዳንድ ገጠሮች ከአንጀት ጋር ተደርጎ በሚሰጣቸው ቂጣ ለጅብ ፈሪ ሳይሆን ዐይን አውጣ ሆነው ይገኛሉ። ጅብም ሊበላቸው አይደፍርም የሚሉ ሰምቻለሁ። ብዙ ውሾች ከሆኑም አንዱን ጅብ አሳደው ነካክሰው ማባረርና መብላት ይችላሉ።

በርዘመሃር የተባለ ፈላስፋ፤ ውሻ አንዳንዴ የሚልከሰከስና ርኩስ ተብሎ ቢናቅም ስድስት ነገሮች ገንዘብ ያደረገ ነው ይላል። ፍቅር፣ ትህትና፣ መስማማት፣ ልቦና፣ ተስፋ እና ምስጋና ናቸው። ርኩስ ተብሎ የሚናቀው ውሻ ከላይ የጠቀስናቸውን ጠባያት ያሳያል። ሰው ግን አንዳንዴ ስሜታዊ ሆኖ የተጠቀሱትን ጠባያት ባለመተግበር ከውሻ አንሶ ይገኛል። በሀገራችን ለውጥ የመጣው ነውጥ ስለተከሰተና ሕዝብ ግጭት በቃኝ ስላለ ነው፤ለውጥ ሲመጣ ደግሞ ዜጋው እንደ ውሻ ወደ ጥፋቱ (ውሻ ያስታወከውን ምግብ መልሶ እንደሚልሰው) መላስና መመለስ አማረው። ይህ ከውሻ ማነስ ነው። በየቦታው የጎበዝ አለቃ መሆን ያማራቸው ነፍጥ እያነገቡ የሚያቅራሩትና ሁከት የሚፈጥሩት ሰው የሚያግቱት ፈራንካ የሚጠይቁት ጥቅማቸውንም ሸተው ነው። በየጫካው ሰው የሚያግቱ ይገቱ እንጂ ወንበር ከያዙ ዲክታተር እንደሚሆኑ ዕኩይ ድርጊታቸው ማሳያ ነው።

ውሻ ቢሰድቡት ቢደበድቡት እስኪሞት ከጌታው ቤት አይለቅም፤ መስማማቱ ነው። ውጣ ቢሉት ይወጣል፤ ቁጣውን በትዕግሥት ተቀብሎ ይሄዳል እንጂ ተቆጡኝ ብሎ ጌታውን አይጠላም ልቦናው ይኸ ነው። ውሻ ውጣ ሲሉት ይወጣል፤ ና ሲሉት ይመጣል ይህ ትህትናው ነው። ውሻ በመጮህ እየዞረ የጌታውን ቤት ተግቶ ነቅቶ ይጠብቃል ማመስገኑ ነው። ጌታውን ሲያይ ጭራውን እየቆላና እየቆለመመ ራሱን እያጎነበሰና ቀና እያደረገ መተሻሸቱም ፍቅሩን ሲገልጽ ነው፡፡

> የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀግንነቱን ያህል ሰላም ወዳድም ነው፡፡ በየትም ሥፍራ ቢኖር፣ የትኛውንም እምነት ቢከተል፣ በተለያዩ ቋንቋዎች ቢገለገል፣ ባህሎቹና ልማዶቹ ቢለያዩም ለሰላምና አብሮነት ሰፊ ቦታን ይሰጣል፡፡ ሰላም የእሴቶቹ አንዱ መገለጫ ነው

የሰው ልጆች ጎጥን እምነትንም ሆነ ፖለቲካን ተገን አድርገው እርስ በርስ ሲጣሉ ችግራቸውን መፍታት የሚፈልጉት በሰለጠነ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት ሳይሆን በጦርነትና በግጭት ነው። እገሌን በሉት ገለመሌ፤ የወንዜ ልጅ በሉት የመንዜ ፤ በጎሳ መጠዛጠዝ፣ መመዛመዝ የሚሉት ዕኩይ አባዜ ይታይባቸዋል።

የብሔር ሰበዝ እየመዘዙ ሊያጋጩን የሚሞክሩ እንዳያፍሩ ይጠንቀቁ። ጉዳዩ በቀላሉ የሚተው ስላልሆነ ትኩረት ይሰጠው። በአንዳንድ ቦታ ጥፋተኞች ሲያዙ ይታያል፤ጥፋተኞች ተጠያቂ መሆን ያልቻሉባቸው ቦታዎች አሉ። ፍትሐዊነት ለሁሉም ይዳረስ፡፡

ብሔር ጠል እሳቤዎች ግጭቶችና ሁሉንም አከሳሪ እንጂ አትራፊ አለመሆኑን መገንዘብ ያሻናል። ግጭቶች መንግሥት አይታገስም በሚል መግለጫ ብቻ አይፈቱም። የብሔር ግጭት ሲቀጣጠል ብዙሃኑ በእሳቱ እንደሚለበለብ መገንዘብ ይገባል። ግጭቶቹ በተነሱባቸው ክልሎች ፍትሐዊነት ነግሦ ጥፋተኞች ሁሉ ለፍርድ ሲቀርቡ ማየት እንሻለን። አንዱን እየከሰሱ ሌላውን እያሞገሱ ግዜ መግዛት ግጭት ማባባስ ይመስለኛል። የሚፈለገው የሕዝብ እንባ የሚያባብሱ ሳይሆን የሚያብሱ ነው። በሀገራችን ያለው ግጭት ይህንኑ የሚያስተምረን ነው። መናቆርን ጥለን ፍቅርን አንጠልጥለን መሄዱ ተመራጭ ነው። በመንግሥት ዙሪያ እየተሰማ ያለው ብሔራዊ ምክክር ብዙሃኑን አካታች ሆኖ፤ ግጭቶችን በጠረጴዛ ዙሪያ ፈተን ፍቅር ትህትናን መስማማትን ልቦና ተስፋና ምስጋናን ገንዘብ ለማድረግ ከላይ ከጠቀስናቸው ግን ከምንንቃቸው ውሾች እንማር።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጀግንነቱን ያህል ሰላም ወዳድም ነው። በየትም ሥፍራ ቢኖር፣ የትኛውንም እምነት ቢከተል፣ በተለያዩ ቋንቋዎች ቢገለገል፣ ባህሎቹና ልማዶቹ ቢለያዩም ለሰላምና አብሮነት ሰፊ ቦታን ይሰጣል፡፡ሰላም የእሴቶቹ አንዱ መገለጫ ነው።

ሆኖም ከዚህ የኢትዮጵያውያን ባህል ባፈነገጠ መልኩ ፍላጎታቸውን በነፍጥ ማሳካት የሚፈልጉ ብድኖች እየተበራከቱ መጥተዋል። ከውይይት ይልቅ ነፍጥ ማንሳት የሚቀናቸውና ሰላም ወዳዱን ህዝብ የሚረብሹ፤አብሮነቱን የሚያውኩ፤ የኢትዮጵያን መረጋጋትና ሉአላዊነት የሚገዳደሩ ቡድኖች እዚህም እዚያም አቆጥቁጠዋል፡፡

እነዚህ ወገኖች በሚፈጥሩት ሁከትና ብጥብጥም ልማት ተደናቅፏል፤የሰዎች ወጥቶ መግባት ተስተጓጉሏል፤አለፍ ሲልም የሀገር ህልውናም አደጋ ላይ ወድቋል። ስለዚህም ነፍጥ አንስቶ ይዋጣልን ማለት ጊዜ ያለፈበት ጀብድ መሆኑን መረዳት ይገባል።

# የዘመን ጥበብ

# ሳቢሳ ጥበባት

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ሦስት የጥበብ ዘለላ፣ ከሁለት ስፍራዎች ተምሰው በአንድ ስብጥር ከቻልን ህምራዊ ስናደርጋቸው፣ ሳቢሳ ጥበባቱን ከዚህም ከዚያም አምጥተን ብናዳብላቸው "ጠቦናል ልቀቁን!"፣ አንዱም በሌላው ተነስቶ "ከግዛቴ አስወጡልኝ!" እንደማይባባሉ ተስፋ እናድርግ።

ሀሳብ በሀሳብ፣ ቃላት በቃላት፣ ፊደላቱም በፊደላት ላይ አመጽ እንደማይቀሰቅሱ እርግጠኞች ከመሆን ሌላ አማራጭ የለንም። ምክንያቱም ሳቢሳ ነው። ከወዲህና ወዲያ የተከናወኑ ጉዳዮች ከዚህች አንዲት ገጽ ሞልተው የሚፈሱ ቢሆንም እንደምንም እያሽጋሸግን ከአንዲት መደብ ላይ ማስተኛቱ ግድ ነው።

ከአንድ መሶብ፣ ከጉርሻ ማዕድ ፊት እናስቀምጣቸው። "ፍቅር ካለ ለሁሉም ይበቃል" ይለዋልና ጠጋ በፍቅር ያቆነጃል። የዛሬውን የጥበብ ጎተራ ሊሞሉልን የተዘጋጁ በርከት ያሉ ጉዳዮች ከየፌርማታው ላይ ቆመው እኛኑ ይጠባበቃሉ።

ጥበብ በየፈርጁ ከግራና ቀኝ ከነፈሰው ጋር ነፍሰን፣ ከሚወርደውም ብናፍስ በረከት ነው። ያሳለፍነው ሳምንት በጥበብ ቤት በሽ በሽ ነበር። ከሀሳቦቻችን አንደኛው ሀሳብ መቅረዝ ያቆማቸው ወጣቶችና ተውኔት ያጌጠው መጽሐፍ ነው። ሁለቱም ከአንድ ገበታ ላይ የተገኙ ማዕድ ናቸው።

ወጣቶቹ ጥበብን እያጠገቡን፣ መጽሐፉ ደግሞ "የወንዜ ሳቢሳ" ይለናል። በሦስተኛውና የመጨረሻው ነገር ማስረጊያችን ደግሞ የጥበብ ልጆች ደማምቀው ያመሹበትን የጉማ ሽልማት ስነ ስርዓት በቀጭን ቀጭኑ እንቋጨዋለን፡፡

አስቦና አቅዶም ይሁን ድንገት የጥበብ እግር ጥሎት ወር በገባ በመጀመሪያዋ ቅዱስ ሐሙስ፣ በሐሙሲቷም የጀንበር ማዘቅዘቂያ ላይ ከኢትዮጵያ ቤተ መጽሐፍትና ቤተ መዛግብት(ወመዘክር) አዳራሽ የተገኘ ሰው ከትኩስ የጥበብ አቦል ላይ ይደርሳል። በኪነ ጥበብና ስነ ጽሁፍ ምሽቶች አድገን አሁን መቀንጨር መጀመራችን እሙን ነው።

የሀገራችንን ጥበብ እቅፍ ድግፍ አድርገው የኖሩ ምሽቶች በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ወደጎን እየተጋደሙ ሲወድቁ ተመናምነው እንጥፍጣፊው እንኳን ናፍቆናል። ታዲያ በአሁኑ ጊዜ በከተማችን አዲስ አበባ ውስጥ ከዓመት እስከ ዓመት፣ ወር እየጠበቁ፣ ወር በገባ በመጀመሪያቱ ሐሙስ ለጥበብ አፍቃሪው አንጀት አርስ ለመሆን የበቁ ወጣቶች ስብስብ አለ። "መቅረዝ" ይሰኛል መጠሪያቸው፡፡

የወሯን የመጀመሪያ ሐሙስ እየጠበቁ የጥበብ ስጦታዎቻቸውን ከመቅረዟ ላይ ያኖራሉ። በተለይ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ተወዳጅነታቸው ከፍ እያለ ዝናቸው መናር ጀምሯል። ገብቶ ለመታደም የቻለ ሁሉ እያመሰገናቸው ይወጣል። እኛም እናመሰግናቸው ዘንድ ከሐሙሶች ሁሉ አንዲቷ ሐሙስ ምክንያታዊ ወኔ ሞልታናለችና ከእርሷ ጋር ጥቂት ሽርሽር እናድርግ፡፡

በጥቅምት አደይ አበባ ታጅባ ሰለል! እያለች የምትመጣው የወርሃ ጥቅምት፣ የመጀመሪያቱ ሐሙስ ባሳለፍነው ሳምንት ጥቅምት 7 ቀን ደርሳ፤ ከሩቅ ቆመው በጉጉት ሲጠባበቋት የነበሩት የመቅረዝ ልጆች ተቀብለዋታል። ታዳሚ አጃቢዎቿን ጋብዘው በወመዘክር አዳራሽ ውስጥ ደግሰው አብልተውላታል። አጠጥተው ሸኝተውላታል። ከበሉትና ከጠጡት፣ እንዲሁም ከተሸኙት መካከል ነንና በልተን ዝም፣ ጠጥተን ጭጭ ብንል ጥበብን "ትዝብት ነው ትርፉ" እናስብላታለን።

ወትሮም አንድ ነገር ብቻ ይዘን ከማንወጣበት የመቅረዞች የኪነ ጥበብ ምሽት በጥቅምት ሰባቷ ሐሙስም ከዝግጅቶቻቸው ጋር የተዋቀረ ሌላ አንድ ዝግጅትም ነበር። ከመቅረዟ ያለፌርማታው መውረድ አይሁንብንና ለሁለተኛው የያዝናትን ጨርሰን ቀጥሎ እንመጣበታለን።

የዕለቱ አመሻሽ ግን ለታደመው የጥበብ አፍቃሪ የሚጣል የሌለው፣ የሚመጠጥ ከረሜላ ነበር። በየመሃል መሃሉ ብቅ እያሉ ከሚቀርቡት ሙዚቃዎች ጋር የታዳሚው ስሜት ሲኮበልል በግልጽ ይታይ ነበር። ልክ እንደ ሁሌም የወሩን በዕለቱ፣ የአንድን ታላቅ የጥበብ ሰው ታሪክና ሥራ እያወሱ ሲተርኩ እንደመስማት ደስ የሚል ነገር አልነበረውም። የዚያን ዕለት ባለተራ ደግሞ ኮሎኔል ሳህሌ ደጋጎ ነበሩ፡፡

በመቅረዝ የጥበብ ጀመአ ውስጥ መሬት ቆመው ሰማይ




**በእለቱ የአንቷን ቼኮቭን አራት የትርጉም ተውኔቶች የያዘው "የወንዜ ሳቢሳ" የተሰኘ መጽሐፍ ተመርቋል፣**

የሚቧጥጡ ወጣት ገጣሚያን አሉ። ብዕሮቻቸው በሳልሳና ቡጊቡጊ እየነጠሩ የሚፈሱ ጸሀፊያን በሽ ናቸው። በጥበባዊ ውበት ወግ ወጉን ይዘው በወግና መነባንቦች ፍስሀን የሚያፈልቁ ወጣቶች የመቅረዝን ቤት ሞልተዋታል። ለመጥፋት የሚቃጣቸውን ሽለላና ፉከራ፣ ቀረርቶና መሰሎቻቸው ሁሉ ከመቅረዙ እንዳይወርዱ ወጣቶቹ "መገን!" ይሏቸዋል።

ድምጻ መረዋ፣ ድምጻ ስርቅርቅ የሙዚቃ ባለተሰጥኦ ልጆች ማይኩን ጨብጠው ከመድረኩ ላይ ሲቆሙ አለማድነቅ ያስረግማል። የጥንቱን የኪነት ቡድኖችን ትርኢት ያስታውሱናልና ለአንዳንዶቻችን ከመድረኩ ላይ የቆሙ የኋልዮሽ መስታወቶቻችንም ጭምር ናቸው። ከሁሉም ዓይነት የኪነ ጥበብ ማሠሮዎች ውስጥ እየጨለፉ ታዳሚውን ያጠግቡታልና ቁጥሩ እየጨመረ መሄዱ አልቀረም። ወጣቶቹ ትንታግ ሳተናዎች ናቸው። ክረምት ከበጋው የጥበብን ዘር የሚዘሩ ብርቱ ገበሬዎች መስለው ታዩኝ። ከመድረክ በስተጀርባ ያለውን ጀመአ የጥበብ ህብረታቸውን ስንመለከት ደግሞ ይበልጥ እንወዳቸዋለን። "ሂስ ሳይሆን መዘላዘል ነው ያለው" አለኝ አንደኛው የቡድኑ አባል ሥራዎቻቸው መድረክ ላይ ከመቅረባቸው አስቀድሞ ስለሚዘጋጁበት መንገድ ሲያወጋኝ።

እንደ ጦር እየተወረወሩ የሚሰበቁ የሂስ ቀስቶችን አልፈው እንደሚመጡ ከአቀራረብ ጀምሮ መድረክ ላይ ሲታዩ ያስታውቃሉ። ከስነ ጽሁፍ እስከ ሙዚቃና ተውኔት፤ በግልም ይሁን ጣምራ ክሽን ያለ ሥራና አቀራረብ አላቸው። በመቅረዞች ህብረት ውስጥ ሂስ ያለው ቦታ የተለየ ነው።

ራሳቸውም ይሁኑ ሥራዎቻቸው በዚህ ታሽተው የሚወጡ በመሆናቸው ለጥበብ ውበትን በማልበስ ተወዳሾች ናቸው። መቅረዞች ገና ብዙ ጥበብ፣ ብዙ ማዕድ አላቸው። ቀኗም የቀን ቅዱስ አትረሳምና ከጥበብ ምንጭ ለመቅዳት ወደ መቅረዝ ወንዝ ወረድ ማለት ብቻ ነው፡፡

በዚያው መድረክ ደግሞ ሌላ በረከት...ጠበቃና የቲያትር ባለሙያው ሳምሶን ብሬ የተመሰጠበትንና ተተርጉመው ቢቀርቡ ለኛም የተሻሉ ነገሮችን ሊከስቱ ይችላሉ ያላቸውን የአንቷን ቼኮቭን አራት የትርጉም ተውኔቶች የያዘውን "የወንዜ ሳቢሳ" የተሰኘ መጽሐፍ አስመርቅቦታል። ወደ መጽሐፉ ከመግባታችን አስቀድመን ቼኮቭ ማነው? ለሚለው ጥቂት ምላሽ ብንፈልግ መልካም ነው።

ቼኮቭ ሩሲያዊ ከያኒ ነው። በአጫጭር ልቦለዶቹና በተውኔት ጽሁፎቹ ዓለም ከምታሞግሳቸውም አንዱ ነው። በኋላኛው የህይወት ዘመኑ እነርሱ ከፊት፣ እርሱ ከኋላቸው ሆኖ ዳናቸውን፣ ኮቴያቸውን እግር በእግር ሲከተላቸውና ሲያስከትሉት፣ ሲመለከታቸውና ሲመለከቱት የነበሩ ታላላቅ የተውኔትና ስነ ጽሁፍ ጠቢባን ከፊቱ ነበሩ።

ሊዮ ቶልስቶይ፣ ቲዮዶር ዴስኮቭስኪ፣ አሌክሳንደር ፑሽኪን፣ ሄነሪ ኤፐሰንና በሌሎችም የዘመኑ ፈርጦች ዓይኑን ተክሎ ልቡን ሰቅሎባቸዋል። ስተት ብሎ ከመሃከላቸው ወጥቶ ከመንበራቸው ቆመ። ቼኮቭ ከእነርሱ እግር ስር ብቅ ብሎ እንደመታየቱ ሥራዎቹም የማይተናነሳቸው ሆነው ተገኝተዋል። እንዲያውም በአጫጭር ልቦለዶቹ ሳያስንቃቸው ሁሉ አልቀረም ነበር፡፡

"ልቦለዶቹንማ እርሱ ይጻፋቸው። በአጫጭር ልቦለድ ማን እንደቼኮቭ!" ተብሎለታል። በሙያው ሀኪም ቢሆንም የራሱን ህይወትና ስሜቱን ሲያክም የኖረው ግን በስነ ጽሁፉ ነው። "ህክምና ህጋዊ ሚስቴ ስትሆን፣ ስነ ጽሁፍ ደግሞ ውሽማዬ ናት" የሚላት ፌዝ መሳይ የእውነታ ህይወት አለችው፡፡

ከቼኮቭ የተውኔት ሥራዎች መካከል ሳምሶን ብሬ "የወንዜ ሳቢሳ" በሚለው የትርጉም መጽሐፉ ካካተታቸው መካከል አንደኛው "የትንባሆ ጉዳት" የሚለው ነው። ይህ ተውኔት በ1986ዓ.ም ለመታተም በቅቶ ነበር። ደራሲው ግን ከስድስት ዓመታት በኋላ በ1992 ዓ.ም ህይወቱ አልፏል። ከሞቱ ሁለት ዓመታትን ቀደም ብሎ ደግሞ በ1990ዓ.ም በራሱ በቼኮቭ ተሻሽሎ በድጋሚ የታተመ ተውኔት ነበር።

ቼኮቭ "ዘ ሀርምፉል ኢፌክት ኦፍ ትንባሆ" ሲል የጻፈውን ተውኔት ተርጓሚው ሳምሶን ብሬ ደግሞ "የትንባሆ ጉዳት" ሲል ተርጉሞ ከሳቢሳዎቹ አንደኛው አድርጎታል። ተውኔቱ ባለ አንድ ገቢርና ገጸ ባህሪይ ቧልታይ ተውኔት ነው።

በጥቅምት ሰባቱ የመቅረዝ መድረክ ላይ ምሽቱን ካደማመቁ ዝግጅቶች መካከል አንደኛው ይኼው "የወንዜ ሳቢሳ" መጽሐፍ ውስጥ አንዱ የሆነው "የትንባሆ ጉዳት" ተውኔት ነበር። ተርጉሞ ለምርቃት ያበቃው ሳምሶን ብሬ ራሱ ተውኖታል፤ ከላይ እንደምንመለከተው። የተውኔቱን ርዕስ ገና ከመመልከታችን ጭብጡ ስለምንና ምን ላይ ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ቀላል መስሎ ቢሰማንም የኋላ ኋላ ሀፍረት እንዳያከናንበን ጥቂት ረጋ እንበል፡፡

ለሰማይ ምድሩ ግልጽ፣ ፊት ለፊት ገጦ ጸሐይ ያሞቀው ቀትረ ቀላል ዓይነት ርዕስ ሆኖ ፊጥ ቢልም፤ ስያሜውን አንብበው ብቻ ስለ ጭብጡ ለማውራት ከቃጣን ቀጣፊ ከማስባል አይምረንም። ምክንያቱም የተውኔቱ ጭብጥ እማሬን ከፍካሬ ጋር ያንጠለጠለ በመሆኑ ነው። ከትንባሆ ጉዳት አስከፊነት ቢነሳም መድረሻው ግን ጉራጉር ውስጥ ይሆንና ብዙ ያስቧጥጠናል።

እዚህ ጋር "ኒውከን" አንድ ለተውኔቱ ገጸ ባህሪይ ነው። ኒውከን ከህይወት ብዙ የተማረ አዋቂ ነው። ኒውከን ግን ኑሮው "ገሪባ!" የሚሉት ዓይነት ነው። በዚህ ላይ ደግሞ ለ30 ዓመታት አብሯት የኖረችው ሚስቱ "የዝናብ ጠፈጠፍ" ናት። በሆነ ባልሆነው ሁሉ ቁምስቅሉን የሚያበላው ምላሷ አይጣል ነው። በኑሮና በትዳር ህይወቱ ምርር! ስልችት! ብሎታል። ሲፈራትም ድመት የተመለከተች አይጥ ያህል ነው።

ካለችው ውልፍት ያለ እንደሆን ውርድ ከራሱ! ኒውከን የረዥም ዘመናት የህይወት ጉዞውን በተውኔቱ ውስጥ እያስተከዘና ሳቅ እያስጫረ ወዲህና ወዲያ በቆሙ ስሜቶች ያስንጠናል።

ታዲያ አንድ ቀን ላይ ለተማሪዎች በበጎ አድራጎት ትምህርት እንዲሰጥ በባለቤቱ በኩል ማሳሰቢያ ይደርሰዋል። "...ትምህርት መስጠት ካለብኝ መስጠት አለብኝ። ይኼው ብቻ ነው ምርጫዬ። በእርግጥ ፕሮፌሰር አይደለሁም። የዩኒቨርሲቲ ዲግሪ አለኝ ማለትም አልችልም፤ ሳልጨርስ ተባረርኳ። ግን የሆነ ሆኖ ሳይንሳዊ ችግሮች ላይ ለ30 ዓመታት ጤንነቴን ለችግር አጋልጬ ምርምር አድርጌያለሁ።

...አንድ ቀን አንድ ምስጉን መጣጥፍ ጽፌ ነበር። የመጣጥፉ ርዕስ "የሆኑ ነፍሳት ጉዳት" ይሰኛል። ... ለዛሬው ትምህርት የምሰጥበት ርዕሰ ጉዳይ የትንባሆ ጉዳት የሚለውን መርጬዋለሁ። ትንባሆ በሰው ዘር ጉዳት አድርሷል፤ እኔ ራሴ ግን አጫሽ ነኝ። ...የኔን ትምህርት በቁም ነገር እንድትከታተሉት እፈልጋለሁ። ትምህርቴን በቁም ነገር ካልተከታተላችሁትማ ከሚስቴ ዘንድ ከባድ መከራ ነው የሚወድቅብኝ...ትንባሆ እጽ ነው..." ብሎ ካለ በኋላ ስለ ትንባሆም ሆነ የትንባሆን ስም የጠራው ከሁለት ጊዜና ሁለት ዐረፍተ ነገር አይበልጥም፡፡

እሱም ከጅምር እስከ ማገባደጃው ለተማሪዎቹ ስለ ሚስቱና መከራው ሲያወራ ቆይቶ ድንገት የሷን መምጣት በተመለከተበት ቅጽበት ተርበድብዶ ርዕስ በመቀየር ነበር። ሆኖም ግን ያወራው ነገር ፍካሬያዊ ጭብጡ ስለ ትንባሆ ጉዳት ነበር። የቼኮቭ አራት የተውኔት ሥራዎች "የወንዜ ሳቢሳ"ን ሆነው መምጣታቸው ለስነ ጽሁፍና ቲያትር እድገታችን የሚያስቀስመው ይኖረዋል።

አሁን አሁን የትርጉም ሥራ የሆኑ ተውኔቶችን ከቲያትር መድረኮች ላይ የምናይበት አጋጣሚዎች ጥቂት ናቸው። አቅልን ስተው የሙጢኝ የሚሉበት ባይሆንም "አይመከረም!" የሚባል ደግሞ አይደለም። እንግዲህ "አሳን መብላት በብልሃት" ነው፡፡

በስተመጨረሻ አንዲት የጥበብ መረቅ ጠብ እናድርግባት። ላስታወስን ከዚህ ቀደም በጥቅምት 8 ቀጠሮ ነበረን። ቀጠሮውም የጉማ፣ ዕለቱም በአርብ ነበር። ብዙም ሳንርቅ ከዕለተ ሐሙስ አመሻሽ ወደ ቀጣይዋ ምሽት ሻገር ስንል ጉማን እናገኛለን። ሸራተን አዲስ በጥቅምት 8 የጉማ ምሽት ታላላቆችን ተቀብላ ታላቅ ሆና አምሽታለች። ከአርቲስቶቹ እስከ ጥበብ አፍቃሪያንና የክብር እንግዶች በአዳራሹ ጢም ብለው ታይተዋል።

ቀደም ሲል ያላሰፈርናቸው አንዳንድ ነገሮችን መስፈሪያው በተገኘ መጠን ብናሰፍረው መልካም ነው። በእጩነት ቀርበው ምሽቱ የለያቸውን አደይ ጉማዎችን በአጭሩ እናነሳሳቸው። ባሳለፍነው ሳምንት የአርብ ምሽት የጉማ ሽልማት ስነ ስርዓት እንደ ዝግጅት ባማረ መልኩ ተጠናቋል። የፈራነው ደርሶ፣ የጠላነው ወርሶ እንደሆን ግን ፍርዱን ለናንተው እንተወው። በቅርብ የኋልዮሽ፣ በአንደኛው አምዳችን ውስጥ የህይወት ዘመን ተሸላሚዋን ፍቅርተ ደሳለኝ፣ የሄርሜላዋን አዜብ ከበደንና የአርአያ ሰብ ከያኒውን ይገረም ደጀኔን አንስተናል።

አሁን ለትውስታ ይሁነንና በ10ኛው ጉማ ከእጩነት ወደ ሽልማት ገበታ ቀርበው የተመገቡ ቀሪዎቹ እንዲህ ተከታትለዋል...በምርጥ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ወንድ ተዋናይ ዘርፍ ጉማን ያጠለቀው አንጋፋው አርቲስት አበበ ባልቻ ሲሆን የታጨው ደግሞ "በህግ አምላክ" በተሰኘው ተከታታይ ድራማ ነበር።

በወንድ ካሉ ቀጥሎ በሴትም አለና በዚህ ደግሞ መዓዛ ታከለ ከ"አፋፉ" ድራማ ነበረች። በፊልሙ ኢንዱስትሪ፣ በድራማው ዘዋሪ ምርጥ ምርጦቹ ተብለው በምርጥ ዋና ወንድ ተዋናይ ሙላለም ታከለ ከ"ገምዛ" ፊልም፣ በምርጥ ዋና ሴት ተዋናይት ደግሞ ቃልኪዳን ጥበቡ በ"ልባም ሴት" ተመርጠዋል።

በምርጥ ረዳት ወንድና ሴት ተዋናያን ቴዎድሮስ ተሾመ ከ"ዝምታዬ" እና ድርብወርቅ ሰይፉ ከ"ዶቃ" ፊልሞች፤ ደረጃ ሁለትን በበላይነት አጠናቀዋል። ነገን ለዋናው ተስፋ ያደርጋሉ። እነርሱ እያደረጉም በአመቱ ምርጡ ተስፋ የተጣለባት ተዋናይት መቅደላዊት ግርማ ከ"ሌባ እና ሌባ" እንዲሁም በወንዶች በረከት ግዛው ከ"ጭረት" ፊልም ሆነዋል።

እነዚህን ሁሉ ከፊት ኋላ በሚገራውና የአንድ ፊልም አስኳል በሆነው ዳይሬክቲንግ፤ ቅድስት ይልማ ከ"ዶቃ" ፊልም የዓመቱ ምርጥ ዳይሬክተር ተብላ ክብረ ሽልማቷን ተቀብላለች፡፡

ከተዋንያን ወደ ትወና መንደር፣ ከባለሙያው ወደ ሙያው ስንዘልቅ አንዱ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ነው። ምርጥ ታሪክ፣ ምርጥ ጭብጥ፣ ቆንጆ ምስል፣ ከቆንጆ ድምጽና በሌላም በሌላም የዓመቱ አሸናፊ፤ በዳንኤል ግርማ እና ኑር አክመል ተዘጋጅቶ የተሠራው "እንደ አንድ" ድራማ ነበር።

ከፊልምና ድራማዎች ውስጥ የድምጽ ዉበት አንደኛው ወሳኝ አላባዊ ነውና አበበ አሰፋ እና ቢኒያም ሰለሞን ከ"ዶቃ" ፊልም ተመርጠው ተሸልመዋል። ከድምጹ ኋላና ፊት፣ ከምስሉ በስተጀርባ ምን ሊኖር ይችላል ካሉ አንድም ማጀቢያ ሙዚቃ ነው። ሙላለም ታከለ እና ዘቢባ ግርማ "ወዳጅ" በተሰኘው ፊልም ውስጥ ባስደመጡት ጥኡም ዜማ፤ በምርጥ የፊልም ሙዚቃ ዘርፍ ነግሠዋል። "በምርጥ የፊልም ጽሁፍ" የሚለው ሽልማትም ወደ ዶቃ ፊልም ሄዷል።

ቅድስት ይልማ እና ቤዛ ኃይሉ አሸናፊዎቹ ሆነዋል። በሲኒማቶግራፊው ብስራት ጌታቸው እና ሰዳኪያል አየለ ከፍ ብለዋል። ዶቃ በሜካፑም አልቀረውምና ዳግማዊ አለማየሁ ልቆበታል። በምርጥ የፊልም ስኮር ኢዩኤል መንግስቱ፣ በምርጥ የፊልም ቅንብር(ኤዲቲንግ) ነብዩ ሰኢድ እና ልዑል አባዲ አሁንም ከዶቃ ነበሩ። ዓመተ ዶቃ...በስተመጨረሻም ራሱ "ዶቃ" የአመቱ ምርጥ ፊልም ሆኖ ሮኬቱን አፈነዳው! ጉማም እንዲህ ሲለን እንዲሁ አመሸ።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የእውቀት ብርሃንን ፈንጣቂው - ሙአለ ሕጻናት

ቤዛ እሸቱ

የወይዘሮ ሰናይት የኋላወርቅ የሰርግ ዕለት እድምተኛው “የዛሬ ዓመት የማሙሽ እናት፤ የዛሬ ዓመት የማሙሽ አባት፤”... እያለ ያዜመው ሊሰምር ቀን እየተቆጠረ ነው። የከተማ ነዋሪ ናትና እሷም በሆዷ ያለውም ጽንስ ደህና እንዲሆን የህክምና ክትትል አልተለያትም። ሆኖም የእናትየው የደም ግፊት ከዕለት ወደ ዕለት ከፍ እያለ ሄደ። የሰባት ወር ነፍሰ ጡር እያለች ለጽንሱም ለእናትም ጤና በቀዶ ጥገና (በኦፕራሲዮን) መውለድ እንዳለባት የህክምና ባለሙያዎች ወሰኑ። በሰባት ወሯ ወንድ ልጇን ታቀፈች። ይሁንና ህጻኑ ያለጊዜው በመወለዱና ኪሎው አነስተኛ በመሆኑ ለተወሰነ ጊዜ በሆስፒታል ቆይቶ ህክምና ማግኘት የግድ ነበር፡፡

እናትና አባት ሳሙኤል ደረጄ ሲሉ የሰየሙት የበኩር ልጃቸውን የህክምና ክትትል አጠናቀው በደስታ ወደ ቤታቸው አመሩ። ከሦስት ወር በኋላ የልጃቸው አይን ላይ ችግር መኖሩን አስተዋሉ። ህጻን ሳሙኤልን ይዘው ወደ ህክምና ተቋም አመሩ። ያኔ ታዲያ የአይን ብርሀኑን ለመመለስ ጊዜው ማለፉንና ረቲናው በመላቀቁ አይነስውር መሆኑ ተነገራቸው። የልጃቸውን ዕይታ ለማሻሻል በርካታ የህክምና ተቋማትን አንኳኩ። ህጻኑ ማሞቂያ ክፍል እያለ አስቀድሞ በህክምና ባለሙያዎች መታየትና ተገቢውን ህክምና ማግኘት የነበረበት መሆኑ ተገለጸላቸው። እነሱ ወደ ህክምና የወሰዱበት ወቅት በአይኑ ላይ የደረሰውን ጉዳት መመለስ የሚቻልበት ጊዜ ካለፈ መሆኑ ተነገራቸው።

እውነታውን ተቀብለው በቤት ውስጥ ለልጃቸው አስፈላጊውን ፍቅር እየሰጡ ቆዩ። ልጃቸው ለትምህርት ሲደርስ ለልጃቸው የእውቀት ብርሃንን ሊሹ አማራጮችን ለማየት ሞከሩ። ያኔ ታዲያ አይነስውር ህጻናት ሰባት ዓመት ሲሞላቸው ቀጥታ አንደኛ ክፍል መግባት እንጂ ሙአለ ህጻናት አልነበረም። ሌሎች ሙአለ ህጻናት ውለው ሲመጡ የእሷ ልጅ እቤት መዋሉ ያልተዋጠላት እናት ብቻዋን በምትብሰለሰልበት ወቅት አንድ እናት ከእሷ ጋር ተመሳሳይ ሀሳብ ይዛ በመገናኛ ብዙሀን አየቻት። ተመሳሳዮች ይሳሳባሉ ነውና አድራሻዋን ፈልጋ አገኘቻት። መሰል ልጆች ያሏቸው ሰባት ወላጆች የጋራ ህብረት ፈጥረው “ለምን ለልጆቻችን መማሪያ አንከፍትም?” ሲሉ በጋራ መከሩ። ያኔ ቪዥን ማየት የተሳናቸው ህጻናት ወላጆች በጎ አድራጎት ድርጅት ተመሰረተ፡፡

የድርጅቱ መስራችና ምክትል የቦርድ ሰብሳቢ ወይዘሮ ሰናይት የኋላወርቅ ድርጅቱ እንደተመሰረተ ለአይነስውራን ህጻናት ከክፍያ ነጻ ሙአለ ህጻናት መከፈቱን ታስረዳለች። መጋቢት 6 ቀን 2014 ዓ.ም የተመሰረተው ድርጅት ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ የግለሰብ ቤት በመከራየትና በልዩ ፍላጎት የሰለጠኑ መምህራንንና ሞግዚቶችን በመቅጠር ለአይነሥውራን ህጻናት ከክፍያ ነጻ የሙአለ ህጻናት ትምህርት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል። ድርጅቱ ለጊዜው ዋና ትኩረቱ የሙአለ ህጻናት ትምህርት ላይ ሲሆን፤ በቀጣይ ያለጊዜአቸው የሚወለዱ (ፕሪማቹር) ህጻናት ላይ አይነስውርነት እንዳይከሰት መከላከል እና አነስተኛ አቅም ያላቸውን የአይነስውር ህጻናት ወላጆችን በኢኮኖሚ የመደገፍ ሀሳብ አላቸው። ትምህርት ቤቱ ቋሚ መደበኛ ገቢ ባይኖረውም ሙአለ ህጻናቱን ያዩ ግለሰቦች በሚያደርጉት ድጋፍ እስካሁን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መቆየቱን ታነሳለች፡፡

የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌታቸው ደጀን ድርጅቱ ለአይነስውር ልጆቻቸው በቂ የትምህርት እድል ማግኘት ባልቻሉ ሰባት ወላጆች መመስረቱን ይናገራል። መስራቾቹ የልጆቻቸውን ችግር ለመቅረፍ ሲንቀሳቀሱ ከእነሱ አልፈው ለሌሎች ልጆችም መትረፍ የቻለ ድርጅት መስርተዋል። ከትምህርት አገልግሎቱ በተጨማሪ ለወላጆች የግንዛቤ ፈጠራም ይሰራል። በተለያየ መንገድ ድጋፍ ከሚያደርጉ ወገኖች በሚገኘው ገቢ ድርጅቱ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ይጠቅሳል። ያም ቢሆን ውድ የሆነ የቤት ኪራይ እንደሚከፍሉና የመምህራን ደመወዝ ክፍያ፣ የተማሪዎች የመማሪያ ቁሳቁስና የሥልጠና ግብአት ለማሟላት ቋሚ ባልሆነና ከግለሰብ በሚገኝ ድጋፍ ወጪዎቹ ይሸፈናሉ። በዚህ የተነሳ ድርጅቱ ችግር ላይ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡

ከክፍያ ነጻ የትምህርት አገልግሎት በሚሰጡ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች እያሉ የነሱ ድርጅት ትምህርት ቤት ያቋቋመበትን ምክንያት ሲያስረዳም፤ በአካቶ ትምህርት አይነስውራን ህጻናት ከሌሎች አካል ጉዳት ካለባቸው እንዲሁም የአካል ጉዳት ከሌለባቸው ጋር ተቀላቅለው እንዲማሩ የሚል ፕሮግራም መውጣቱን ይጠቅሳሉ። ነገር ግን ተግባራዊ በሚደረግበት ወቅት የመስማት ችግር የእይታ ችግር እንዲሁም ሌሎች ችግር ያለባቸውን ልጆች አንድ ላይ በአንድ ክፍል በሚማሩበት ወቅት ያለባቸውን የአካል ጉዳት ግምት ውስጥ ያስገባ የትምህርት አሰጣጥ ፕሮግራም አይኖርም። ተማሪዎች በጋራ አንድ ክፍል ተቀምጠው እንዲማሩ መደረጋቸው ህጻናቱን ውጤታማ እያደረጋቸው ስላልሆነና ማግኘት ያለባቸውን እውቀት እያገኙ ስላልሆነ ትምህርት ቤቱ መከፈቱን ያነሳል።



ለአይነሥውራን ህጻናት ከክፍያ ነጻ የሙአለ ህጻናት ትምህርት አገልግሎት እየተሰጠ ነው፤

ትምህርት ቤቱ የሚገኘው ለብዙሀኑ አማካኝ ቦታ ባለመሆኑ ህጻናቱ ወደትምህርት ቤት እንዲሄዱ ወላጆች በየቀኑ ለከፍተኛ የትራንስፖርት ወጪ ይዳረጋሉ። በዚህ ምክንያት የኢኮኖሚ አቅማቸው የሚችል ወላጆች ብቻ ልጆቻቸውን ሲያስተምሩ የትራንስፖርት ወጪውን መሸፈን ያልቻሉ በርካታ ወላጆች ልጆች ትምህርታቸውን ለማቋረጥ ተገደዱ።

እንደ ምክትል ቦርድ ሰብሳቢዋ ማብራሪያ የትራንስፖርት አገልግሎት ቢመቻች በርካታ ቤት ውስጥ ያሉ ህጻናት ወደ ትምህርት ቤት ይመጣሉ። ለተማሪዎቹ የምገባ አገልግሎትና የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ የታቀደ ቢሆንም የድርጅቱ ገቢ ይህን ለማድረግ ውስን በመሆኑና ቀጣይነቱ ላይ እርግጠኛ መሆን ስላልተቻለ ጀምሮ ከማቋረጥ በሚል አገልግሎቱ ሳይጀምር ቀርቷል። በቀጣይ ድርጅቱ የተሻለ ገቢ ካገኘ የተማሪዎች ምገባና የህክምና አገልግሎት እንደእቅድ በመያዙ የማስጀመር ሃሳብ አለ፡፡

ወደ ድርጅቱ ልጆቻቸውን ለማስመዝገብ ከሚሄዱ ወላጆች ውስጥ የተወሰኑት የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲመቻች ይጠይቃሉ። ይህን አገልግሎት ማግኘት ባለመቻላቸውም አመላልሶ የማስተማር አቅም እንደሌላቸው በመግለጽ የሚቀሩ ወላጆች አሉ። ድርጅቱ በአዲስ አበባ ቅርንጫፎችን በመክፈት ህጻናቱ ብዙ ርቀት ሳይጓዙ ወላጆችም ለከፍተኛ ወጪ ሳይዳረጉ የትምህርት አገልግሎት የሚመቻቸበት ሁኔታን ለመፍጠር ሀሳብ አለ። የድርጅቱ ትልቅ ወጪ የኪራይ ክፍያ ነው የሚለው ሥራ አስኪያጁ አቶ ጌታቸው፤ ድርጅቱ የትምህርት አገልግሎት የሚሰጥበት ለሁሉም አካባቢዎች አማካኝ የሆነ የማስተማሪያ ቦታ ቢመቻች ትልቁ የድርጅቱ ችግር ይቃለላል ይላል። ይህም ያሉትን ተማሪዎች ቁጥር ከመጨመር ባሻገር የትምህርት ጥራቱን ማሻሻልና ተማሪዎቹ በምቹ ሁኔታ እንዲማሩ ማድረግ ያስችላል። ሕብረተሰቡ የተለያዩ ወጪዎችን ለመሸፈን የገንዘብም ሆነ የአይነት ድጋፍ በማድረግ ድርጅቱን ከመዘጋት እንዲታደገው ጥሪ አቅርቧል።

# ዓለም አቀፍ

## የጋዛን ኢኮኖሚ ወደ ነበረበት ለመመለስ 350 ዓመታት ሊወስድ እንደሚችል ተመድ አስታወቀ

የጋዛን ኢኮኖሚ ወደ ነበረበት ለመመለስ እና ለመልሶ ግንባታ 350 ዓመታት ሊወስድ እንደሚችል ተመድ አስታወቀ::

የተመድ የንግድ እና ልማት ኮንፈረንስ ማክሰኞ ይፋ ባደረገው ሪፖርት ጦርነቱ ነገ ካበቃ እና ጋዛን ወደ ቅድመ ጦርነት ደረጃዋ ለመመለስ 350 ዓመታት ሊወስድ እንደሚችል አስታውቋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኤጀንሲዎች ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ እጅግ ገዳይ እና አውዳሚ ወታደራዊ ዘመቻዎች አንዱ እንደሆነ የሚነገርለትን የጋዛ ጦርነት ለመልሶ ግንባታ አስርት ዓመታትን ሊወስድ እንደሚችል ሲያስጠነቅቁ እንደሰነበቱ ይታወሳል፡፡

አሁን ጦርነቱ ከተጀመረ ከአንድ ዓመት በኋላ እየወጡ የሚገኙ አዳዲስ ሪፖርቶች ደግሞ የጋዛን ኢኮኖሚ መልሶ ለመገንባት መቶ ዓመታትን ሊወስድ እንደሚችል እያመላከቱ ነው፡፡

የመልሶ ግንባታው እና ኢኮኖሚውን ድጋሚ ለማነቃቃት የሚወስደውን ጊዜ ለማሳጠር እስራኤል የጣለችው የእንቅስቃሴ እገዳ ሊነሳ ይገባል ተብሏል፡፡

ከጦርነቱ በፊት ሀማስ በ2007 ስልጣን ከያዘ ጀምሮ ጋዛ በእስራኤል እና በግብፅ ኢኮኖሚያዊ እገዳ ስር ነበር፡፡

በሃማስ እና በምዕራቡ ዓለም የሚደገፈው የፍልስጤም አስተዳደር በዌስት ባንክ መካከል የተደረጉ አራት ጦርነቶች እና መከፋፈል እንዲሁ በጋዛ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ ጫናን አሳድረዋል፡፡

አሁን ያለው ጦርነት በግዛቱ ላይ አስከፊ ውድመት አስከትሏል፣ መንደሮች በሙሉ ወድመዋል፣ መንገዶች እና ወሳኝ መሰረተ ልማቶች ፈርሰዋል።

መልሶ ግንባታው ከመጀመሩ በፊት በአስከሬን እና ባልፈነዱ ቦምቦች የተሞሉ ፍርስራሾች እና ተራሮች መጽዳት አለባቸው።

የተመድ የንግድ እና ልማት ኮንፈረንስ ማክሰኞ ይፋ ባደረገው ሪፖርት ከ2007-2022 በጋዛ የነበረው ዓመታዊ ጥቅል ምርት እድገት 0.4 በመቶ ሲሆን እስራኤል አሁን ተግባራዊ እያደረገች በምትገኘው እገዳ ጋዛን በ2022 ወደነበረበት ኢኮኖሚያዊ እድገት ለመመለስ 100 ዓመታትን ይፈልጋል ብሏል፡፡

እስራኤል እገዳው ያስፈለገው ሃማስ የጦር መሳሪያ እንዳያስገባ ለማድረግ ነው ስትል ታጣቂ ቡድኑን ለጋዛ ችግር ተጠያቂ አድርጋለች።

በተባበሩት መንግሥታት የእስራኤል አምባሳደር ዳኒ ዳኖን ለሪፖርቱ ምላሽ ሲሰጡ “የጋዛ ህዝብ በሃማስ መያዙን እስከቀጠለ ድረስ የጋዛ ነዋሪዎች የወደፊት ተስፋ የላቸውም” ብለዋል።


በጥር ወር መጨረሻ የዓለም ባንክ በጋዛ የደረሰው ጉዳት 18.5 ቢሊዮን ዶላር እንደሚገመት አስቀምጦ ነበር፤ ይህ ግምት የእስራኤል ታንኮች እና የአየር ጥቃቶች በደቡባዊ ራፋህ እና በሌሎች ከፍተኛ ጉዳት በደረሰባቸው የጋዛ አካባቢዎች ጠንካራ ጥቃት መከፈት ከመጀመራቸው በፊት የተተነበየ ነበር፡፡

በሌላ በኩል መስከረም ላይ በሳተላይት ምስል ቀረጻ ተመስርቶ በተደረገ የተባበሩት መንግሥታት ግምገማ በጋዛ ውስጥ ከሚገኙት ህንጻዎች ሩብ ያህሉ መውደማቸውን ወይም ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰባቸው አስቀምጧል፡፡

ከ227 ሺህ በላይ የመኖሪያ ቤቶችን ጨምሮ 66 በመቶ የሚሆኑ መሰረተ ልማቶች ጉዳት እንደደረሰባቸው ተናግሯል።

በኖርዌይ የስደተኞች ምክር ቤት የሚመራ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ሰጪዎች ጥምር የሆነው ሼልተር ክላስተር የፈረሱትን ቤቶች ብቻ ለመገንባት ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅ ሲያሰላ 40 ዓመታት እንደሚፈጅ አረጋግጧል።

እንደ ሳኡዲ አረብያ እና አረብ ኢምሬትስ ያሉ ሀገራት ለጋዛ መልሶ ግንባታ ድጋፍ ለማድረግ ፈቃደኛ ቢሆኑም ጋዛ ከእስራኤል ቁጥጥር ነጻ ወጥታ ፍልስጤም ወደ ነጻ ሀገርነት የሚወስዳትን መንገድ ስትጀምር ብቻ ድጋፍ እንደሚያደርጉ አቋማቸውን ገልጸዋል፡፡





## በሱዳን ተመቶ በወደቀው አውሮፕላን ሩሲያውያን ሳይሞቱ እንዳልቀረ ተጠቆመ

በካርቱም የሚገኘው የሩሲያ ኤምባሲ በዳርፉር በወደቀው ሩሲያ ሰራሽ አውሮፕላን ውስጥ የነበሩ ሩሲያውያንን እጣ ፈንታ እያጣራ መሆኑን ገልጿል።

“ኢልዩሺን አይኤል -76” የተሰኘው ሩሲያ ሰራሽ የጭነት አውሮፕላን በሱዳን ጦር ወደተያዘችው ኤል ፋሽር መድሃኒትና ሌሎች ቁሳቁሶችን ጭኖ ሲጓዝ ነበር ተብሏል።

የሱዳን ፈጥኖ ደራሽ ሃይል (አርኤስኤፍ) በግብጽ ጦር አብራሪዎች ሲበር ነበር ያለውን የሩሲያው አውሮፕላን መትቶ እንደጣለው ከትናንት በስቲያ ይፋ ማድረጉ ይታወሳል።

በጀነራል ሃምዳን ዳጋሎ (ሄሜቲ) የሚመራው ጦር ግብፅ በምትፈፅመው ጥቃት የንጹሃንን ህይወት እየቀጠፉ ነው ሲል ይከሳል።

ካይሮ ግን 18ኛ ወሩን በያዘው ጦርነት ለሱዳን ጦር ወታደራዊ ድጋፍ እያደረገች ነው በሚል የሚቀርብባትን ወቀሳ በተደጋጋሚ ውድቅ አድርጋለች።

በዳርፉር ተመቶ ስለወደቀው ሩሲያ ሰራሽ አውሮፕላን ዛሬም እየወጡ የሚገኙ መረጃዎች ማብራሪያ የሚሹና አሻሚ ናቸው።

አውሮፕላኑ ሶስት ሱዳናውያን እና ሁለት ሩሲያውያንን አሳፍሮ እንደነበርና ከቻድ ድንበር አካባቢ ተነስቶ ወደ ኤል ፋሽር ሲጓዝ መመታቱን ሱዳን ትሪቡን ዘግቧል።

የፈጥኖ ደራሽ ሃይሉ በበኩሉ የአውሮፕላኑን ጥቁር ሳጥን (ብላክ ቦክስ) እና የጉዞ ሰነዶችን ማግኘቱን የገለጸ ሲሆን፤ ከግብጽ ጋር ስላለው ግንኙነት ግን ማስረጃ አላቀረበም።

# የኮሪደር ልማቱ እና ተጨባጭ ትሩፋቶቹ

**በጋዜጠኛና ሲኒየር የኮሙኒኬሽን ባለሙያ ሳንዱዘር አሥራት**

አዲስ አበባ የዓለም ሦስተኛ የዲፕሎማሲ ማዕከል መሆኗን በተጨባጭ የሚያረጋግጡ አሻራዎችን በሁሉም ረገድ ማኖሯን እንደቀጠለች ነው። የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከመሆኗም ባሻገር የአፍሪካ ሕብረት መቀመጫ የሆነችው መዲናዋ ልዩ ልዩ ዓለም አቀፋዊ ውሳኔዎች የሚተላለፉባት፤የዓለም ሦስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል ሆናም እያገለገለች ትገኛለች። የባለ ብዙ የትብብር መድረክ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶችን ጨምሮ የዓለም የዲፕሎማቲክ ልዑካን መሰብሰቢያና መኖሪያም ጭምር ነች።

ከምስረታዋ ጊዜ አንስቶ ከተማዋ፤ በአዝጋሚ የለውጥ ሂደት አልፋ አሁን ወደምትገኝበት ነባራዊ ሁኔታ ላይ ደርሳለች። በወርሀ መጋቢት 2010 ዓ.ም በሀገሪቱ የተደረገውን የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ ወሳኝ የገፅታ ግንባታና ፈጣን ‹‹የስማርት ሲቲ›› የለውጥ ተግባራትን በጊዜ የለንም መንፈስ እያከናወነች ትገኛለች፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በርዕሰ መዲናዋ አዲስ አበባ፤ ለዘመናት የልማት ሥራዎችን በሚፈለገው ፍጥነትና ጊዜ ጀምሮ መጨረስ አዳጋች ነበር። አዳዲስ የልማት ሥራዎችን ደረጃ በደረጃ መጀመርን ጨምሮ ቅንጅታዊ የፕሮጀክት አመራር ውስንነት በጉልህ ይስተዋልም ነበር። ከዚያም አልፎ በየአካባቢው የብሶትና የህዝባዊ ቁጣም ምንጭ መሆኑ የቅርብ ግዜ ትዝታ ነው።

የፕሮጀክቶች አመራር ክፍተት፣ ብክነትና ምዝበራ በተደጋጋሚ ከማጋጠሙ የተነሳ፤ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎችና ምሁራን ጨምሮ የሚመለከታቸው አካላት ተደጋጋሚ ወቀሳ ይሰነዘር እንደነበር የቅርብ ግዜ ትውስታ ነው። ለዚህም የዓባይ ግድብን ጨምሮ፤ ሌሎችም ወሳኝ ሀገራዊ ሜጋ ፕሮጀክቶች የገጠማቸው ችግርና በዋቢነት ማንሳት ይቻላል፡፡

ለዚህ ነው የለውጡ አመራር ከላይ ያነሳሁትን ጉልህ ችግር ሊያሻሽል የሚያስችል ስር ነቀል ለውጥ ለማድረግ የተገደደው። በተለይ ፕሮጀክቶችን ጀምሮ መጨረስን ማእከል ያደረጉ መሻሻሎች መታየት መጀመራቸው የነበረውን ጉድለት በጉልህ ያመላከተ ሆኗል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ከተደረገው የመንግሥት ለውጥ ወዲህ፤ የነዋሪውን ሁለተናዊ የልማት ተጠቃሚነትን ጨምሮ በምርጫ ወቅት ለህዝቡ የገባቸውን ቃሎች ደረጃ በደረጃ በተግባር ለመፈጸም እንዲያስችለው ዘርፈ ብዙ የከተማ ልማት ዕቅዶችን ፤ግዜ ወስዶና በጥናት ለይቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በሁለንተናዊ መልኩ ከተማዋ ወደ ፈጣን የለውጥ ሂደት እንድትገባ ለማስቻል እየተወሰዱ ያሉ የሪፎርም እርምጃዎችን ተከተሎ በርካታ ወሳኝ የልማት ስራዎች ባልተለመደ መልኩ በተጨባጭ መታየት ጀምረዋል። በአንድ የምርጫ ዘመን ቀርቶ ፤ በተያዘላቸው የግዜ ሰሌዳ ተፈጽመው የማያውቁ የልማት ሥራዎች ከለውጡ በኋላ ከ60ና 90 ቀናት ባጠረ ግዜ ተፈጽመው፤ ለታለመላቸው ህዝባዊ አገልግሎት ክፍት ማድረግ እየተለመደ መጥቷል።

የከተማዋን ዓለም አቀፍ ተቀባይነት፡ ገጽታና ደረጃ በሚፈለገው ልክ ማሻሻል እንዲቻል በሁሉም ረገድ እየተከናወኑ ያሉ የስማርት ሲቲ የከተማ ልማት የሪፎርም ተግባራት ፤በጥብቅ የፕሮጀክት አመራር ስነ ምግባር እየተመሩ ነው። ከወትሮ በተለየ መንገድ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የስማርት ሲቲ የከተማ ልማት ተግባራት፤ ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን ጨምሮ የሌሎች ሀገራትን የከተማ ልማት ልምድና ተሞክሮ ከከተማዋ አሁናዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም የሚተገበሩ ናቸው።

የልማት እቅዶቹ በሰው ተኮር የልማት መርህ የነዋሪዎችን ደህንነት በጠበቀ መልኩ የሚከናወኑ መሆናቸው፣ ከፕሮጀክቶቹ የበለጠ ተጠቃሚ የሚሆንበትን እድል እየፈጠረ ነው። የኮሪደር ልማቱ “ሰውነትን በሚያስቀድም መርህ“ የሚከናወን መሆኑም ለዚህ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ቀደም ባለው ወቅት ከአንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ተገንብተው ለአገልግሎት ክፍት የተደረጉ የኮሪደር ልማት ስራዎች፣ አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎች፣ ዓለም አቀፍ የኮንፈረንስ ማዕከላት (ማሻሻያ የተደረገባቸውን ጨምሮ) እንደ አዲስ ተገንብተው ለህዝባዊ አገልግሎት ክፍት በመደረግ ላይ ያሉ የጤና መሰረተ-ልማቶች ፣ የኢንቨስትመንት እና ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖች በአጠቃላይ በከተማዋ የስማርት ሲቲ የከተማ ልማት ፕሮግራም ማሕቀፍ ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው።

**የልማት እቅዶቹ በሰው ተኮር የልማት መርህ የነዋሪዎችን ደህንነት በጠበቀ መልኩ የሚከናወኑ መሆናቸው፣ ከፕሮጀክቶቹ የበለጠ ተጠቃሚ የሚሆንበትን እድል እየፈጠረ ነው፡፡ የኮሪደር ልማቱ “ሰውነትን በሚያስቀድም መርህ” የሚከናወን መሆኑም ለዚህ ተጨባጭ ማሳያ ነው**

የኮሪደር ልማትን ጨምሮ በከተማዋ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉ የከተማ ልማት ዕቅዶች አሁናዊ አፈጻጸም፤ ጀምሮ በጥብቅ ስነምግባር ተቀናጅቶ የመጨረስን አዲስ የፕሮጀክት አመራር ልምድ በሀገር አቀፍ ደረጃ እያስተዋወቀ ያለ ነው። በሁሉም ረገድ እየተከናወኑ ያሉ የልማት ሥራዎች በይበልጥ በግዜ የለንም መንፈስ ተጠናክረው የሚቀጥሉ ስለመሆናቸው በተለያዩ ጊዜያት በተደጋጋሚ ሲነገር ተደምጧል።

ለዚህም ተጨባጭ ማሳያ የሚሆነው፣ በአንድ የምርጫ ዘመን እንኳን በተያዘላቸው የግዜ ሰሌዳ ተፈጽመው የማያውቁ የልማት ሥራዎች ከስልሳና ዘጠና ቀናት ባጠረ ግዜ፤ ተጠናቀው ለታለመላቸው ህዝባዊ አገልግሎት ክፍት መደረግ የመቻላቸው ጉዳይ ነው። ለአብነት ያክል በከተማ አስተዳደሩ በተከታታይ ዓመታት ተገንብተው ለአገልግሎት ብቁ የተደረጉ ወደ 30 ሺ ገደማ ልዩ ልዩ የልማት ስራዎች ተጠቃሽ ናቸው፤የነዋሪውን የኑሮ ጫና በዘላቂነት ለማቃለልም ያላቸው ጠቀሜታም ከፍ ያለ ነው፡፡

እነዚህ የልማት ሥራዎች የከተማዋን ጎስቋላ ገፅታ በሚፈለገው አግባብ እየለወጡ ያሉ፤ ከወትሮ በተሻለ ሰፋፊ የስራ ዕድሎችን የፈጠሩ፤ ወሳኝ የመንግሥት አገልግሎቶችን በቴክኖሎጂ ያሳለጡ ናቸው። የከተማዋን ገቢ ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋገሩ ስለመሆናቸውም በተደጋጋሚ ተገልጿል። በከተማዋ አዲስና እየዳበረ ያለውን አሁናዊ የፕሮጀክቶች የስራ አፈጻጸም ያስገኟቸው ውጤቶች በቀናነት መመልከት ከተቻለ ከተማዋ፤ በሁሉን አቀፍ የለውጥ ሂደት ላይ መሆኗን በልኩ መረዳትና ማድነቅ እንዲሁም መደገፍ ለሚፈልግ አካል ብዙም የሚከብድ አይደለም።

ከለውጡ ማግስት አንስቶ በተከታታይ በፕሮጀክቶች አመራርና አስተዳደር ረገድ በተጨባጭ የታየው ስኬትና ውጤት ሊመዘገብ የቻለው መንግሥት የመፈፀም አቅሙን በማሳደጉ፤ ብክነትን መቀነስ መቻሉን ጨምሮ የልማት አጋሮችን እና የነዋሪውን ሁለንተናዊ አቅም አስተባብሮ መጠቀም በመቻሉ ነው። ለዚህ ከንቲባዋ ለከተማው ምክር ቤት የ2016 ዓ.ም የስራ አፈጻጸምን በማስመልከት በሰጡት ማብራሪያ በግልጽ አስቀምጠውታል። ይህንኑ ጀምሮ የመጨረስ አዲስና እየዳበረ የመጣውን የፕሮጀክት አመራር ልምድ ተከትሎ፤ ከንቲባ አዳነች የቀዳማይ ልጅነት ፕሮግራምን ጨምሮ ከተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሀገራት ልዩ ልዩ የማበረታቻ ሽልማቶችን መቀበላቸውም ይታወሳል።

የከተማዋ የኮሪደር ልማት ትግበራ፤ የጎረቤት ሩዋንዳ ኪጋሊ ከተማን ጨምሮ የሌሎችንም ዓለም አቀፍ ከተሞች ተሞክሮዎችን ዋቢ አድርጎ እንደሚፈጸም ከመሆኑም ባሻገር፤ ከከተማዋ ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ነው። ከተማ አስተዳደሩ የኮሪደር ልማት በሚያልፍባቸው መዳረሻዎች ካሳ፣ ተለዋጭ ቦታና በየደረጃው የሚገኙ ቤቶችን አስቀድሞ እያቀረበ ያለ ስለመሆኑ የልማቱ ተነሽዎች በተለያዩ ጊዜያት ለሚዲያ አካላት ከሰጧቸው ምስክርነቶች መረዳት የሚቻል ይሆናል።

በመጀመሪያው ምዕራፍ አጠቃላይ ግንባታቸው ተጠናቆ ለህዝባዊ አገልግሎት ሙሉ በሙሉ ክፍት ተደርገው ከነበሩት አምስቱም የኮሪደር ልማት መዳረሻዎች መካከል ከአራት ኪሎ በመስቀል አደባባይ አድርጎ እስከ ቦሌ ድልድይ (7 ኪሎ ሜትር) ፤ ከቦሌ አየር መንገድ እስከ መገናኛ ዲያስፖራ አደባባይ (4 ነጥብ 9 ኪሎ ሜትር) ፤ ከመገናኛ ዲያስፖራ አደባባይ በአራት ኪሎ አድርጎ ዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ድረስ (6 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር)፤ ከፒያሳ ዓድዋ ድል መታሰቢያ ዙሪያ፣ በለገሃር ሜክሲኮ፣ በሳርቤት አድርጎ እስከ ወሎሰፈር (10 ኪሎ ሜትር) ባለው የተከናወኑና አሁንም እየተሰሩ የሚገኙ የልማት ሥራዎች በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በአምስቱም የኮሪደር ልማት መዳረሻዎች፤ ከ240 ኪሎ ሜትር በላይ መንገድ እና በተጓዳኝ በፕሮግራም ማሕቀፉ ተካተው የተከናወኑ መሰል መሰረተ ልማቶችን ጨምሮ 70 የከተማዋን የውስጥ ውበት ከመልካም የአየር ንብረት ጠባይ ጋር አዳምረው መንፈስን የማደስ አቅም ያላቸው የህዝብ መናፈሻዎች ተገንብተው የከተማዋ ነዋሪ ከቤተሰቡ ጋር ባመቸው ሰዓት ሁሉ እየተገለገለባቸው ነው፡፡

ከተማዋን በሁሉም ረገድ ተመራጭ የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን ለማስቻል የተያዘውን ራዕይ ከማሳካት አኳያ፤ የከተማዋን ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ወደ ላቀ ምዕራፍ ለማሸጋገር የሚረዱ የፍሳሽ ማስተላለፊያዎች፣ በአይነታቸው ልዩ የከተማዋን ሰላማዊነት የሚያፀኑ የደህንነት ካሜራዎች፣ የብልህ ትራንስፖርት ስርዓት (intelligent transport system) በመሬት ውስጥ የመዘርጋት ስራ ፣ ከ400 የሚልቁ ህንጻዎች ዕድሳትን ጨምሮ ወጥ የቀለምና የመብራት ስራዎች እና ሌሎች ተያያዥ ተግባራት ዘመን ተሻጋሪ አገልግሎት እንዲሰጡ ሆነው በላቀ ጥራት እየተሰሩ ስለመሆናቸው ከተማ አስተዳደሩ የሚያወጣቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ከከተማ አስተዳደሩ የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው ፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ፤ ለኮሪደር ልማት ፕሮግራም ተነሺዎች 6 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር ካሳ ተከፍሏል። ለልማቱ ተነሺዎች በተቀላጠፈ አኳኃን ለሁለት ሺህ 538 ቦታዎች (33 ነጥብ 4 ሄክታር) ምትክ መሬት በከተማው የመሬት ልማት ማኔጅመት ቢሮ በኩል ተላልፏ። በሌላ መልኩ የልማት ሥራው ለከተማዋ ነዋሪዎች ይዞት በመጣው መልካም ዕድል ፤ እጅግ ጎስቁለው ለመኖር አመቺ ያልሆኑ መኖሪያ ቤቶችን ጨምሮ በንግድ ቤቶች ውስጥ የነበሩ በርካታ የልማት ተነሺዎች ምቹ የመኖሪያ እና መስሪያ ቦታ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በአገልግሎትና በአቅርቦት ሥራ ላይ የተሰማሩ ብዙሃን የንግዱ ማህበረሰብ አካላት፤ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በልማቱ ሳቢያ የተፈጠረው ሰፊ የገበያ ትስስር አካል በመደረጋቸው ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና ተጠቃሚነትን በከተማዋ እንዲሰፍን እያስቻለ የሚገኝ የልማት ስራም መሆኑ ተጨማሪ ማስረጃ ሳያሻው በፍሬው የሚታይ ነው።

ከሁለተኛው ምዕራፍ የኮሪደር ልማት መጀመር አስቀድሞ፤ በቅርቡ ተመርቆ ለህዝባዊ አገልግሎት ክፍት የተደረገው የአፍሪካ ፤የኢትዮጵያና የአዲስ አበባ መግቢያ በር ተደርጎ የሚታየው የቦሌ መንገዶች የልማት ኮሪደር ፕሮግራም ርዕሰ መዲናዋ አዲስ አበባ የንግድ፣ የቱሪዝም ፣ የዓለም አቀፍ ኮንፈረንስና የልዩ ልዩ የስማርት ሲቲ አገልግሎቶች ማዕከል በተጨባጭ እየሆነች መምጣቷን ያረጋገጠም ሥራ መሆኑ የበርካቶችን ምስክርነት እያገኘ ነው።

የቦሌ መንገዶች፣ የልማት ኮሪደር ሥራ ወደ ቦሌ ዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ እና ወደሌሎችም የከተማዋ አካባቢዎች በትራንስፖርት የሚደረግን ጉዞ በእጅጉ የተቀላጠፈ እንዲሆን አስችሏል። በቦሌ መንገዶች የኮሪደር ልማት ፕሮግራም ማሕቀፍ የተገነቡ፤ ልዩ ልዩ የቢዝነስ ማዕከላት፣ ሆቴሎች፣ ሬስቶራንቶች እና ሱቆች የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎችን ቀልብ በእጅጉ መሳብ ችለዋል። በዚህም በአካባቢው የሚከናወኑ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የምሽቱን ክፍለ ግዜ ጨምሮ፤ ከፍተኛ የኢኮኖሚ መነቃቃት እንዲታይባቸው ከመሆኑም ባሻገር ፤መጪው ግዜ ለከተማዋ ብሩህ መሆኑን አመላካች ተደርጎ ተወስዷል፡፡

በኮሪደር ልማት መርሀ-ግብር በከተማዋ ተግባራዊ ከሚደረጉ ዝርዝር የልማት ሥራዎች መካከል የመንገድ ኮሪደር ልማት፤ የወንዝ ዳርቻዎች አዋሳኝ የተፋሰስ ልማት ፣ የብስክሌትና ሞተር አልባ የትራንስፖርት አገልግሎቶች ልማት ፣ ዘመናዊ የትራንስፖርት ተርሚናሎች ግንባታ ፣ አገናኝ የኮሪደር ልማት ድልድዮች፣ ማሳለጫዎችና የመጋቢ መንገዶች ልማት፤ የመንገድ ዳር የህዝብ መፀዳጃ ቤቶች፤ ፋውንቴይኖች እና የህዝብ መናፈሻ ስፍራዎች፤ ወጥ የህንጻ ቀለምና የከተማ ማብራት፤ ደረጃቸውን የጠበቁ ፓርኪንጎች፣ የመኪና መጫኛና ማውረጃ አገልግሎቶችን ጨምሮ የአረንጓዴ ልማት ሥራዎችን ያካተቱ ናቸው።

# ስፖርት





# «ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ጥያቄ በማቅረቧ ኮርተናል»

- የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሞሴፔ

ዓስማየሁ ግዛው

ኢትዮጵያ የ2029ኙን የአፍሪካ ዋንጫ ለማስተናገድ ጥያቄ ማቅረባ እንዳኮራቸው የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሞሴፔ ተናግረዋል። ካፍ 46ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውን በአዲስ አበባ አድርጎ ከትናንት በስቲያ ባጠናቀቀበት ወቅት ፕሬዚዳንቱ በሰጡት መግለጫ፣ ኢትዮጵያ አህጉራዊ ውድድሩን ለማዘጋጀት ያቀረበችው ጥያቄ በትክክለኛው ወቅት ላይ መሆኑን ገልፀው በዚህም የካፍ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ኩራት እንደተሰማቸው አስረድተዋል። ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋንጫን ለማስተናገድ ያሳየችው ፍላጎትና እቅድም የሚደነቅ ነው ብለዋል።




የካፍ ፕሬዚዳንት ፓትሪስ ሙሴፔ ጠቅላላ ጉባዔው በስኬት መጠናቀቁን ገልፀዋል፣

ኢትዮጵያ ጠቅላላ ጉባዔው ላይ ለመታደም ከተለያዩ ሀገራት ለመጡ ልዑካን ያደረገችው አቀባበል እንዳስደሰታቸው የገለፁት ሙሴፔ፣ «ኢትዮጵያ ለሁላችንም ቤታችን ናት» በማለት ተናግረዋል። ኢትዮጵያ በእግር ኳስ ትልቅ ታሪክ እንዳላት ያስታወሱት ፕሬዚዳንቱ፣ በኢትዮጵያ ያላው የእግር ኳስ ፍቅርና ስሜት እንዳስደነቃቸው ገልፀዋል።

ፕሬዚዳንቱ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የስፖርት መሠረተ ልማቶችን እንዳስጎበኟቸው በማስታወስ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ለእግር ኳስ እድገት የሚሠራውን ሥራ መታዘባቸውንም ጠቁመዋል። ኢትዮጵያ ጨምሮ 13 ሀገራት የ2029ኙን የአፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት ጥያቄ እንዳቀረቡ የተናገሩት ሙሴፔ፣ የኢትዮጵያን መንግሥትና እግር ኳስ ፌዴሬሽኑን እንደሚያበረታቱም ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንቱ እንደተናገሩት፣ ኢትዮጵያ ውድድሩን ለማዘጋጀት እንደማንኛውም ሀገር እቅዷን የማቅረብ መብት አላት። ጥያቄዋ ተቀባይነት ማግኘት አለማግኘቱም በካፍ አሠራር መሠረት በሥራ አስፈፃሚው የሚታይ ይሆናል።

ሙሴፔ ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጋር ባደረጉት ውይይት የእግር ኳስ እድገት ላይ በመሥራት ትልልቅ እግር ኳስ ተጫዋቾችን ለማፍራት ፍላጎት እንዳላቸው ማስተዋላቸውንም አክለዋል። የኢትዮጵያን የእግር ኳስ መሠረተ ልማቶች ከካፍ ምክትል ፕሬዚዳንት ጋር በመሆን እንደተመለከቱት ጠቁመውም፣ ኢትዮጵያ ውድድሩን ለማዘጋጀት ያላትን ሁሉንም እቅዶች በተቀመጠው ሕግና የአስተዳደር መመሪያ መሠረት እንደሚመለከቱት አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ የካፍ መሥራች አባል እንደመሆና ውድድሩን ለማዘጋጀት እቅዷን እንድታቀርብ አበረታታለሁም ብለዋል። በዚህም መሠረት ሁሉንም መስፈረቶች ካሟላች፣ ውድድሩን ለማስተናገድ እጩ ሆና መቅረብ እንደምትችል ገልፀዋል።

ለአህጉሪቱ እግር ኳስ እድገት፣ በኢትዮጵያ እና በሁሉም ሀገራት የሚሠራው ሥራ ወሳኝ መሆኑንም ገልጸውም፣ በዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት እግር ኳስን የሚወድ በመሆኑ፣ የወደ ፊቱ የሀገሪቱ እግር ኳስ ጊዜ ጥሩ ይሆናል የሚል ተስፋ አላቸው።

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ነጻነት ትልቅ ሚና የተጫወተች ሀገር እንደሆነች ያስታወሱት ሙሴፔ፣ የአፍሪካ ሀገራት ውድድሮችን ለማስተናገድ የካፍን መመዘኛ መስፈርቶችን ያሟሉ ስታዲየሞች መያዝ እንዳለባቸውም አያይዘው ገልፀዋል። አሁን ላይ 24 የአፍሪካ ሀገራት የካፍና የፊፋን ደረጃ የሚያሟላ ስታድየም እንደሌላቸው ገልጸውም፣ ሁሉም ሀገራት ቢያንስ አንድ የካፍና ፊፋን ደረጃ የሚያሟላ ስቴድየም ሊኖራቸው እንሚገባ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ጅራ በበኩላቸው፣ ኢትዮጵያ ለአፍሪካ እግር ኳስ ትልቅ መሰረት የጣለች ሀገር መሆኗን ጠቅሰው፣ የአፍሪካ ዋንጫን ሦስት ጊዜ በማስተናገድ አንድ ጊዜ ዋንጫ ማንሳቷን በማስታወስ በአቶ ይድነቃቸው ተሰማ የካፍ ፕሬዚዳንት ዘመን ለአፍሪካ እግር ኳስ እድገት ትልቅ ሚና መጫወተን ተናግረዋል።

አቶ ኢሳያስ ኢትዮጵያ ከአምስት አስርተ ዓመታት በኋላ የአፍሪካ ዋንጫን አዘጋጅ መሆን እንደምትፈልግና ከአምስት ዓመት በኋላ በ2029 የሚካሄደውን የአፍሪካ ዋንጫ ለማስተናገድ ጥያቄ ማቅረቧን አስረድተው፣ ለዚህም መሳካት በቁርጠኝነት እንደምትሠራ ቃል ገብተዋል። በአሁኑ ወቅት 11 ስታዲየሞች በግንባታ እና በማሻሻያ ላይ እንደሚገኙ ጠቁመውም፣ የካፍ እና ፊፋ መስፈርትን እንዲያሟሉ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

## ትግራይ ክልል

በይግ/ባይ፡- የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓ/ሕግ እና በይግ/መ/ሰጭ፡- አቶ ሕሉፍ ልዑል ደበሱ መካከል ባለው የከባድ ዝርፊያ ወንጀል ክርክር በአድራሻዎ ተፈልገው ስለታጡ ለቀረበብዎት ክስ መልስ እንድትሰጡበት ለ26/2/2017 ዓ/ም ጠዋት 2፡30 ሰዓት በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ወንጀል ችሎት መቐለ ተዘዋዋሪ ችሎት እንድትቀርቡ፣ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ካልቀረቡ ግን ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ወንጀል ችሎት**

በከሳሽ የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓ/ሕግ በተከሳሾች/መልስ ሰጪዎች 1. አቶ ዋስትና ባህራነ ወልደንጉስ 2. አቶ መርሃዊ ዘርአይ ብርሃነ በመካከላችሁ ስላለው የከባድ እምነት ማጉደል ወንጀል ክርክር፣ የትግራይ ክልል ጠ/ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት በ20/01/2017 ዓ/ም በሰጠው ትእዛዝ ተከሳሾች በአድራሻችሁ ተልኮላችሁ ስላልተገኛችሁ፣ በ19/2/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት መቐለ ከተማ በሚሰየመው የትግራይ ክልል ጠ/ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት ቀርባችሁ እንድትከራከሩ፣ ካልቀረባችሁ ግን መዝገቡ በሌላችሁበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን የትግራይ ክልል ጠ/ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት አዟል።

**የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት**

በከሳሽ የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓ/ሕግ በተከሳሽ ታጋይ ደንቡሽ ፀሃየ ብሩህ መካከል ስላለው የግድያ ወንጀል ክርክር በአድራሻዎ ተልኮልዎት ስላልተገኙ ለቀረበብዎት ክስ መልስ እንዲሰጡበት በ14/2/2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:30 ሰዓት ወደ መቐለ ከተማ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ተዘዋዋሪ ችሎት እንዲቀርቡ፤ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ካልቀረቡ ግን ጉዳይዎን በሌሉበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን ፍርድ ቤት አዟል።

**የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት**

በከሳሽ የክልል ዓ/ሕግ እና በተጠሪ ሃፍቶም ገ/ሄር ሃይሉ መካከል ስላለው የከባድ አካል ጉዳት ክርክር፣ ተጠሪ በጠ/ፍርድ ቤት ችሎት የክርክርና ውሳኔ አቤቱታ መዝገብ የቀረበብዎ መሆኑን አውቀው፣ ለ4/3/2017 ዓ.ም 2:30 ሰዓት ጠ/ፍርድ ቤት የሰበር ክርክርና ውሳኔ ችሎት ቀርበው የቃል ክርክር እንዲያካሄዱ፤ ቀርበው የቃል ክርክር ካላካሄዱ ግን መዝገቡን በሌሉበት ታይቶ የሚወሰን መሆኑን ፍርድ ቤት አዟል።

**የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት**

በከሳሽ፡- የትግራይ ክልል ፍትሕ ቢሮ ዓቃቤ ሕግ እና በይግ/ተከሳሽ፡- አቶ ካሕሳይ ማሩ አብርሃ መካከል ስላለው የግ/ግድያ ወንጀል ክርክር በአድራሻዎ ተልኮልዎት ስላልተገኙ ለቀረበብዎት ክስ መልስ እንዲሰጡበት በ18/02/2017 ዓ/ም ከጠዋቱ 2:30 ሰዓት ወደ መቐለ ከተማ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተዘዋዋሪ ችሎት እንዲቀርቡ፤ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ካልቀረቡ ግን ጉዳይዎን በሌሉበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥበት መሆኑን ፍርድ ቤት አዟል።

**የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ችሎት**

በከሳሽ ዐቃቤ ህግ እና በተከሳሽ ጠዓመ ሀጎስ አርአያ በተከሰሱበት በህገወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ክርክር ዓቃቤ ህግ በመሰረተባችሁ ክስ ቀርበው ልትከላከሉ በአድራሻዎ ሊገኙ ስለልቻሉ በዚሁ ማስታወቂያ ለ21/2/2017 ዓ.ም 8፡00 ሰዓት በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ደቡባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማይጨው የወንጀል ምድብ ችሎት ቀርበው ለቀረበልዎት ክስ እንዲከላከሉ፤ በተባለው ቀንና ሰዓት ካልቀረቡ ጉዳዩን በሌሉበት የሚታይ መሆኑ ፍርድቤቱ አዟል፡፡

**የደቡባዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማይጨው ወንጀል ምድብ ችሎት**

## ሐረሪ ክልል

ወ/ሮ መንበረ ጥላሁን ወ/ማርያም የተባለችው 1ኛ ልጄ የሆነው ተማሪ ዳንኤል በጋሻው ኃይሌ የተባለው ጥር 6 ቀን 1967 ዓ.ም ለሕዝብ ቆጠራ ከቤት እንደወጣ እስካሁን ድረስ ሳይመለስ ቀርቷል። 2ኛ አሁንም ልጄ የሆነው ተማሪ አዲስዓለም በጋሻው ኃይሌ የተባለውም በአእምሮ ህመም ምክንያት አዲስ አበባ አማኑኤል ሆስፒታል አስገብቼው በህክምና ላይ እንዳለ ከሆስፒታሉ ውስጥ ታህሳስ 4 ቀን 2012 ዓ.ም ጠፍቶ እስካሁን ድረስ ሊገኝ አልቻለም ብላ በጽሁፍ አመልክታለች ስለዚህ ከላይ ስማችሁ የተመዘገበው ተማሪዎች ካላችሁ በ28/2/2017 ዓ.ም እንድትቀርቡ ወይም እዚህ ቦታ የጠፉት ልጆች አሉ የሚል ወገን ካለ ከላይ በተጠቀሰው ቀን በሐረሪ ሕ/ክ/መንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ቢሮ ይቅረብ፡፡ ባይቀርብ ግን ፍ/ቤቱ የቀረበለትን ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**የሐረሪ ሕ/ክ/መንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት /ሐረር/**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

አመልካች፡- ወ/ሮ ነጃት መሀመድ አህመድ ተጠሪ ፡- አቶ የኑስ ሰኢድ መካከል የባልና ሚስት የፍች ክርክር ጉዳይ ተጠሪ 10/03/2017 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት 1ኛ ችሎት ፍትሐብሔር ችሎት ከጠዋቱ በ3፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍርድ ቤት**

አመልካች/ከሳሽ አቶ ብስራት ተክሉ እና ተጠሪ/ተከሳሽ ወ/ሮ ልዩወርቅ መኮንን መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተጠሪ/ተከሳሽ ወ/ሮ ልዩወርቅ መኮንን ለ11/03/2017ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ላይ በሬጅስትራር መልስ በፅሑፍ እንዲያቀርቡ እንዲሁም ለ17/03/2017 ዓ.ም በ5፡00 ሰዓት በችሎት ለክስ መስማት እንዲያቀርቡ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 1ኛ ቤተሰብ ፍ/ብሔር ችሎት አዟል፡፡ የከሳሽ/አመልካች ክስ ከሬጅስትራር ፅ/ቤት ከቀጠሮ ቀን በፊት ቀርበው እንዲወስዱ እናሳስባለን።

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

አመልካች እነ ለእስራኤል ረዳ መሸሻ ተጠሪ ንግስት ረዳ ላይ የመጥፋት ውሳኔ እንዲሰጣቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ካሉ ወይም ያሉበት የሚያውቅ ሰው ካለ ለጥቅምት 19 ቀን 2017 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት አ/አ/ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአራዳ ምድብ ችሎት**

በአመልካች፡- አቶ ፈንታሁን ገበየሁ ክንዴ እና በተጠሪ፡- ወ/ሮ ኤደን ድንበሩ ከበደ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተጠሪ ወ/ሮ ኤደን ድንበሩ ከበደ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ ፍ/ቤቱ ስላዘዘው ለ04/03/2017 ዓ.ም በ8፡00 ሰዓት ለሆነው ቀነ ቀጠሮ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት መናገሻ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

አመልካች እነ ለእስራኤል ረዳ መሸሻ ተጠሪ አቶ ዳዊት ደስታ ላይ የመጥፋት ውሳኔ እንዲሰጣቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ካሉ ወይም ያሉበት የሚያውቅ ሰው ካለ ለህዳር 2 ቀን 2017 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት አ/አ/ከተማ የመ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአራዳ ምድብ ችሎት**